**ዋና አዘጋጅ፡-**
ይገዛል አረጋ

**ሪፖርተር፡-**
ይገዛል አረጋ
አስቻለው ይርሰማ
ጌትነት መለኩ
መሰረት አለማየሁ
ሄኖክ ከድር
ታደሰ አለማየሁ
መክሊት ይልማ
አቡበከር አሰፋ
ሰላማዊት እሸቴ
አቡበከር አረቦ

**ኤዲተር፡-**
ይገዛል አረጋ

**ፎቶግራፈር፡-**
ብሩክ ተክሉ
ድረስ ወርቁ

**አስተባባሪ፡-**
ሲፈን ባዩ

**ፀሀፊ፡-**
ሰላማዊት ተመልሶ

**ሹፌር፡-**
ዳንኤል ባይሳ

**ፅዳት፡-**
ንጋት ታደገ

**ዲዛይንና ህትመት፡-**
ኤልያና ማተሚያ ቤት
0911 079663
0930 878787

## ማውጫ

1. የአዘጋጁ መልዕክት ....99
2. የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ሃላፊ መልዕክት ....99
3. የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት ....99
4. የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ሃላፊ መልዕክት ....99
5. ስራ ዕድል ፈጠራ ከዳቦ በላይ....99
6. የህዝብ ድምፅና የተጠያቂነት ማረጋገጫ ተቋም ....99
7. በለውጥ ምህዋር ላይ ያለ ተቋም....99
8. ከቤተሰብ ፍጆታ እስከ ገበያ ማረጋጋት ....99
9. ከምርት አቅርቦት እስከ ስርጭት....99
10. ተቋማዊ ስኬታማነት....99
11. የግንባታ ፍቃድ ህጋዊ የማስተካከያ እርምጃዎች....99
12. ግንባታ ለዘላቂ ልማት....99
13. ወጤታማ የበጀት አጠቃቀም ....99
14. ኢንዱስትሪ ልማት ለቀጣ ሀገር ዕድገት....99
15. ስማርቲ ሲቲን የመገንባት ራዕይ በልደታ....99
16. መስሪያ ቦታዎች ልማትና ስኬቶች....99
17. የገበያ ማረጋጋትና የህብረት ስራ ማህበራት ሚና ....99
18. ተቋማዊ አቅም ግንባታ ለብልፅግና....99
19. የመልካም አስተዳደር እምርታ ....99
20. ችግርን በቦታው የመፍታት ጥበብ....99
21. የሰላሙ ዘብ....99
22. ህግ አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም!....99
23. ህግን ማክበር ለህዝብ ጥቅም....99
24. ብክነትን የቀረፈ ተቋም....99
25. መልካም ስነ-ምግባር ለሀገር ዕድገት....99
26. ከትውልድ መቅረጽ እስከ ተቋማት ደረጃ ማሻሻል....99
27. የሴቶች ተሳትፎ ለሁለንተናዊ ተጠቃሚነት....99
28. የህዝብ ጤና እና የአገልግሎት ጥራት....99
29. ስፖርት ለጤና፣ ለስብዕና እና ለኢኮኖ እድገት....99
30. ተፈጥሮአዊ፣ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቻችን ለብልፅግናችን!....99
31. የቅንጅት ውጤት....99
32. በጎ ፍቃድ ከተግባር ወደ ባህል....99
33. ውብ፣ምቹና ፅዱ ልደታ....99
34. ፅዱ ልደታ....99
35. ቀልጣፋ አገልግሎት እያሰፈነ ያለ ተቋም....99
36. አካባቢ ጥበቃና የልደታ አዲስ ምዕራፍ....99
37. የህዝብ ተሳትፎ ስኬት....99
38. የቁጥጥር ስርዓት ለጤና ደህንነት!....99

## የአዘጋጁ መልዕክት

ውድ የልደታ ፋና መጽሔት አንባቢያን፣የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በሁለንተናዊ የለውጥ ጉዞ ውስጥ ይገኛል። አስተዳደሩ ያስመዘገበውን የለውጥ ጉዞና ስኬቶች ለእናንተ ለማድረስም ይህ መጽሄት ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ መጽሔት የተከናወኑ ሥራዎችን ከማስተዋወቅ ባሻገር የለውጥ ጉዞአችንን የሚያንጸባርቅ፣ የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳይ እና የወደፊት አቅጣጫችንን የሚያመላክት ነው።

በከተማችን እየተካሄደ ያለው የልማት እንቅስቃሴ የነዋሪዎችን የኑሮ ጥራት ለማሻሻል፣ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የከተማ አስተዳደር ለመገንባት እና ለሁሉም የሚጠቅም አካታች ልማት ለማረጋገጥ ያለመ ነው። በዚህም ረገድ በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በአካባቢ ፅዳትና ውበት፣ በሥራ እድል ፈጠራ፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ እና በዲጂታል አስተዳደር ዘርፎች አበረታች ሥራዎች ተከናውነዋል።

መልካም አስተዳደር ለሁሉም የልማት ጥረቶቻችን ዋና መሠረት ነው። ተጠያቂነት፣ ግልጽነት፣ ፍትሃዊነት እና ለሕዝብ ቅርብ የሆነ አገልግሎት በማረጋገጥ የሕዝባችንን እምነት ለማጠናከር በቁርጠኝነት እየሠራን እንገኛለን። የተገኙ ውጤቶችም የለውጥ ሂደቱ በትክክለኛ አቅጣጫ እየተጓዘ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

ሆኖም ለውጥ የማያቋርጥ ጉዞ እንጂ የሚቆምበት መዳረሻ አይደለም። ስለዚህ የተጀመሩ ሥራዎችን በማጠናከር፣ አዳዲስ እድሎችን በመጠቀም እና የሕዝብ ተሳትፎን ይበልጥ በማጎልበት ዘላቂና ተጨባጭ ውጤቶችን ለማስመዝገብ እንተጋለን።

የዛሬው ስኬት የሕዝባችን፣ የሠራተኞቻችን፣ የአመራሮቻችን እና የሁሉም ባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረት ውጤት ነው። ስለዚህ የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ በጋራ በማስቀጠል የበለጠ የተሻለ፣ የበለጸገች እና ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ልደታ ለመገንባት ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ የዝግጅት ክፍላችን መልዕክት ነው፡፡

መልካም ንባብ!



**ወ/ሮ ሲፈን ባዩ**
**የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ**

ክቡራን የልደታ ክ/ከተማ ነዋሪዎች፣ የልማት አጋሮቻችን፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ምሁራን፣ ነጋዴዎች፣ ሰራተኞችና ውድ አንባቢዎች፤

በመጀመሪያ በልደታ ክ/ከተማ የተከናወኑ የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የማህበራዊ እና የትውልድ ግንባታ ስራዎችን በሚያንፀባርቀው በዚህ የመጽሄት ዕትም ከእናንተ ጋር በመገናኘታችን ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል። ይህ መጽሄት የመረጃ ምንጭ ብቻ ሳይሆን በክ/ከተማችን እየተካሄዱ ያሉ የለውጥ ጉዞዎችን የሚያሳይ፣ ህዝብና መንግስትን በመረጃ የሚያስተሳስር እና የጋራ ኃላፊነትን የሚያጎለብት የመግባቢያ መድረክ ነው።

ልደታ ክ/ከተማ በታሪካዊ ዳራዋ፣ በህዝቦቿ ብዝሃነት፣ በንግድና በማህበራዊ እንቅስቃሴዎቿ የምትታወቅ ክ/ከተማ ናት። በዚህ ታሪካዊ እና ህዝባዊ መሰረት ላይ ተመስርተን የተሻለ ከተማ ለመገንባት በብርቱ ቁርጠኝነት እየሰራን እንገኛለን። በየዘርፉ የተመዘገቡ ውጤቶችም የዚህ ጥረት ማሳያ ናቸው።

በመሰረተ ልማት ዘርፍ የመንገድ ግንባታና ጥገና፣ የፍሳሽ መስመሮች ማሻሻያ፣ የመብራት ዝርጋታ፣ የአካባቢ ውበትና ጽዳት ስራዎች በሰፊው ተከናውነዋል። ከዚህ ባሻገር ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ የጤና፣ የትምህርትና የህፃናት ማቆያ ተቋማት በ24/7 የስራ ባህል ተገንብተው ወደ አገልግሎት እየገቡ ይገኛሉ። እነዚህ ፕሮጀክቶች ለህዝባችን የተሻለ የኑሮ ሁኔታ ለመፍጠር ከሚደረጉ ጥረቶች መካከል ዋናዎቹ ናቸው።

በኢኮኖሚ ዘርፍ ወጣቶችና ሴቶችን ማዕከል ያደረጉ የስራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራሞች፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ፣ የገበያ ትስስር ማመቻቸት እና የክህሎት ስልጠናዎች በተጠናከረ ሁኔታ እየተሰጡ ነው። ይህም የነዋሪዎችን የኢኮኖሚ ተሳትፎ ለማሳደግና የኑሮ ጫናን ለማቅለል አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል።

በትውልድ ግንባታ ዘርፍ ደግሞ ወጣቱ ትውልድ ከሀገር ፍቅር፣ ከሥነ-ምግባር፣ ከትምህርትና ከሥራ ባህል ጋር ተሳስሮ እንዲያድግ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተግባራዊ እየሆኑ ነው። የህፃናት ማቆያዎች፣ የወጣቶች ማዕከላት፣ የስፖርትና የባህል መድረኮች ትውልዱን በአዎንታዊ እሴቶች ለመቅረፅ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ነው።



## ወ/ሮ ልዕልቲ ግደይ

### የልደታ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ

### የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት

በዘመናዊ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ልማት ማለት የሚታይ ግንባታ ብቻ ሳይሆን የሰው ሕይወትን የሚያሻሽል፣ የኢኮኖሚ አቅምን የሚያጠናክር፣ ማህበራዊ ፍትሕን የሚያሰፋ እና የህዝብን እምነት የሚያጎለብት ሁሉን አቀፍ ለውጥ ነው።

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በዚህ እውነት ላይ ተመስርቶ “በአዲስ ዕይታ የልደታ ከፍታ” በሚል መሪ ቃል የልማት ፣የኢንሼቲቭ እና የመልካም አስተዳደር ጉዞውን በተጨባጭ ውጤቶች እያረጋገጠ ይገኛል።

ክፍለ ከተማው በኢንሼቲቭ ስራዎች፣ በመንግስት ፕሮጀክቶች፣በማህበራዊ መሠረተ ልማቶች እና በሰው ተኮር አገልግሎቶች ላይ ያሳየው እንቅስቃሴ የነዋሪዎችን ኑሮ በተጨባጭ ለውጧል።ይህም ልማት በህዝብ ተሳትፎ፣ በእቅድ እና በጠንካራ አመራር ሲታገዝ ከተማዊ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል አስመስክሯል።

የኢንሼቲቭ ስራዎችን በተሻለ መንገድ ለማስፈፀም ከሌሎች ክፍለ ከተሞች ጋር የተደረገው የልምድ ልውውጥ ትልቅ ግብዓት አበርክቷል። በዚህም የተሻሉ የአሰራር ልምዶች ተወስደው ወደ ተግባር ተቀይረዋል። በተጨማሪም የቃል ኪዳን ስምምነቶች በመፈራረም የተጀመሩ ስራዎች የህዝብ ፍላጎትን ምላሽ በሚሰጥ መልኩ ተፈፃሚ ሆነዋል።

በዚህ ሂደት የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች ተከናውነው ለበርካታ ዜጎች የመኖሪያ ችግርን ለማቃለል አስችለዋል። እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያዎች በመገንባታቸው ወጣቶች ጊዜያቸውን በጤናማ መንገድ እንዲያሳልፉ እና የአካል ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ አግዘዋል።

የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት የህዝብ መረጃ ፍላጎትን በአግባቡ ለማሟላት እና ትክክለኛ፣ ወቅታዊና ተደራሽ መረጃ ለማድረስ በተለያዩ የመገናኛ አማራጮች እየሰራ ይገኛል። በተለይም የህዝብ ቅሬታዎችንና ጥያቄዎችን በቅርበት በመከታተል ለተገቢ መፍትሄ የሚያበቃ የመረጃ ስርጭትና የግንኙነት ስራ እየተከናወነ ነው። መንግስትና ህዝብ በግልፅነት እንዲግባቡ ማድረግ የተቋማችን ዋና ተልዕኮ ነው።

ውድ የልደታ ክ/ከተማ ነዋሪዎች፤ እየተመዘገቡ ያሉ ውጤቶች የአንድ ተቋም ወይም የጥቂት ሰዎች ጥረት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም የጋራ ተሳትፎ፣ ድጋፍና ትብብር ውጤት ናቸው። ስለሆነም የጀመርነውን የልማት ጉዞ በአንድነት በማስቀጠል ለልጆቻችን የተሻለች ልደታን እናወርሳለን።

በመጨረሻም ለክ/ከተማችን ልማት በቀንና በሌሊት እየሰሩ ላሉ አመራሮች፣ ሰራተኞች፣ የፀጥታ አካላት፣ የልማት አጋሮችና ለመላው ህዝባችን ከልብ እናመሰግናለን። ወደፊትም በአንድነት፣ በቅንነትና በጠንካራ ትብብር በሁሉም ዘርፎች የተሻለ ውጤት እናስመዘግባለን።





**ጂ+4 መኖሪያ ቤትና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች**

የህፃናት ማቆያዎችና የመጫወቻ ስፍራዎች መገንባታቸው ለቤተሰቦች ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፤ በተለይም ሴቶች ወደ ሥራ ዓለም በነፃነት እንዲሳተፉ ድጋፍ አድርጓል።



**የህፃናት ማቆያዎችና የመጫወቻ ስፍራዎች**

የመንገድ ግንባታዎች የትራንስፖርት ችግሮችን በመቀነስ ንግድና እንቅስቃሴን አቀላጥፈዋል።የካፌና ሱቅ ግንባታዎች ደግሞ ለወጣቶችና ለአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ እድል በመፍጠር የገቢ ምንጭ ሆነዋል።

ለበርካታ ዓመታት ህዝብ እንዲሆንለት ሲፈልግ የነበሩ ነገር ግን ትኩረት የተነፈጋቸው ልማቶችን እውን በማድረግ የማህበረሰቡን የመልማት ጥያቄ በአጠረ ጊዜ መፍታት ተችለዋል፡፡

በዚህ ረገድ የወረዳ 5 ጤና ጣቢያ ግንባታ ለነዋሪዎች ቀልጣፋና ተደራሽ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ አስችሏል። በተለይ እናቶችና ህፃናት የሚያገኙትን የጤና አገልግሎት በእጅጉ አሻሽሏል።



**የጤና ጣቢያ ግንባታ**

የፍሬ ህይወትና የቅዱስ ጊዮርጊስ ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ግንባታ ደግሞ ህፃናት ከልጅነታቸው ጀምሮ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ መሠረት ጥሏል። ይህም የትምህርት ተደራሽነትን ከማስፋት ባሻገር ለወደፊቱ ብቁ ትውልድ መፍጠር ያለውን አስተዋፅኦ ያሳያል።



**የትምህርት ቤቶች ግንባታ**

የወረዳ 1 ድልድይ ግንባታ በማህበረሰቡ መካከል የነበረውን የመንቀሳቀስ ችግር በመቅረፍ ተደራሽነትን አሻሽሏል። ይህም ንግድ፣ ትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶች በቀላሉ እንዲደረሱ አስችሏል።



**የሳህሉ ጫካ ድልድይ ግንባታ**

የኢኒሼቲቭ ስራን በተመለከተ :-የከተማ ግብርና ፕሮጀክት አፈፃፀም ምርትን ከማምረት እስከ ገበያ ያደረሰ ልማት የከተማ ግብርና ፕሮጀክቶች በልደታ ክፍለ ከተማ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር ለስራ እድል ፈጠራና ለገቢ ማሳደግ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የከተማ ግብርና ውጤቶች ማምረቻና መሸጫ ሱቆች በመገንባታቸው አምራቾች ምርታቸውን በቀጥታ ወደ ገበያ እንዲያቀርቡ አስችሏል። ይህም የደላላ ተፅዕኖን በመቀነስ አምራቹ ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጓል፤ ሸማቹም በተመጣጣኝ ዋጋ ምርት እንዲያገኝ አስችሏል።





**የከተማ ግብርና ውጤቶች ማምረቻና መሸጫ ሱቆች**

የእንስሳት እርባታ ክላስተር ግንባታ ደግሞ በዘመናዊ መንገድ የእንስሳት ሀብትን ለማልማት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። ይህም የወተት፣ የእንቁላልና የስጋ ምርት እንዲጨምር በማድረግ የምግብ አቅርቦትን አጠናክሯል። በተጨማሪም ለብዙ ወጣቶችና ሴቶች የሥራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን አሳድጎታል።







**የእንስሳት እርባታ ክላስተር ግንባታ**

ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠር የተቋም ውጤታማነትን ለማሳደግ መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ አስተዳደሩ በርካታ ስራዎችን አከናውኗል። የአስተዳደሩ ካፌ ተገንብቶ ለሰራተኞችና ለተገልጋዮች ምቹ የአገልግሎት ሁኔታ ፈጥሯል። የሰራተኞች ጅም ደግሞ የአካል ብቃትን በማሳደግ ጤናማና ንቁ የሥራ ኃይል እንዲፈጠር አግዟል። የሰራተኞች ሱፐርማርኬት በተመጣጣኝ ዋጋ የፍጆታ እቃዎችን በማቅረብ የኑሮ ጫናን አቃልሏል። የህፃናት ማቆያ ደግሞ በተለይ ለሴት ሰራተኞች ትልቅ እፎይታ ፈጥሯል፤ በልጆቻቸው ደህንነት ተረጋግተው በሥራቸው ላይ እንዲያተኩሩ አስችሏል። የደህንነት ካሜራዎች መገጠማቸው ደግሞ የተቋሙን ደህንነት በማጠናከር ግልፅነትና ተጠያቂነትን አሳድገዋል።






**የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ እና የደህንነት ካሜራ**

ሞዴል መንደር ግንባታ ንፅህ፣ ውበትና ማህበራዊ አንድነት የሞዴል መንደር ግንባታ ፕሮጀክት የከተማውን ገፅታ ከመቀየር ባሻገር ማህበረሰቡ በንፅህናና በተቀናጀ አካባቢ እንዲኖር አስችሏል።

በፕሮጀክቱ ውስጥ የተከናወኑ የመንገድ ማሻሻያዎች፣ የአረንጓዴ ልማቶች እና የህዝብ መገልገያ ስፍራዎች ከተማውን ለኑሮና ለኢንቨስትመንት ምቹ አድርገውታል።





**ሞዴል መንደር**

በሰው ተኮር ልማት 69 እናቶችን ከአደጋ ወደ ዘመናዊ ንግድ ማዕከል ልማት ሰውን ካላማከለ ትርጉም አይኖረውም።በዚህ እሳቤ መሠረት በብርድና በፀሀይ ሲንገላቱ የነበሩ 69 እናቶችን ወደ ዘመናዊ የንግድ ሼድ ማሸጋገር መቻሉ ከሰው ተኮር ስራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው።




**ዘመናዊ የንግድ ሱቆች**

በአጠቃላይ በክፍለ ከተማው የተከናወኑ የኢንሼቲቭ ስራዎች፣ የመንግስት ፕሮጀክቶች ፣የመልካም አስተዳደር እና በሰው ተኮር አገልግሎቶች የልደታን የከፍታ ጉዞ ያሳያሉ።

እነዚህ ስራዎች የህዝብን እምነት በማጠናከር፣ የኑሮ ጫናን በማቃለል፣ የሥራ እድል በመፍጠር እና ማህበራዊ ፍትሕን በማስፋት ቀጣይ የልማት ጉዞውን የሚያበረታቱ ናቸው። በጠንካራ አመራር፣ በህዝብ ተሳትፎ እና በጋራ ርብርብ የልደታ ከፍታ ከዛሬው ይልቅ ከፍ ወዳለ ደረጃ እንደሚደርስ ተስፋ ይሰጣል።

## በአዲስ ዕይታ የልደታ ክፍታ



**አቶ ዘመኑ ደሳለኝ**
**የልደታ ክ/ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ**

ከተማችን አዲስ አበባ ስሟን የሚመጥን፣ ዉብ፣ ፅዱ፣ ለመኖርያ የተመቸች እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። ክፍለ ከተማችን ልደታም የከተማዋን እድገትና ብልፅግና የሚመጥን የልማት ስራዎችን በማከናወን የነዋሪዎቿን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ሰፋፊ ስራዎች በማከናወን ላይ ናት። የከተማችንን ሰላምና ፀጥታ አስተማማኝ ከማድረግ አኳያ ህዝባዊ ተሳትፎ ለማጎልበት እና በማጠናከር በፀጥታ ስራ ህዝቡ በበላይነት ተዋናይ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር በርካታ ስራዎችን መስራት ተችሏል።

በሰው ተኮር በሆኑ ስራዎቻችን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖቻችንን መርዳትና መደገፍ ባህል ያደረገች ከተማ መፍጠር ችለናል፤ የበጎ ፈቃድ ስራዎች የህሊና እርካታ የምናገኝበት ከመሆኑ በተጨማሪ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖቻችን ችግራቸው የሚፈታበት ተግባር በመሆኑ የመተባበርና መደጋገፍ ባህልን በማጎልበት በርካታ የበጎ ፈቃድ ስራዎች እየሰራን እንገኛለን።

ነዋሪዎቻችንን የሚመጥን ቀልጣፋ እና ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት የጀመርናቸውን ስራዎች አጠናክረን እንቀጥላለን። የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች ከሌብነት የጸዳ፤ ፈጣን፤ ቀልጣፋና ብቃት ያለው አገልግሎት በመስጠት ሀገራዊ ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል፡ ፡ የአገልግሎት ቅልጥፍናን ለመጨመር በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር ለመዘርጋት የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በብልፅግና ፓርቲ የሚመራው የመደመር መንግሥት “የጉባ ብስራቶች የመደመር መንግሥት ትሩፋቶች” በሚል መሪ ቃል በከተማችን እና ክ/ከተማችን ህዝባዊ የውይይት መድረኮች ማካሄዱ የሚታወስ ነው። ለተከታታይ ሁለት ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ አስራ አንዱም ክ/ከተሞች እና በሁሉም የክልል ዋና ዋና ከተሞች የውይይት መድረኮች ከፍ ያለ የህዝብ ተሳትፎ የታየባቸው ሆነው ተካሂደዋል።

ህዝባዊ የውይይት መድረኮቹ መንትያ ግቦች ያነገቡ ናቸው፤ አንደኛው ግብ ብልፅግና ለህዝብ የገባውን ቃል ህዝብ አስተባብሮና ተጠቃሚ አድርጎ በተግባር የገለጠበትን እውነታ ከህዝቡ ከራሱ አብሮ ለመገምገም ሲሆን፤ ሁለተኛው ግብ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች የሚሰተዋሉ ችግሮችን ከህዝቡ ከራሱ በማዳመጥ መፍትሄ መስጠት ነው። የህዝባዊ ውይይት መድረኩ መሪ ቃል አካል የሆነው አንደኛው ነጥብ 7ቱ የጉባ ብስራቶች ሲሆኑ እነዚህም ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክታችን በድምር በ6 እጥፍ ሚተልቁ የ30 ቢልየን ዶላር ፕሮጀክቶች ናቸው። እነዚህ የማዳበሪያ፣ የነዳጅ ማጣሪያ፣ የጋዝ ኃይል፣ የኒኩሌር ኃይል፣ የቤት ልማት እና የግዙፍ አየር ማረፍያ ግንባታ ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያን በቀጣይ 5 ዓመታት ወደ የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት የሚያደርሱ እና የሀገረ-መንግስት ግንባታ አካል የሆኑ ስትራቴጂክ ፕሮጀክቶች ናቸው።

መንግሥት በነዚህና ሌሎች አያሌ ድሎች ሳይዘናጋና ሳይኩራራ በህዝብ ዘንድ የሚነሱ ችግሮችና ቅሬታዎች በመድረኩ እንዲነሱ አድርጓል። መንግሥት በህዝብ ዘንድ የሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ከህዝቡ አንደበት ለማዳመጥ የሄደበት ርቀት የህዝባዊነቱ እና የአገልጋይነቱ ጥግ ማሳያ መሆናቸው በተሳታፊዎች በደስታ-እምባ ጭምር የታጀበ እውቅናና ምስክርነት ተሰጥቶታል።

ይህ ነባራዊ ሁኔታ በአንዳንድ ባዳዎችና ባንዳዎች በማህበራዊ ሚዲያ ከሚነዙ የሀሰት ወሬዎችና አሉባልታዎች በተቃራኒ ህዝብ ከመንግሥት ጎን ያለ መሆኑ እና የሚያጋጥሙ ችግሮችም ከመንግሥትና ህዝብ የመፍታት አቅም በላይ አለመሆናቸው ከፍተኛ እምነትና ተስፋ እንዳለ ታይቷል።

የመንግሥት ህዝባዊነትና ህዝብን የማዳመጥ ተግባር በተከታታይ ዓመታት የተስተዋለ ቢሆንም በዚህ ጊዜ እየተካሄደ ያለው ህዝባዊ ውይይት ላይ የተለየ ትርጉም ተገኝቶበታል። ይህ የተለየ ትርጉም በዚህ ዓመት ነጻ፣ ፍትሀዊ፣ ተዓማኒና አሳታፊ ሆኖ ለሚካሄደው ሀገራዊ ምርጫ እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንዲሁም ለቀጣይ 5 ዓመታት የብልፅግና የመሪነት ያለው ህዝባዊ ድጋፍና ዝግጁነት ነው። በከተማችን አዲስ አበባ እና በክ/ከተማችን የተከናወኑ የልማት ስራዎች ወጣቶችን በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው። ወጣቶችና ሴቶች በሰው ተኮር፣ በበጎ ፈቃድ፣ ሰላምና ጸጥታ፣ በኮሪደር ልማትና ሌሎች ፕሮጀክቶች ጉልህ ሚና በመጫወት የስራ እድል ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። ወጣቶችን በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ምጣኔ ሃብት ዘርፎች ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ አካታች እድገት ለማምጣት የተጀመረው ተግባር የሚበረታታና ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው።

## "ስራ እድል ፈጠራ ከዳቦ በላይ"

ተቋሙ በክፍለ ከተማ ደረጃ የስራና ክህሎት ጽ/ቤት በሚል በሁለት ዘርፎችና በ8 ቡድኖችና በማደራጀት የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ማጠንጠኛ የሆነውን የስራ እድል መፍጠርንና የስራ ስምሪትን በማሳለጥ ላይ ይገኛል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትንና የሙያ ደህንነትን ጤናማ በማድረግ፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ለማረጋገጥ እና ለኢንዱስትሪው እድገት መሰረት የሚጥሉ ኢንተርፕራይዞችን የማልማትና የኢንተርፕራይዞች ሽግግር ስራን በማፋጠን በምርትና ምርታማነት ላይ እምርታዊ ለውጥ የማምጣት ተልዕኮን ለማሳካት እንዲያስችለው ነው፡፡

በባለፉት የለውጥ ዓመታት ትግበራ የተመዘገቡ ውጤቶችን እንዲሁም የታዩ ክፍተቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ የስራ ገበያውን መሰረት በማድረግ የሰው ኃይል የማሰልጠንና የማዘጋጀት፣ የከተማዋን ነዋሪ የስራ አጥነት ችግር የሚቀርፍ ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡ የስራ ስምሪትን በማሳለጥና የአሰሪ ሰራተኛ ግንኙነትን መልካም በማድረግ የኢንዱስትሪ ሰላም ማስፈን፣ የኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችል ቅንጅታዊ ስራዎች አተገባበርን እንዲሁም ለዘርፉ የተሰጠውን ተልእኮ ዋና ዋና ተግባራት አጠቃላይ አፈጻጸም ከክ/ከተማው ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ እና የጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ አዳሙ በዛብህ ጋር የመጽሔት ክፍላችን ቆይታ አድርጋለች፡፡ መልካም ንባብ!

**አቶ አዳሙ በዛብህ**
**የክ/ከተማው ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚና**
**የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** በበጀት አመቱ ለማሳካት የተያዙት የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ያሉበት ደረጃ ቢያብራሩልን?

**አቶ አዳሙ በዛብህ፡-** ተቋሙ የሐብት ክፍፍል ፍትሃዊነት የሚረጋገጥበት፣ የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ንረት የሚረጋጋበት፣ የአሰሪ እና ሰራተኛ ግንኙነት ጤናማ የሚሆንበትና የኢንዱስትሪ ሰላምና የሰራተኞች የሙያ ደህንነት የሚረጋገጥበት እንዲሁም የኢንተርፕራይዞችን የማምረት አቅም እና የምርትና አገልግሎት ጥራት በማሳደግ በብቃት፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የተለያዩ መንግስታዊ ድጋፎችን በማድረግ ዜጎች በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ የሚደረግበት ከመሆኑም ባሻገር ምርታቸውን ለሀገር ውስጥና የውጪ ገበያ በማቅረብ የገበያን ክፍተት በመሙላትና የውጭ ምንዛሬን በማስገኘት እንዲሁም የሚጠበቅባቸውን ግብር በመክፈል ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖያዊ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ከቅድመ ስራ እድል ፈጠራ እና ስራ እድል ፈጠራ አኳያ በዚህ በጀት አመት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም **25,903** ስራ ፈላጊዎችን በመመዝገብ እና በ**1054** የግል እና የመንግስት ተቋማት እንዲሁም የተለያዩ ኢንተርፕራዞችና ኢንዱስትሪዎች ከ**26,652** በላይ ክፍት መደቦችንና ጸጋዎችን በመለየት በከተማ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ እና ንግድና አገልግሎት ዘርፎች ለ**24,556** የክ/ከተማችን ነዋሪ ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ **13,292** ሴቶች ሲሆኑ **11,473** ወጣቶች ከመሆናቸውም ባሻገር የተፈጠረው የስራ እድል ቋሚ የስራ እድል ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን **3405** ስራ ፈላጊዎችን በ**829** ኢንተርፕራይዞች ማደራጀት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የወጣቶች እና የሴቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተከናወኑ ተግባራት ምንድናቸው?

**አቶ አዳሙ በዛብህ፡-** በክ/ከተማችን በዘርፉ ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል ዋነኛው የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ድህነትን መቀነስ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለወጣቶችንና ሴቶች ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር የክፍለ ከተማችንን ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ የተለያዩ የቅድመ ስራ እድል ፈጠራ ስራዎችን በማከናወን ለስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር የመንግስት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶችና ነባር ኢንተርፕራይዞች ሊፈጥሩ የሚችሉ ጸጋዎችንና ክፍት የስራ መደቦችን በጥናት በመለየት ለክ/ከተማው ነዋሪዎች እና ስራ ፈላጊዎች በዘርፉ ተግባራት ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ወጣቶችንና ሴቶችን በስራ ፈላጊነት እንዲመዘገቡ በማድረግ ስራ ፈላጊዎች ያላቸውን እውቀት እና ትኩስ ጉልበት ተጠቅመው እንዲሁም እንደ ከተማ ያሉንን ውሱን ሃብቶች በፍትሃዊነት በመደገፍና የስራ እድል በመፍጠር አመርቂ ውጤት ማስመዘገብ ሌላኛው ግባችን ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ድህነትና ተረጂነት ቅነሳ መርሃ ግብር ለማሳካት ተቋሙ ምን አከናውኗል?

**አቶ አዳሙ በዛብህ፡-**በከተማ ምግብ ዋስትና እና ስራ ፕሮጀክት በክ/ከታማችን ዝቅተኛ ነዋሪዎችን የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ በተጨማሪ ፋይናንስ ተጠቃሚ የነበሩ የ**607** አባወራ እማወራ ተወካዮች **1,807** የቤተሰብ አባላት በአንድ በኩል በአካባቢ ልማት ስራ አካባቢያቸውን እያጸዱ እና እያለሙ በሌላ በኩል ደግሞ ገቢ እያገኙ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን በ3 ዓመት ቆይታቸው የተፈቀደላቸው ግራንት ተለቀላቸው ቁጠባቸውን በመጨመር እንዲሸጋገሩ እና በመረጡትና በሰለጠኑበት ዘርፍ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በሌላ በኩል በመንግስት ማችንግ ፈንድ በተመደበ በጀት በ**3,382** አባወራ እማወራዎች ስር **10,931** የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት ስራ አንጻር በ3ኛ ዙር ብቃት የወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት ተጠቃሚ በሆኑ 4 ወረዳዎች ልምምዳቸውን ያጠናቀቁ **775** ወጣቶችን ሙሉ በሙሉ ተቀጣሪ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ አፈፃፀም እንዴት እየተከናወነ እንደሆነ ቢያብራሩልን?

**አቶ አዳሙ በዛብህ፡-** በመንግስት በጀት በሚካሄድ የወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት በሁለት ወረዳዎች **300** ወጣቶችን በማለማመድ

ለማስተሳሰር በተያዘው እቅድ መሰረት ምዝገባና ምልመላ ተጠናቆ **375** ወጣቶች የህይወት ክህሎት ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ ከእነዚህ ውስጥ **300** ወጣቶች ከኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር የስራ ላይ ልምምድ እያደረጉ ይገኛሉ። በተያያዘ ለኢንተርፕራዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሚሰጡ ድጋፎች መካከል የቁጠባ፣ ብድርና የመሳሪያ ሊዝ ብድር ማመቻቸት፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት፣ የንግድ ልማት አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ፣ የእድገት ደረጃ ሽግግር ድጋፍ፣ የመስሪያ ቦታ አቅርቦት፣ የምርት እና ምርታማነት ልኬት እና መሰል ድጋፎች ይገኙበታል። ከዚህ አኳያ ለኢንቨስትመንት መሰረት የሆነው ቁጠባ በመሆኑ የዘርፉ አንቀሳቃሾች በቁጠባ ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ ጨብጠው ወደ ቁጠባ እንዲገቡ ሰፊ ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን!
**አቶ አዳሙ በዛብህ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## የህዝብ ድምፅና የተጠያቂነት ማረጋገጫ ተቋም

የአካባቢ ራስ አስተዳደሮች ውጤታማ እና ለህዝብ ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርጉት የምክር ቤቶች ሚና ከፍተኛ ነው። ምክር ቤቶች በሕዝብ የተመረጡ ተወካዮች በመሆናቸው የሕዝቡን ፍላጎት ለአስፈጻሚ አካላት በማቅረብ እና ተፈጻሚነታቸውን በመከታተል፣ የአስፈፃሚ አካላትን ሥራ በመቆጣጠር እና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ዋነኛ ምሰሶዎች ናቸው።

በተለይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከህዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር በቀጥታ የተገናኙ በመሆናቸው የምክር ቤቶች የቁጥጥርና ክትትል ሥራ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

የልደታ ፋና መጽሔት በዚህ እትሙ የልደታ ክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤን በማነጋገር ምክር ቤቱ በአስፈፃሚ አካላት ላይ ስለሚያደርገው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ፣ የህዝብን ሉዓላዊ ስልጣን ለማረጋገጥ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት፣ ስለተገኙ ውጤቶች እና ስለወደፊት አቅጣጫዎች ቆይታ አድርጓል።



**አቶ ዘሪሁን ሽፈርዳ**
**የልደታ ክ/ከተማ ምክር ቤት አፈ- ጉባኤ**

**ልደታ ፋና፡-** ምክር ቤቱ ለአስፈፃሚ አካላት የሚያደርገው የቁጥጥርና ክትትል ሥራ አለ? ካለስ ምን ዓይነት ናቸው?
**አቶ ዘሪሁን፡-** በእርግጥ አለ። ከምክር ቤቱ ዋና ዋና ተግባራት አንዱ አስፈፃሚ አካላት በሕግ፣ በፖሊሲ እና በተያዙ ዕቅዶች መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል ነው። ይህም በመደበኛ የሥራ ሪፖርት ግምገማ፣ በመስክ ምልከታ፣ በቋሚ ኮሚቴዎች ክትትል፣ በፕሮጀክት ጉብኝት እና በልዩ ጥናቶች ይከናወናል። በተለይ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በበጀት አጠቃቀም፣ በገቢ አሰባሰብ እና በልማት ፕሮጀክቶች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

**ልደታ ፋና፡-** ምክር ቤቱ የህዝብ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት ሥራዎችን ሠርቷል?
**አቶ ዘሪሁን፡-** ምክር ቤቱ የሕዝብ ወኪል በመሆኑ የህዝቡን ድምፅ ለአስፈፃሚ አካላት በማቅረብ እና ምላሽ እንዲያገኝ በማስቻል የህዝብ ሉዓላዊነትን ያረጋግጣል። በየወቅቱ ከህዝብ ጋር የውይይት መድረኮችን በማካሄድ፣ የህዝብ ጥያቄዎችን በመሰብሰብ፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ የህዝብ ተሳትፎን በማሳደግ እና በተለያዩ አካባቢዎች የተነሱ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ በማድረግ የሕዝብ ሥልጣን ባለቤትነት በተግባር እንዲረጋገጥ እየሰራ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** በተደረጉ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ምን ውጤቶች ተገኝተዋል?
**አቶ ዘሪሁን፡-** የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ተጨባጭ ውጤቶችን አስገኝተዋል። የአገልግሎት ፍጥነትና ጥራት ተሻሽሏል፣ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ተፋጥኗል፣ የበጀት አጠቃቀም ግልፅነት ጨምሯል፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀንሱ ተደርጓል። ከዚህ ባሻገር የተቋማት ተጠያቂነት እና ለህዝብ የመመለስ ባህል ተጠናክሯል።

**ልደታ ፋና፡-** አስፈፃሚ አካላት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ሳይወጡ ሲቀሩ የምክር ቤቱ ሚና ምንድን ነው?
**አቶ ዘሪሁን፡-** በመጀመሪያ የችግሩን ምክንያት በጥልቀት እናጠናለን። ከዚያም የማሻሻያ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተቋማቱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክሉ እናደርጋለን። የሚፈለገው ለውጥ ካልታየ በሕግ መሰረት ተገቢው ተጠያቂነት እንዲወሰድ እናደርጋለን።

**ልደታ ፋና፡-** አስፈፃሚ አካላትንና ማህበረሰቡን ፊት ለፊት አገናኝታችሁ የምታወያዩበት ስርዓት አለ?
**አቶ ዘሪሁን፡-** አዎን፣ በየደረጃው የተጠያቂነት መድረኮች፣ የሕዝብ ውይይቶች፣ ክፍት መድረኮች እና የህዝብ ጥያቄና ምላሽ ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ። ይህም ህዝቡ ጥያቄውን በቀጥታ እንዲያቀርብ እና አስፈፃሚ አካላት በቀጥታ ምላሽ እንዲሰጡ እድል ይፈጥራል።

**ልደታ ፋና፡-** ማህበረሰቡ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዴት ታስተናግዳላችሁ?
**አቶ ዘሪሁን፡-** የህዝብ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች በተለያዩ መንገዶች ይሰበሰባሉ። ከዚያም በሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎችና አስፈፃሚ አካላት ተመርምረው መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል። የተሰጡ መፍትሄዎች በተግባር መተግበራቸውንም በቀጣይነት እንከታተላለን።

**ልደታ ፋና፡-** ለልደታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ዘሪሁን፡-** የክፍለ ከተማችን እድገት የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው። ማህበረሰቡ በልማት ሥራዎች፣ በሰላም ግንባታ እና በመልካም አስተዳደር ማጠናከር ሂደቶች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፍ እጠይቃለሁ። ምክር ቤቱም የህዝብ ድምፅ ሆኖ በታማኝነት እና በተጠያቂነት መስራቱን ይቀጥላል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ምክር ቤት በአስፈፃሚ አካላት ላይ የሚያደርገው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የተሻለ አገልግሎት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ መሆኑን ከቆይታችን ተረድተናል። እንዲሁም ምክር ቤቱ የህዝብን ሉዓላዊ ሥልጣን በተግባር ለማረጋገጥ፣ የህዝብ ተሳትፎን ለማጠናከር እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ ነው።

ለዘላቂ ልማትና ለተሻለ አገልግሎት የህዝብ፣ የምክር ቤቱ እና የአስፈፃሚ አካላት የጋራ ትብብር ወሳኝ በመሆኑ ይህ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይጠበቃል።

## በለዉጥ ምህዋር ላይ ያለ ተቋም

ለልደታ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት በበጀት አመቱ የተከናወኑ ስራዎች በተለይም በሴክተሩ የመጡ ለዉጦች፣ወጪ ቆጣቢና እንግልትን የሚያስቀሩ ቴክኖሎጂ ትግበራ፣በተለይም አዲሱን የውል አሰራርና የመልካም አስተዳደር የመሳሰሉ ጉዳዮች ተዳሰዋል ለነዋሪዎቻችን ወቅታዊና ጠቃሚ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ እንታትራለን:: ከእዚሁ ጉዳይ ጋር ልደታ ፋና ከልደታ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ገመቹ ጌታቸዉ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርጓል በንባብ ተከታተሉን!

**ልደታ ፋና፡-** በ2018 በጀት ዓመቱ የክፍለ ከተማው ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ካቀዳቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል እስካሁን ባለው ጊዜ የተመዘገቡት ጉልህ ስኬቶች ምንድናቸው?

**አቶ ገመቹ፡-** “በበጀት ዓመቱ የቤቶች አስተዳደርን በማዘመን ረገድ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበናል። በዋናነትም የ**13,076** ተከራዮችን ውል በሲስተም በማደስና ከቤት ኪራይ እንዲሁም ከተለያዩ አገልግሎቶች **89,800,345** ብር ገቢ መሰብሰብ ችለናል። የመረጃ አያያዛችንን ለማዘመን የ**120** ቤቶችን የካርታ ስራ መረጃ ለሚመለከተው አካል ያስተላለፍን ሲሆን፣ በፋይል ቤቶች ላይም የክትትል ካሜራ በመግጠም ደህንነታቸውን አረጋግጠናል።

በህግ ረገድ የ**75** ቤቶችን መረጃ ለአቃቤ ህግ በማደራጀት የ**35**ቱን ውሳኔ ማግኘት የቻልን ሲሆን፣ በአጠቃላይ የምናስተዳድራቸውን ቤቶች መረጃ በአዲስ መልክ አደራጅተናል። በተጨማሪም **206** በህገ-ወጥ መንገድ ተይዘው የነበሩ ቤቶችን በማስለቀቅ፣ **196**ቱን ለልማት ተነሺዎችና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ማስተላለፍ ችለናል።”



**አቶ ገመቹ ጌታቸው**
**የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**በበጀት ዓመቱ ተግባራዊ መሆን የጀመረው አዲሱ የውል አሰራር ቀደም ሲል ከነበረው አሰራር በምን ይለያል? ለነዋሪውስ የሚሰጠው ፋይዳ ምንድነው?

**አቶ ገመቹ፡-**“የመረጃ አያያዛችንን ከነበረበት ባህላዊ አሰራር ወደ ዘመናዊ ኦንላይን ሲስተም መቀየራችን በስራችን ላይ ትልቅ መሻሻል አምጥቷል። ይህ በሲስተም የታገዘ የውል አሰራር በተለይ ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን በመቀነስ ረገድ የሚጠቀስ ስኬት ነው። ተገልጋዮች ቀደም ሲል ውል ተዋውለው ክፍያ ለመፈጸም ወደ ገቢዎች መሄድ ነበረባቸው፤ አሁን ግን ሳይንገላቱ ባሉበት ሆነው በቴሌ ብር ክፍያቸውን ማጠናቀቅ በመቻላቸው የተገልጋይ እርካታ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። በአጠቃላይ ይህ ሲስተም የመንግስትን ንብረት ከህገ-ወጥ ተግባራት ለመከላከል ከመርዳቱም በላይ፣ የቤቶችን መረጃ በቀላሉ ፈልጎ ለማግኘትና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት አስችሎናል።”





**የቤት ውል ሲዋዋሉ የሚሳይ**

**ልደታ ፋና፡-** አዲሱ የውል አሰራር በቤት ልማትና አስተዳደር ዘርፍ ይስተዋሉ የነበሩ ህገ-ወጥ ተግባራትንና የተንዛዙ ሂደቶችን በመቀነስ ረገድ ምን ሚና እየተጫወተ ይገኛል?

**አቶ ገመቹ፡-** የመንግስት ቤቶች ሲስተም ላይ መግባቱ ቀድሞ የነበረውን በህገወጥ መንገድ የሚጠፉ የቤቶች መረጃዎች በጥንቃቄ እና ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እንዲያዙ ማድረግ መቻሉ ህገወጥ ድርጊት እንዲቀንስ ትልቅ ሚና መጫወት ችሏል፡፡

- ሌብነት እና ብልሹ አሰራር መቀነስ መቻሉ
- ተገልጋይ ቀድሞ ላይ መጥቶ አገልግሎት ለመውሰድ የሚፈጀው ጊዜ መቆጠቡ ወይም መቀነሱ

**ልደታ ፋና፡-** ነዋሪዎች አዲሱን የውል አሰራር በሚገባ ተረድተው እንዲተገብሩት በማድረግ ረገድ በክፍለ ከተማው የተከናወኑ የንቃተ-ህሊና ማሳደጊያ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ ገመቹ፡-** በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በመጠቀም የማስተባበር እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል ተገልጋዮች በአዲሱ ሲስተም ለመገልገል ሲመጡ ቀድሞ ስለሲስተሙ ማወቅ ስለነበረባቸው በተለያዩ የሚዲያ መንገዶች ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን እንዚህ የሚዲያ ዘዴዎች ፍላየር ፤በየወረዳው ማስታወቂያ መለጠፍ፤በተቋሙ ፌስ ቡክ ፤በተቋሙ ዌብሳይ እና በየወረዳው ቅስቀሳ በማድረግ ግንዛቤ መፍጠር መቻሉ፡፡

ተገልጋዮችን በየመስኮቱ ወረፋ መያዣ ዲፕሌ በማዘጋጀት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታ በማስተዋወቅ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ማግኘት ችለዋል

- ተገልጋዮች በአከፋፈል ዙሪያ የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታት ባለሙያ በመመደብ ቴሌ ብር እንዲከፈትላቸው ፤ሚስጥር ቁራቸው ሲያግራቸው ቴሌ ሳይሄዱ በቢሮ ባለሙያ በማስተካከል አገልግሎቱ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ እና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ
- ለሌላ አላማ የሚፈጠሩ መድረኮችን ጭምር በመጠቀም ግንዛቤ በመፍጠር



**የህዝብ ውይይት/ ግንዛቤ / ሲሰጥ**

**ልደታ ፋና፡-** በቤቶች አስተዳደር ዘርፍ ከነዋሪዎች በተደጋጋሚ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎች ምንድናቸው? እነዚህን ለመፍታት ምን ተጨባጭ እርምጃዎች ተወስደዋል?

**አቶ ገመቹ፡-** በቤቶች በተደጋጋሚ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ዋነኛው የቤት ማስተላለፈ ላይ የሚነሱ ችግር እና የቤት ይቀየርልኝ ጥያቄዎች ዋነኞቹ ሲሆኑ

በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ችግር ለደረሰባቸውና የቤት ይቀየርልኝ ጥያቄ ላቀረቡ 45 ተገልጋዮች ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 200 ለሆኑ ህጋዊ ተከራዮች ምትክ ቤት መስጠት መቻሉ

ፍሃዊ የቤት ማስተላለፍ ያለመኖር ችግር መፍታት በተመለከተ ወረፋ ላይ ከሚገኙ ከተቋሙ የተፃፈላቸው፤በካቢኔ ተወስኖላቸው ወረፋ እየጠበቁ የሚገኙ የቤት ችግረኞችን መድረክ በመፍጠር መመሪያው ቤት አሰጣጡ ላይ ምን ይላል የሚለውን እና የቤት አቅርቦት እንደ ክ/ከተማ መኖሩን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ግንዛቤ በመፍጠር ሁሉም የቤት ችግኛ ወረፋውን ግልፀኝነት በተቋሙ ቀርቦ ማየት እንደሚችል በማሳወቅ ለውጦች ማየት መቻሉ

**ልደታ ፋና፡-** የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ የሚነሳውን በሕገ-ወጥ የተያዙ ቤቶችና ማስፋፋትን ከመከላከል አኳያ በበጀት ዓመቱ ምን ዓይነት የክትትልና እርምጃ ተወስዷል ስርአት ተዘርግቷል? የተገኘውስ ውጤት ምንድነው?

**አቶ ገመቹ፡-** በ2018 ዓ.ም 206 በህገወጥ የተያዙ ቤቶችን በማስለቀቅ እና 195 ቤቶች ለልማት ተነሺዎች ፤ወረፋ ላይ ላሉ የቤት ችግረኞች ማስተላለፍ ችለናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በክፍለ ከተማው ስር የሚገኙ የቀበሌ ቤቶችንም ሆነ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ከማስተላለፍና ከውል እድሳት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት የተወሰዱ ተጨባጭ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

**አቶ ገመቹ፡-** ቤቶችን በእጣ የማስተላለፍ ሂደት መከተል ፍትሃዊና ተደራሽ እያደረግን እንገኛለን እንዲሁም ቤቶችን በመለየት በእቅድ ለአቅመ ደካማ እና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ ቤቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊነቱንም በመከታተል ቅሬታዎችንም አግባበብ ባለዉ መልኩ ለመፍታት ችለናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በዘርፉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንዲሁም የሙስና ተጋላጭነትን ለመቀነስ በየደረጃው ያለውን የአመራርና የፈፃሚ መዋቅር እንዴት እየተከታተላችሁት ነው?

**አቶ ገመቹ፡-** በግልፅ፤ቀልጣፋ እና ፈጣን አገልግሎት እንዲሰጥ ለባለሙያ ተገቢውን ድጋ እና ክትትል በማድረግ አጫጭር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት የአቅም ግንባታ እና የአመለካት ለውጥ ላይ በትኩረት መስራት ተችሏል

ስራዎች በቴክኖሎጂ በመታገዝ እንዲሰሩ በማድረግ የነበረውን እንግልት እና ምልልስ በመቀነስ የሌብነት ተጋላጭነትን በመቀነስ

ልደታ ፋና፡- በ2018 በጀት ዓመት በመልካም አስተዳደር ስራዎች ውጤታማ መሆናቸውን በምን መለኪያ ማረጋገጥ ይቻላል?

አቶ ገመቹ፡-በበአጭር ጊዜ ውስጥ 206 ህገወጥ ቤቶችን በማስለቀቅ 196 ነዋሪዎች በማስተላለፍ 2500 ሰው በላይ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻም በቀሪው የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነዋሪዎች ከቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ምን አዳዲስ ስራዎችንና ማሻሻያዎችን ይጠብቁ?

**አቶ ገመቹ፡-** በሁሉም አገልግሎት በቴክኖሎጂ የሚሰጡ በመሆናቸው ለዘመናዊ አሰራር እንዲዘጋጁቀልጣፋ ፈጣን እና ግልፅ የሆነ አገልግሎት መሰጠት፣በአጭር ሰዓታት ውስጥ ፈጣን አገልግሎት መስጠት፣ምቹ እና ወጪ ቆጣቢየሆኑ ቤቶችን ለተገልጋዮች በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የተሻለ የአኗኗር ሂደት እንዲኖር ማድረግ፣የተሻለ ለተገልጋይ እና ለአገልጋይ ምቹ የሆነ ተቋም መገንባት የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎቻችን ናቸዉ፡፡

## ከቤተሰብ ፍጆታ እስከ ገበያ ማረጋገት

መንግሥት ለአርሶ አደሮችና ለከተማ ግብርና የሰጠው ትኩረት ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ ለገበያ የሚቀርብ ምርት እንዲመረት አስችሏል፡፡ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ያስቀመጡትን አቅጣጫ ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ግብርና ዘርፍ በተደራጀ መልኩ ተቋቁሞ በከተማው ውስጥ ከፍተኛ የአመለካከትና የተግባር ለውጥ አምጥቷል፡፡

**"በሌማት ትሩፋት"** መርሃ ግብር አንድም ክፍት ቦታ ጾም ማደር የለበትም በሚል አቅጣጫ የተጀመሩ ሥራዎች ዛሬ በተጨባጭ ውጤት እየታዩ ይገኛሉ፡፡

የዝግጅት ክፍላችን ከልደታ ክፍለ ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከአቶ እንግዳው ጓዴ ጋር ቆይታ አድርጓል ተከታተሉን፡፡



**አቶ እንግዳው ጓዴ**
**አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመሪያ ስለ ከተማ ግብርና በልደታ ክፍለ ከተማ እየተሰራ ያለውን ስራ አጠቃላይ ምን ይመስላል?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፡-** መንግስት ለአርሶ አደርና ለከተማ ግብርና የሰጠውን ትኩረት ተከትለን በልደታ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን፡፡ ቀደም ሲል ከተማ ግብርና በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ላይ ብዙ ጥርጣሬ ነበር፤ ዛሬ ግን ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ ለገበያ የሚቀርብ ምርት በስፋት እየተመረተ ነው፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ የአመለካከት ለውጥ መፈጠሩን ያሳያል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በ2018 በጀት ዓመት የተመዘገቡ ዋና ዋና ውጤቶች ምን ይመስላሉ?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፡-** በእንስሳት እርባታ ዘርፍ 22,332 ነባር ተጠቃሚዎችን ማሳተፍ ችለናል፡፡ በእጽዋት ልማት ዘርፍ ደግሞ 43,240 ተጠቃሚዎች ተሳትፈዋል፡፡ በአጠቃላይ 65,572 ተጠቃሚዎች በከተማ ግብርና ተሰማርተው እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ ይህ ቁጥር የዘርፉን መስፋፋትና የማህበረሰቡን ተሳትፎ በግልጽ ያሳያል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የከተማ ግብርና ስራውን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቴክኖሎጅዎች ካሉ ቢገልጹልን?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፡-** ዘርፉን ዘመናዊና ምርታማ ለማድረግ በርካታ ቴክኖሎጂዎችን እያስተዋወቅን ነው፡፡ የዶሮ ኬጅ ቴክኖሎጂ፣ PEM አጠቃቀም፣ ዘመናዊ የሽግግር ቀፎዎች፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያዎችን በቅንጅት መጠቀም፣ ንጹህና ምርታማ ዘሮችን ማቅረብ እንዲሁም ስታንዳርዱን የጠበቀ የሽቅብ እርሻ ቴክኖሎጂ ከዋና ዋናዎቹ መካከል ናቸው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የማህበረሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ ምን ዓይነት ስራዎች ተሰርተዋል?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፡-** በኤክስቴንሽን ኮሙኒኬሽን ስራ ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥተናል፡፡ ቤት ለቤት የግንዛቤ ስራዎች፣ የህዝብ ንቅናቄዎች፣ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች፣ የልምድ ልውውጥ ጉብኝቶች እና ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፋፋት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም የነበረው አሉታዊ አመለካከት ተቀይሮ "ይቻላል" የሚል መንፈስ በማህበረሰቡ ውስጥ ተፈጥሯል፡፡

**ልደታ ፋና፦** በእንስሳት ጤና ጥበቃ ዘርፍ ምን አይነት ስራዎች እየተሰሩ ነው?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፦** የእንስሳት ጤና ጥበቃ ለልማታችን መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ለወተት ከብቶች፣ ለዳልጋ ከብቶች፣ ለበጎችና ፍየሎች፣ ለዶሮዎች እንዲሁም ለሌሎች እንስሳት የክትባትና የህክምና አገልግሎት እንሰጣለን። በተጨማሪም የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከል ሰፊ የክትባት መርሃ ግብር ተካሂዷል።

**ልደታ ፋና፦** ምርት የሚያመርቱ ተጠቃሚዎች የገበያ ችግር እንዳይገጥማቸው ምን ተደርጓል?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፦** ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ ምርት የሚያመርቱ አምራቾችን ከገበያ ጋር ለማገናኘት በየወረዳው የእሁድ ገበያ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም እንቁላልና ሌሎች ምርቶች በቅናሽ ዋጋ ለማህበረሰቡ እንዲደርሱ እየተሰራ ነው። ይህ የገበያ መረጋጋትን በማገዝ ረገድ ጉልህ ሚና አለው።

**ልደታ ፋና፦** በመጨረሻ ለልደታ ወጣቶችና ለማህበረሰቡ ምን መልዕክት አለዎት?

**አቶ እንግዳው ጓዴ፦** ከተማ ግብርና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ የስራ ዕድልና የገቢ ምንጭ ነው። በተለይ ወጣቶች በዚህ ዘርፍ ተደራጅተው ቢሰማሩ በአጭር ጊዜ ሀብት መፍጠር ይችላሉ። ስለዚህ ያሉትን ዕድሎች በመጠቀም በልማቱ እንዲሳተፉ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በአጠቃላይ በልደታ ክፍለ ከተማ የከተማ ግብርና ዘርፍ እያሳየ ያለው እድገት ከጓሮ አትክልት አልፎ የኢኮኖሚ እድገት፣ የገበያ መረጋጋት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ምንጭ ሆኗል ተግባሩን ማጠናከር ይገባል እያልን ጽሁፋችንን በዚሁ ቋጨን።

## ከምርት አቅርቦት እስከ ስርጭት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት በየደረጃው ግብረ ሀይል በማቋቋም ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። የከተማው ነዋሪዎች የኑሮ ጫና ለመቀነስ ከአርሶ አደሮችና ዩኔኖች ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪና የከተማ ግብርና ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የኑሮ ውድነት ለመከላከል ርብርብ አድርጓል። የእሁድ ገበያን በስፋት በማቅረብና ህገ-ወጥ ነጋዴዎችን በመቆጣጠር የገበያ ማረጋጋት ስራ ተሰርቷል። የከተማ አስተዳደሩ የገበያ አለመረጋጋት ጥያቄዎችን መፍትሄ በመስጠት በሚያደርገው ርብርብ የከተማው ነዋሪዎች የበኩላቸውን ሚና በመወጣታቸው ውጤታማ ስራ ተሰርቷል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት የገበያ አለመረጋጋትና የኑሮ ውድነትን ለመከላከል የኢንዱስትሪና የከተማ ግብርና ምርቶችን በስፋት፤በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብና የድጎማ ምርቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ በማሰራጨት ውጤታማ ስራ ተሰርቷል።የኑሮ ጫናን ለማቃለል ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የእሁድ ገበያዎችን በማስፋትና ህገ ወጥ ነጋዴዎችን በመቆጣጠር የገበያ ማረጋጋት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። በመሆኑም የገበያ ማረጋጋትና የኑሮ ውድነትን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ ከንግድ ጽ/ቤት ሃላፊ ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው ጋር ቆይታ አድርገናል መልካም ቆይታ።



**ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው**
**የንግድ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፦** የኑሮ ውድነትን ለመከላከል የምርት አቅርቦትን ለማስተካከል ምን እየተሰራ ነው ?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፦** የኑሮ ውድነትን ጫና ለመቀነስ የምርት አቅርቦትን በመጨመር እንዲሁም የገበያ ሰንሰለቱን በማሳጠር የሸማቹን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ተግባር በትኩረት እየተሰራ ይገኛል። በዚህም በአምራችና በሸማች መካከል ያለውን ረዘም ያለ የደላላ ሰንሰለት በመስቀረት ፣ ምርት ከአርሶ አደሩና ከአምራች ማህበራት ቀጥታ ወደ ከተማችን ሸማቾች እንዲደርስ ከ115 ምርት አቅራቢዎች ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር ምርት በስፋትና በዝቅተኛ ዋጋ እየቀረበ ይገኛል። ከዚህም ጎን ለጎን እንደ ዘይት፣ ስኳር፣ የስንዴ ዱቄት እና ጤፍ ያሉ መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች በህብረት ስራ ማህበራትና በማኪባ በኩል በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲሰራጩ ተደርጓል። ምርት በመደበቅ ሰው ሰራሽ እጥረትና የዋጋ ንረት የሚፈጥሩ ነጋዴዎችን ለመከላከልም 240 በክፍለ ከተማችን የሚገኙ መጋዘኖችን የመፈተሽና የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል። የክትትልና የቁጥጥር ስራው በቋሚነት ይበልጥ በማጠናከር በግብረሃይል ደረጃ በየደረጃው ባለው መዋቅር እየተሰራ ይገኛል::

**ልደታ ፋና፦** የእሁድ ገበያን ከማስፋትና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የተሰሩ ስራዎች ቢገልፁልን ?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፦** የእሁድ ገበያ የኑሮ ውድነትን ለመከላከልና አማራጭ የገበያ ቦታዎችን ለመፍጠር ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ሸማቾች ረጅም ርቀት ሳይጓዙ በየአቅራቢያቸው ምርት ማግኘት እንዲችሉ 14 የእሁድ ገበያ ማዕከላትን በማቋቋም ቁጥርና የስርጭት ተደራሽነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል። በተለይ ዘንድሮ በልዩ ኢኒሽቲብ በክፍለ ከተማ ደረጃ በወረዳ 9 አዲስ አንድ የገበያ ማዕከል በመገንባት ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል። በእነዚህ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች እንዲሁም በገበያ ማዕከሉ ሁሉም የምርት ዓይነት ማለትም የግብርና ምርቶች ፣የኢንዱስትሪ ምርቶችና እሴት የተጨመረባቸው ዳቦና እንጀራን ጨምሮ ከመደበኛው ገበያ ከ15% እስከ 20% ቅናሽ እንዲኖራቸው ከአምራቾች ጋር የጋራ ስምምነት የተደረገ ሲሆን፣ ይህም በሸማቹ ማህበረሰብ ላይ ይደርስ የነበረውን ጫና በከፍተኛ ሁኔታ አቅልሏል።

ከዚህ በተጨማሪም ማዕከላቱ ንፅህናቸው የተጠበቀ፣ ለገዢና ለሻጭ ምቹ እና የተስተካከለ ስነ-ስርዓት የሰፈነባቸው እንዲሆኑ የማስተባበር ስራዎች በልዩ ትኩረት ተሰርተዋል።

**ልደታ ፋና፡-** ህገ-ወጥ ንግድን ከመከላከል አንጻር የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን ?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** ፍትሃዊና ህጋዊ የንግድ ስርዓትን ለመዘርጋት የህገ-ወጥ ንግድ እንቅስቃሴን መግታት ቀዳሚ ተግባራችን በመሆኑ፣ ከፀጥታ አካላትና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተደራጀ የጋራ ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል። በዚህም መሰረት 774 ያለ ፍቃድ በሚነግዱ፣ የዋጋ ማጋነን በሚፈጥሩ፣ ደረሰኝ ሳይቆርጡ በሚያሽሹ እና ጥራት የሌላቸውን (ጊዜያቸው ያለፈባቸውን) ምርቶች በሚሸጡ ነጋዴዎች ላይ የማያወላዳ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎች ተወስደዋል። ከእርምጃው ባሻገርም ህገ-ወጥ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚና በህዝብ ጤና ላይ የሚያመጣውን ጠንቅ በማስረዳት፣ በ8588 ነጻ የጥቆማ ስልክ ቁጥር ህብረተሰቡ ራሱ የጥቆማና የክትትል ቀዳሚ አካል እንዲሆን ሰፊ የግንዛቤ መፍጠር ስራዎች ተከናውነዋል።

**ልደታ ፋና፡-** የንግድ ፍቃድ ቁጥጥርን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች ቢጠቀሱልን ?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** እያንዳንዱ የንግድ ተቋም በህጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ የክትትል ስራዎች በየደረጃው ተጠናክረዋል። በየአካባቢው የሚገኙ የንግድ ተቋማት የንግድ ፍቃድ ያላቸውና የታደሰ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከታታይ የድንገተኛና መደበኛ አሰሳ ስራዎች ተከናውነዋል። በእነዚህ ንቅናቄዎችም የንግድ ተቋማት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍና ደረጃ ልክ ብቻ እየሰሩ መሆኑንና ከተሰጣቸው ፍቃድ ውጭ ሌላ ስራ አለመስራታቸውን የመቆጣጠር ስራ የተሰራ ሲሆን፣ ፍቃዳቸውን በወቅቱ ያላደሱ ነጋዴዎችም እየተደረገ ባለው የክትትልና የቁጥጥር ስራ ወደ ህጋዊት እንዲመለሱ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎቶችን በኦንላይን በመሰጠቱ ያስገኘው ውጤትና ጠቀሜታ ቢያብራሩልን ?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎትን ወደ ዲጂታል ማስተላለፍ መቻሉ በዘርፉ ትልቅ እመርታ ያስመዘገበ ተግባር ሆኗል። ነጋዴው ማህበረሰብ በአካል ቢሮ ሳይመጣ ባሉበት በታ ሆነው በእጅ ስልኩ አገልግሎት ማግኘት በመቻላቸው እንግልት፣ አላስፈላጊ ወጪና ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። የአገልግሎት አሰጣጡ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት በመሆኑም፣ ቀደም ሲል ይስተዋሉ የነበሩ የሙስና እና የብልሹ አሰራር ክፍተቶችን ሙሉ በሙሉ በሚያስብል ደረጃ ማስቀረት ተችሏል። በተጨማሪም የንግዱን ማህበረሰብ መረጃ በዘመናዊ መልኩ በኢፋይሊንግ መያዝ መቻሉ፣ ለመንግስት የፖሊሲ ውሳኔዎችና ለቀረጥ/ታክስ አሰባሰብ ትክክለኛና ፈጣን መረጃ ለማግኘት ትልቅ ፋይዳ አበርክቷልል::የደንበኞች እርካታንም ወደ 95% ማሳደግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** የንግድ ስርዓታችን ጤናማና ፍትሃዊ መሆን የሚችለው የመንግስት፣ የነጋዴው ማህበረሰብና የሸማቹ ህዝብ ቅንጅት ሲጠናከር ብቻ ነው። የንግዱ ማህበረሰብ ከትርፍ ባለፈ ማህበራዊ ኃላፊነትን በማስቀደም ህጋዊነቱን ጠብቆ እንዲነግድ፤ ሸማቹ ማህበረሰብ ደግሞ ህገ-ወጥ አሰራሮችን በመጠቆም እና አላስፈላጊ የዋጋ ንረትን በጋራ በመታገል የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ተስፋነሽ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ተቋማዊ ስኬታማነት

በዚህ አምድ የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን ስኬታማነት ዳሰናልና ተከታተሉን መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** በ2018 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ ጽ/ቤታችሁ አፈጻጸም በአጠቃላይ እንዴት ነበር?

**አቶ ካሳሁን፡-** በ2018 በጀት ዓመት በተለያዩ የመሬት አስተዳደር፣ የልማት ዝግጅት፣ የካሳ ክፍያና የገቢ ማሰባሰብ ዘርፎች ከፍተኛ ውጤቶችን አስመዝግበናል። በተለይም ለከተማው ገቢ ማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ከዓመታዊ የሊዝ ክፍያ፣ ውዝፍ የሊዝ ክፍያና ከተለያዩ አገልግሎቶች 199.2 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ የተያዘውን ዕቅድ በእጥፍ በማለፍ 384.9 ሚሊዮን ብር ማሰባሰብ ችለናል። ይህም 193.2 በመቶ አፈጻጸም ነው።



**አቶ ካሳሁን ጥላሁን**
**የመሬት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

**ልደታ ፋና፡-** በካቢኔ ውሳኔዎች አፈጻጸም ረገድ ምን ያህል ስራ ተሰርቷል?

**አቶ ካሳሁን፡-** ከከተማ አስተዳደሩ ወደ ክፍለ ከተማችን የተላኩ 95 የካቢኔ ውሳኔዎችን ሙሉ መረጃ በማደራጀት በትኩረት ሰርተናል። ከእነዚህ 66ቱን በተሳካ ሁኔታ ለባለመብቶች ማስረከብ ተችሏል። የተቀሩት 29 ውሳኔዎች ደግሞ በሕጋዊ፣ በአስተዳደራዊ እና በሌሎች ተግዳሮቶች ምክንያት በሂደት ላይ ይገኛሉ።

**ልደታ ፋና፡-** በኮሪደር ልማት ስራዎች የተገኙ ውጤቶችስ?

**አቶ ካሳሁን፡-** የከተማዋን ገጽታ ለማሻሻል በ1ኛና 2ኛ ዙር ኮሪደር ልማት ሥራዎች ለተነሺ ዜጎች 441.7 ሚሊዮን ብር የካሳ ክፍያ ተፈጽሟል። ይህም 98.8 በመቶ አፈጻጸም ነው። ከዚህም 343 የቀበሌ ቤት እና 82 የግል ቤት ተነሺዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

**ልደታ ፋና፦** ለልማት ተነሺዎች ምትክ ቦታና ቤት በማቅረብ ረገድ ምን ተሰርቷል?

**አቶ ካሳሁን፦** ለልማት ተነሺዎች 70 ምትክ ቦታ የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል። በተጨማሪም ለ180 ተነሺዎች ምትክ ቤት እንዲሰጥ ለከተማ 166 ጥያቄዎች ቀርበዋል።

**ልደታ ፋና፦** በመሬት ዝግጅትና ባንክ ሥራዎች ምን ውጤት ተገኝቷል?

**አቶ ካሳሁን፦** ዘመናዊ የመሬት ባንክና የጥበቃ አሰራርን ለማጠናከር 7.98 ሄክታር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 10.96 ሄክታር መሬት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህም 137.3 በመቶ አፈጻጸም ነው። እንዲሁም 8.86 ሄክታር መሬት ለሀገራዊ ፋይዳ ፕሮጀክቶች እንዲውል ተለይቶ ተዘጋጅቷል።

**ልደታ ፋና፦** በመረጃና የክርክር መዝገቦች አያያዝ ምን ያህል ስራ ተሰርቷል?

**አቶ ካሳሁን፦** በበጀት ዓመቱ ለመሬት መረጃና ምዝገባ ኤጀንሲ ምላሽ ለመስጠት 4,072 ማህደራት ተስተካክለው ተልከዋል። ይህም ከ100 በመቶ በላይ አፈጻጸም ነው።

**ልደታ ፋና፦** የመጨረሻ መልዕክትዎ?

**አቶ ካሳሁን፦** በ2018 በጀት ዓመት ያስመዘገብነው ውጤት የሠራተኞቻችን፣ የአመራሩና የህብረተሰቡ የጋራ ጥረት ውጤት ነው። በቀጣይም የመሬት አስተዳደርን በዘመናዊ አሰራር በማጠናከር፣ የከተማውን ገቢ በማሳደግና ለልማት ተነሺዎች ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት በመስጠት የልደታን ልማት ለማፋጠን እንቀጥላለን።

## የግንባታ ፈቃድና ሕጋዊ የማስተካከያ እርምጃዎች

በክ/ከተማችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የግንባታ እንቅስቃሴ በስፋት ለማስቀጠል ህግና ስርዓት የተከተለ እንዲሆን እንዲሁም የተቀናጀ እንዲሆን ለማስቻል የከተማ አስተዳደሩ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን እንደገና ተቋቋሞ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶችን ለመወጣት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሰዎችን እያደረገ ይገኛል። በጽ/ቤቱ የህንጻ ግንባታ ፍቃድ አሰጣጥ፣ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር፣በመጠቀሚያ ፈቃድ እና የማስታወቂያ ፈቃድ፣ የመረጃ ዶክመንቴሽን እንዲሁም ሌሎች ልዩ ልዩ የአገልግሎት ሥራዎቻችን በዘመናዊነት መንገድ በማሰልጠንና ከግንባታ ጋር በተያያዘ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል። በ2018 በጀት ዓመትም ተቋሙን ለመለወጥ ጥረቱ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል። በመሆኑም ከልደታ ክፍለ ከተማ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ኃላፊ ከአቶ ዳዊት ጥበቡ ቆይታ አድርገናል ተከታተሉን።

**ልደታ ፋና፦** በቅድሚያ ከኛ ጋር ቆይታ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን።

**አቶ ዳዊት፦** እኔም በጽ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፦** በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ይግለጹልን?

**አቶ ዳዊት ፦** በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት የሚሰጡ አገልግሎቶች በአጠቃላይ ዋና ዋና አገልግሎቶች አምስት(5) የህንጻ ግንባታ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት፣የህንጻ ግንባታ ክትትል እና ቁጥጥር አገልግሎት መስጠት፣የህንጻ መጠቀሚያና ኢኒስፔክሽን አገልግሎት መስጠት፣የውጪ ማስታቂያና ፈቃድ ቁጥጥር አገልግሎት መስጠት፣የመረጃና ዶክመንቴሽን አገልግሎት መስጠት ናቸው።

**ልደታ ፋና፦** በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ከማዘመን አንጻር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ ዳዊት፦** እንደ ከተማ አስተዳደሩ አቅጣጫ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ከእጅ ንኪኪ እና አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ከማስቀረት አገልግሎቶችን ከማዘመን አንጻር እንደ ት/ቤት ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው ለአገልግሎት ወደ ጽ/ቤቱ የገቡ የፋይል ማስተዳደር /File adminis-tration/ ስራ ሲሆን በዚህ ፋይል ማስተዳደር ስራ ውስጥ ዋና ዋና ተግባር እና አስፈላጊነት በፅ/ቤቱ ለአገልግሎት የሚገቡ ፋይሎች በቀላሉ መዝግቦ በአምስቱ የስራ ሂደቶች /ቡድኖች/ የሚመሩ ፋይሎችን የመከታተያ ቁጥር በመስጠት ጊዜና ሰዓት ቀን በመመዝገብ የገቡ ፋይሎችን ብዛት በቁጥር ቅደም ተከተል ለማወቅ የሚረዳ እንዲሁም አገልግሎቶች በተቀመጡላቸው በስታንዳርድ መፈጸማቸውን ለአገልግሎት ወደ ጽ/ቤቱ የገቡ ፋይሎች ወደ የተኛው ቡድን/የስራ ሂደት/ ባለሙያ ጋር እንደደረሰ እንዲሁም ባጠቃላይ የስራ ዓመራሮች ድረስ በቀላሉ ስራን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል ቴክኖሎጂ በጽ/ቤታችን አልምተን እየተጠቀምን እንገኛለን። በዚህም ተገልጋይ እንግልትን በመቀነስ እንዲሁም በስታንዳርድ አገልግሎቶች በመሰጠታቸው የተገልጋይን እርካታ በመጨመር እና ፍትሃዊ አገልግሎት አሰጣጥ እና መልካም አስተዳደር እንዲኖር ተደርጓል።



**አቶ ዳዊት ጥበቡ**
**የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፦** ህገ-ወጥ ግንባታን ከመከላከል አንጻር የተሰሩ ስራዎችና የመጣ ውጤት ምን ይመስላል?

**አቶ ዳዊት፦** በጽ/ቤቱ በህጋዊ መንገድ አገልግሎት ጠይቀው በህንጻ ግንባታ ኮዶችና ስታንዳርዶች እንዲሁም ህጎች አሟልተው የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት አግኝተው በጽ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግላቸው ህንጻዎች በአግባቡ መከታተልና ከተሰጣቸው ህጋዊ ግንባታ ፈቃድ ውጪ የሚገነቡት ላይ ጠንከር ያለ እና አስተማሪ ህጋዊ ማስተካከያ እርምጃ ጽ/ቤቱ እየወሰደ ይገኛል። በዚህም በ9 ወር ውስጥ 43 ግንባታዎች ላይ የእርምት እርምጃ ተወስዷል። ከህንጻ ግንባታ መጠቀሚያ ኢንስፔክሽን አገልግሎት ጋር ተያይዞ የአገልግሎት ለውጥ የፓርኪንግ አገልግሎት ለውጥ በማድረግ አብዛኞቹ ከተፈቀደው ውጪ

ለስቶር፤ለባንክ አገልግሎት የዋሉትን በተሰጣቸው ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ በቁጥር በበጀት ዓመቱ እስካሁን 14 ህንጻዎች ላይ የእርምት እርምጃ በጽ/ቤቱ ተወስዷል፡፡







እርምጃ ተወሰደባቸው ህንፃዎች

በተጨማሪም ከህገ ወጥ የውጪ ማስታወቂያ ጋር ተያይዞ በከተማ አስተዳደሩ በተያዘው አቅጣጫ ስማርት ሲቲ ከመፍጠር ጋር ተያይዞ በዋናነት ከተያዙት ስራዎች ማንኛውም የውጪ ማስታወቂያ የከተማ አስተዳደሩ ባወጣው መመሪያና ደንብ መሰረት የውጪ ማስታወቂያ ስታንዳርድ አገልግሎት ማግኘት የሚችል መሆኑን በተለያየ ጊዜ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ ሆኖም ግን የከተማዋን ገጽታ የሚያበላሹ ህገ-ወጥ የውጪ ማስታወቂያዎች ላይ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት በ9 ወር ውስጥ 3370 ከህግ ውጪ ቢልቦርዶች የተሰቀሉ/የተነተጠለጠሉ/ እና የተቀመጡ የውጪ ማስታወቂያዎችን የማስተካከያ/ስታንዳርድ/ የማስጠበቅና የማስወገድ /የማስነሳት/ ስራ ተሰርቷል፡፡



ህገ ወጥ ማስታወቂያ ሲወገድ

በዚህም ህገ ወጥትን በመከላከል ጽ/ቤቱ በህንጻ ግንባታ የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላን እና ስታንዳርዳይዜሽን ከማስጠበቅ አንጻር ከፍተኛ አስተዋኦ ጽ/ቤቱ እያደረገ ይገኛል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ከህገ ወጥ የውጪ ማስታወቂያ ጋር ተያይዞ በክ/ከተማችን ገጽታ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ የውጪ ማስታወቂያ ተገልጋዩ እንዲጠቀም በማድረግ የክ/ከተማችንን ስማርት ሲቲ ከማድረግ አኳያ እንደ ጽ/ቤት ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለዚህም ማሳያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥረ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ከ11 ክፍለ ከተሞች በውጪ ማስታወቂያ ስታንዳርድ ከማስጠበቅ እንዲሁም ህገ-ወጥ የውጪ ማስታወቂያዎችን በማስነሳት/ማስወገድ/ አንደኛ በመውጣ ተሸላሚ ሆኗል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ወደ ተቋማችሁ የሚመጡ ተገልጋዮች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረጋችሁ ያላችሁት ጥረት እንዴት ይገለፃል ?

**አቶ ዳዊት ፡-** በልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ተገልጋዮች ቅድመ ሁኔታዎች /የአገልግሎት/መስፈርት እስከ አሟሉ ድረስ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ፈጣን አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ በመጨመር የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መቅረፍ እንዲሁም የሌብነትና ብልሹ አሰራር አጥብቀን በመከላከል እንዲሁም ህገ ወጥ ግንባታን ከተሰጣቸው የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ለውጥ ያደረጉ ከስታንድረድ በታች የሆኑ የውጪ ማስታወቂያዎችን ወደ ስታንዳርድ በማምጣት ፕላኑንና ስታንዳርድ የማስጠበቅ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል ዋና ተግባራችን ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ዳዊት፡-** እንደ ልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳድር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከሌብነትና ብልሹ አሰራር የነጻ እና አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ አገልግሎት አሰጣጡን ፈጣንና ቀልጣፋ በማድረግ ለተገልጋዩ ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም ህገ ወጥነትን ከህንጻ ግንባታ ከመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ከተሰጣቸው የግንባታ ፈቀድ አገልግሎት ውጪ ለውጥ በሚያደርጉ እንዲሁም ከስታንዳርድ ውጪ የሆኑ ህገ-ወጥ ውጪ ማስታወቂያ በመከላከል አንጻር የከተማችንን ከመዋቅራዊ ፕላን ከማስጠበቅ አኳያ እንዲሁም ስታንዳርዳይዜሽን በማስጠበቅ ስማርት ሲት ለመፍጠር የሚደረገው ርብርብ እንደ ልደታ ክ/ከተማ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት የበኩላችንን እንድንወጣ እላለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን ፡፡

**አቶ ዳዊት፡-** እኔም መረጃ እንዳካፍል ስለጋበዛችሁኝ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ግንባታ ለዘላቂ ልማት

የአንድ አካባቢ ሁለንተናዊ ዕድገትና የነዋሪዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚለካው በግንባታና መሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ጥራትና ፍጥነት ነው። የክፍለ ከተማችን የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች አጠቃላይ ሒደት፣ ያሉ አሠራሮች፣ የተገኙ ስኬቶችና የወደፊት አቅጣጫዎችን ከዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት ሃላፊ ከሆኑት ከአቶ ቢኒያም ሰይፉ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።



**አቶ ቢኒያም ሰይፉ**
**የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** አንድ የግንባታ ሥራ ለማከናወን የሚፈልግ አካል ምን ሊያቀርብ ይገባል?

**አቶ ቢኒያም፡-** ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል የግንባታ ሥራ በስኬት ለመጀመር በሕግና በአሠራር የተቀመጡ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላት ግድ ይላል። በዚህም መሠረት አንድ ግንባታ ለመጀመር የሚፈልግ አካል በመጀመሪያ ሕጋዊ የቦታው ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ ካርታ ወይም የሊዝ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪም ህንጻው የሚያርፍበት የአፈር ምርመራ የላብራቶሪ ውጤት ከተገኘ በኋላ በባለሙያ የተረጋገጠ የስነ-ህንጻ (Architecture)፣ የሕንጻ መዋቅር (Structural)፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካልና እንደ አስፈላጊነቱ ሜካኒካል ክፍሎችን ያካተተ የተሟላ የዲዛይን ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅበታል። እነዚህ ሰነዶች ተገምግመው ከሚመለከተው አካል ሕጋዊ የግንባታ ፈቃድ (Building Permit) ማግኘት ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም ትላልቅ ፕሮጀክቶች በአካባቢና በማኅበረሰብ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ ያጠኑበትን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ማያያዝ አለባቸው። በመጨረሻም ግንባታውን በተያዘለት ጊዜና ጥራት ለማጠናቀቅ የሚያስችል የስራ ተቋራጩና የአማካሪውን (Consultant) የፋይናንስና የቴክኒክ አቅም ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በቅድሚያ ማቅረብ ግዴታ ነው።

**ልደታ ፋና፡-** በክፍለ ከተማው የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በታለመላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ምን እየተሰራ ይገኛል?

**አቶ ቢኒያም፡-** የፕሮጀክቶች መጓተት የመንግስትን ሀብትና የሕዝብን ተስፋ ለብክነት ስለሚዳርግ፣ በክፍለ ከተማችን ያሉ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ቁጥጥርና ድጋፍ በከፍተኛ ትኩረት እየተከናወነ ይገኛል። ይህንን ለማሳካትም የባለሙያዎች ቡድን በመመደብ የ7/24 የስራ ባህልን በመከተል በየሳምንቱና በየደረጃው የፕሮጀክቶችን አካላዊ አፈጻጸም (Physical Progress) በመስክ ላይ በቀጥታ የመገምገምና ቀጣይነት ያለው የሱፐርቪዥን ሥርዓት የመዘርጋት ሥራ እየተሰራ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ከተቋራጮች ጋር የተገባውን ውል መሠረት በማድረግ፣ ሥራዎችን ያለበቂ ምክንያት ያዘገዩ አካላት ላይ ሕጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድና ክፍያዎችን ከአፈጻጸም ጋር በጥብቅ የማገናኘት አሠራር እየተተገበረ ይገኛል። መደበኛ የክትትል መድረኮችን በማጠናከርም፣ በየአሥራ አምስት ቀኑና በየወሩ ከተቋራጮች፣ ከአማካሪ መሐንዲሶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ የግምገማ መድረኮችን በማካሄድ ማነቆዎችን ወዲያውኑ በመስክ ላይ የመፍታት ልምድ ተዘርግቷል። እንዲሁም የፕሮጀክቶችን ፍጥነት ለመጨመር የወሰን ማስከበር (Right of Way) ችግሮችን በፍጥነት በመፍታትና የክፍያ ሰነዶችን (Certificates) በጊዜ በማፅደቅ የንብረትና የፋይናንስ አቅርቦቱ እንዲሳለጥ እየተደረገ ነው።

**ልደታ ፋና፡-** ፕሮጀክቶቹ መሰራታቸው ለህብረተሰቡ ያላቸው ጠቀሜታ ምንድነው?

**አቶ ቢኒያም፡-** በክፍለ ከተማው የሚገነቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ቀጥተኛ ተጠቃሚው ማኅበረሰቡ በመሆኑ እነዚህ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ በርካታ ሁለንተናዊ ጥቅሞችን ያስገኛሉ። በአንድ በኩል እንደ ጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶችና የአስተዳደር ቢሮዎች ያሉ ግንባታዎች መፋጠናቸው ነዋሪው ጥራቱን የጠበቀና ቀልጣፋ የመንግሥት አገልግሎትን በቅርብ ርቀት እንዲያገኝ ያደርገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በእያንዳንዱ የፕሮጀክት ሳይት ላይ ግንባታው በሚካሄድበት ወቅት ለበርካታ የአካባቢው ወጣቶችና ሴቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጠራል። ከሁሉ በላይ ደግሞ ደረጃቸውን የጠበቁ የመንገድ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮችና የጋራ መኖሪያ ቤቶች መገንባታቸው በአካባቢው የነበረውን የልማት ጥያቄ በመመለስ የነዋሪዎችን ጤና፣ ደህንነትና አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ጥራትን በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽለዋል።

**ልደታ ፋና፡-** ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላችሁ ቅንጅታዊ አሠራር ምን ይመስላል?

**አቶ ቢኒያም፡-** የማንኛውም ግንባታ ስኬት የሚወሰነው በቅንጅታዊ አሠራር (Synergy) ላይ በመሆኑ ክፍለ ከተማችን ይህንን መሠረት በማድረግ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርብ ትስስር ይሠራል። ከመሠረተ ልማት አቅራቢዎች ማለትም ከውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፣ ከኤሌክትሪክ አገልግሎትና ከቴሌኮም ጋር በጋራ የታቀደና የተቀናጀ አሠራር በመዘርጋት፣ የቅንጅት ማነስ የሚያስከትለውን የሀብት ብክነትና የመሠረተ ልማት ስራ መደጋገም ማስቀረት ተችሏል። ከተጠቃሚው ነዋሪ ማኅበረሰብ ጋርም ቢሆን የልማት ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት ሰፊ ውይይት የሚደረግ ሲሆን፣ በግንባታ ሒደትም ነዋሪው የባለቤትነት ስሜት ኑሮት የራሱን የክትትልና የጥበቃ ሚና እንዲወጣ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ ከፋይናንስና ዕቅድ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የፕሮጀክቶች በጀት በወቅቱ እንዲለቀቅና የሀብት ብክነትም ሆነ የኦዲት ግኝቶች እንዳይኖሩ የጋራ የቁጥጥር ሥርዓት እየተከተልን እንገኛለን።

**ልደታ ፋና፡-** የግንባታ ሥራዎች መሠራታቸው ለኅብረተሰቡ ብሎም በአጠቃላይ እንደ ክ/ከተማ ያላቸው ሚና ምንድነው?

**አቶ ቢኒያም፡-** እነዚህ ግንባታዎች ለአንድ አካባቢ ዘላቂ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ያላቸው ሚና ስትራቴጂካዊና የጀርባ አጥንት የሚባል ነው። ዘመናዊና ውብ ዲዛይን ያላቸው ሕንጻዎችና መሠረተ ልማቶች የክፍለ ከተማችንን ገፅታ ሙሉ በሙሉ በመቀየር አካባቢውን ለኢንቨስትመንት፣ ለቱሪዝምና ለንግድ ሥራዎች እጅግ ሳቢና ተወዳዳሪ ያደርጉታል። በተለይም ደግሞ የፍሳሽ ብክለትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመከላከል የሚሠሩ ዘመናዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታዎችና የአረንጓዴ ልማቶች የከተማዋን ሥነ-ምህዳር በማስተካከል የነዋሪዎችን ጤና ለመጠበቅና ንፁህ አካባቢ ለመፍጠር የማይተካ ሚና አላቸው። በተጨማሪም የሕዝብ ጥያቄ የሆኑ ትልልቅ ልማቶችን በጥራትና በዲዛይኑ መሠረት በጊዜ ገደቡ ገንብቶ ለነዋሪው ማስረከብ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን መተማመን፣ አንድነትና መልካም አስተዳደር ይበልጥ ያጠናክራል።

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ቢኒያም፡-** ልማት የጋራ ሂደት ነው፤ የመንግሥት ዓላማና ፍላጎት የሕዝባችንን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽሉ ጥራት ያላቸው መሠረተ ልማቶችን በተገቢው ጊዜና በቁጠባ መገንባት ነው። ይህ እንዲሳካ የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የተጣለባቸውን ሙያዊና አገራዊ ኃላፊነት በታማኝነትና በፍጥነት ሊወጡ ይገባል። ነዋሪው ማኅበረሰብም የተገነቡ የልማት አውታሮችን እንደ ጠቅላላ ሀብቱ በመቁጠር እንዲጠብቃቸውና በግንባታ ሂደት ለሚፈጠሩ ጊዜያዊ መስተጓጎሎች አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን ክፍለ ከተማችንን የብልጽግና ተምሳሌት እናደርጋታለን።

## ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም

ውስን የሆነውን የመንግስትና ህዝብ ሀብት ወይም በጀት ለታለመለት ዓላማ ማዋል እንዲችል በማሰብ ከከተማ የወረደውን በጀት እንደ ክፍለ ከተማችን ተጨባጭ ሁኔታ የተደለደለውን በጀት መሰረት በማድረግ ለሁሉም ባለበጀት መ/ቤቶች ደልድለን በማቅረብ በየደረጃው ያለ አካል እንዲያፀድቀው ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በጀቱ ወደ ስራ በሚገባበት ጊዜ ለታለመለት ዓላማ ማዋል እንዲችል የተለያዩ ስራዎች ተሰርቷል፡፡ቅድሚያ ተሰጥቶዋቸው ሊሰሩ የሚገቡ ስራዎች መሰራት እንዲችሉ እንዲሁም በዋናነት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በፋይናንስ አሰራርና መመሪያ ብቻ ወጪዎች እንዲከናወኑ በርካታ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በመስራት ተጠያቂነት እንዳይኖር ይህንን ጥንካሬ በቀጣይነት እንዲተገበር በተቋማችን የሚደረጉ ጥረቶች እንደተጠበቀ ሆኖ የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ሚና ከፍተኛ መሆን ይገበዋል፡ ፡ የመንግስት ስራዎች ሲከናወኑ የሚያስፈል ገው የበጀት ጥያቄ በመኖሩ እያንዳንዱ በባለቤትነት ስሜት የፋይናንስ ስርአትን የተከተለ መሆኑን ብቻ እያረጋገጡ መሄድ አስፈላጊ ሲሆን የመንግስትና የህዝብ ሃብት የፋይናንስ አሰራር ስርዓትን ተከትሎ ስራ ላይ እንዲውል ምን ስራዎች እየተከናወኑ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን በልደታ ክፍለ ከተማ የፋይናንስ ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ተኽላይ አፅብሃ ጋር ቆይታ አድርጋለች፡፡ መልካም ንባብ፡፡



**አቶ ተኽላይ አፅብሃ**
**የፋይናንስ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራትና የተመዘገቡ ስኬቶች ምንድን ናቸው?

**አቶ ተኽላይ፡-** የማዘጋጃቤታዊ ገቢን ከማሳደግ አንጻር በተቀመጠው እቅድ መሰረት መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ህብረተሰቡ ለመንግስት ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በማስጀመር አጠናቆ በማስረከብ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ ገቢ የመሰብሰብ አቅም ከታቀደው እቅድ አንጻር አበረታች መሆኑ፤የበጀት አፈጻጸም ጥቅም ላይ በማዋል ዉጤታማ መሆኑ፤የሌብነት እና ብልሹ አሰራርን ታግሎ ማስተካከያ ከማድረግ አንጻር በኦዲት ምርመራ የተገኙ ግኝቶችን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ በግለሰቦች እጅ የሚገኛውን የህዝብ እና የመንግስት በጀት ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የበጀት አጠቃቀምና ቁጥጥር ሥርዓቱን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ምን ዓይነት አዳዲስ አሰራሮች (Reforms) ተዘርግተዋል?

**አቶ ተኽላይ፡-** በተቋማት ተመድበው ለሚገኙ ባለሙያዎች ላይ በበጀት አጠቃቀም መመሪያ ላይ ግንዛቤ መስጠት የተቻለ ሲሆን በሌላ በኩል የተቋማት በጀት አፈጻጸማቸውን በቅርበት በመከታተል የውይይት መድረክ በማመቻቸት የጋራ ማድረግ መቻሉ፤በተመረጡ የበጀት ዝውውሮች ላይ ትኩረት በመስጠት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እየታየ የሚፈቀድበት አሰራር መዘርጋት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ ግልጽነትና ተጠያቂነትን (Transparency and Accountability) ለማስፈን እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ምንድን ናቸው?

**አቶ ተኽላይ፡-** በጽ/ቤቱ የሚሰጡ 11 ዋና ዋና አገልግሎቶችን ተገልጋይ አገልግሎቱን ፈልጎ ለማግኛት ወደ ጽ/ቤት ሲመጣ መሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያሟላ በጽ/ቤቱ መግቢያ በር ላይ በባነር ተዘጋጅቶ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ እንዲለጠፍ የተደረገ እና በተጨማሪም በብሮሸር ህትመት በማዘጋጀት ተደራሽ ተደርጓል፡ ፡ በፋይናንስ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ላይ ከክ/ከተማ እስከ ወረዳ ለተመረጡ 400 የህ/ሰብ ክፍሎች ጋር አንድ ጊዜ የቅድመ በጀት ውይይት ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለ375 የሂሳብ፣ግዥ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ዘመናዊ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን (በIBEX System iTAP System) ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ያለንበት ደረጃ ምን ይመስላል?

**አቶ ተኽላይ፡-** ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አንጻር እንደ ጽ/ቤት ውጤታማ መሆን የተቻለ ሲሆን ለተቋማት ፍትሃዊ የበጀት ድልድል ስራ መስራት፤ተቋማት የበጀት ጥያቄዎችን ተመልክቶ በጀት የማስተላለፍ፤ገቢ መሰብሰብ ክትትል ማድረግ፤የተለያዩ ክፍያዎችን ወጪ የማሳወቅ ለምሳሌ የሠራተኞች ደመወዝ እና የሥራ ማስኬጃና የካፒታል ፕሮጀክቶች ክፍያ እየተሰራበት ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** የውስጥ ኦዲትና የፋይናንስ ቁጥጥር መሥሪያ ቤቱን ከብክነት በመጠበቅ ረገድ ያለው ሚና እንዴት ይገለጻል?

**አቶ ተኽላይ፡-** በሌብነትና ብልሹ አሰራር ዙሪያ በክ/ከተማው ስር ለሚገኙ ተቋማት በተደረገው የኦዲት ምርመራ የተገኙ ግኝቶችን / አሰራር ችግሮች/የፋይናንስ አዋጅ፤ደንብና መመሪያውን ተከትሎ ባለመፈፀም በተወሰደው የእርምት እርምጃ ክትትል በማድረግ ብር 2,198,352.00 የህዝብና የመንግስት በጀት በማስመለስ 100% ተግባራዊ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና ፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ተኽላይ፡-** የመንግስት ስራዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የበጀት አቅርቦት ወሳኝ ቢሆንም እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በባለቤትነት ስሜት የፋይናንስ ስርዓቱንና መመሪያውን ተከትሎ መስራት ይኖርበታል። ተጠያቂነት የሌለው አሰራርን ለመገንባትና የተመዘገቡ ጥንካሬዎችን ለማስቀጠል የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ሚና ከፍተኛ ሊሆን እንደሚገባ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እና ለሰጡን መረጃ እናመሰግናለን።

**አቶ ተኽላይ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## ኢንዱስትሪ ልማት ለቀጣይ ዕድገት

ሀገራችን ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በምታደርገው ጉዞ የኢንዱስትሪ ልማት የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት እንዲሆን በልዩ ትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡ ፡መንግስት የድህነት ቅነሳ ግብን ለማሳካትና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ያተኮሩ ስትራቴጅዎችን ቀርጾ ወደ ተግባር ገብቷል።በተለይም በ2018 በጀት ዓመት የተጀመረውን የዘርፉን ተመዳዳሪነት የሚያሳድገው አዲሱ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታት ትልቅ ዕድል ፈጥሯል።

በዚህም መሰረት በክፍለ ከተማችን የሚታየውን የስራ አጥነትና የድህነት ችግር ለመቅረፍ የግልና የምህበር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በልዩ ሁኔታ ድጋፍ እየተሰጣቸው ይገኛል።እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲተኩና የኤክስፖርት ምርቶችን በማሳደግ የውጭ ምንዛሬ ግኝቶችን እንዲያሳድጉ መንግስታዊ ድጋፎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።ከዚህ ጎን ለጎን ከተማችን እያከናወነችው ያለው የኮሪደር ልማትና ሌሎች የመሰረተ ልማት ስራዎች ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ምቹ ሁኔታን እየፈጠሩ ይገኛሉ።

የኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት የተጣለበትን ሀገራዊ ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የአምራቾችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ቀልጣፋና ተደራሽ የድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት ላይ ይገኛል።

በመሆኑም ጽ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ያለፉትን ጥንካሬዎች በማስቀጠልና ውስንነቶችን በመለየት የ2018 በጀት ዓመት ስራዎችን በማከናወን ለ2019 በጀት ዓመት እንደግብዓት ይወስዳቸዋል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት መንግስታዊና ቴክኒካዊ የምክር ድጋፎችን በማቅረብ እንዲሁም የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ/ካይዘን አገልግሎት በመስጠት አምራች ኢንዱስትሪዎች በብቃትና በተወዳዳሪነት እንዲያድጉ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል።

በ2018 በጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ያከናወናቸውን ስራዎች በተመለከተ /ቤቱን ኃላፊ አቶ አበበ ዱላ ጠይቀን የሰጡንን ሃሳብ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።



**አቶ አበበ ዱላ**
**የኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**በ2018 በጀት ዓመት አምራቾችን ከመደገፍ አንጻር የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አበበ፡-**በ2018 በጀት ዓመት ለ22 ኢንዱስትሪዎች በማሽነሪ ድጋፍ በማድረግ በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል።ሌላው የቴክኒክና የምክር አገልግሎት የተሰጠ ድጋፍ ሲሆን ለ8 ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጅ መረጣና የኮሚሽንግና የምክር አገልግሎት በመስጠት ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** ለኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የስራ ዕድል ፈጠራና ምርታማነትን ለማሳደግ የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አበበ፡-**የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የንግድ ልማት ድጋፍ በመስጠት ኢንዱስትሪዎች በዕቅድ የያዙት ዓላማ እውን እንዲሆን እየተሰራ ይገኛል።ሌላው የስራ ዕድል ፈጠራና የሰለጠነ የሰው ሀይልን አቅርቦትን ለማሻሻል በተወሰደው ርምጃ ለ546 ዜጎች በኢንዱስትሪው ዘርፍ የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሰለጠነ የሰው ሀይልን ለማቅረብ በተሰራው ስራ 172 የሰለጠኑ ሰዎችን ማቅረብ ችለናል፤

**ልደታ ፋና፡-** የቴክኖሎጅ ሽግግርና ማሻሻያን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢገልፁልን?

**አቶ አበበ፡-**በ2018 በጀት ዓመት የቴክኖሎጅ ሽግግርና ማሻሻያ በተመለከተ በትኩረት የተሰሩ ሲሆን በውስጡም የቴክኖሎጅ መቅዳት የምርት ናሙናና የማሽነሪ/ቴክኖሎጅ ሽግግርን ያካትታል። በ2018 በጀት ዓመት 6 ቴክኖሎጅዎችን በመቅዳት ለአገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን አምራች ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጅ ሽግግር ተደርጎላቸዋል።ከዚህ በተጨማሪም የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅምና የምርታማነት ዕድገት ስንመለከት ደግሞ የተቋማትን የምርት ልኬት የተከናወኑ ሲሆን የኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ዕድገት ለማሳደግ በተደረገው የኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ውጤታማ ስራዎችን መስራት ችለናል።

**ልደታ ፋና፡-** ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱትን ምርት ለውጭ ገበያ እንዲልኩ ከማስቻል አኳያ የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አበበ፡-** በያዝነው በጀት ዓመት ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱትን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ በተሰራው ስራ አዲስ ኤክስፖርተሮችንና ነባር ኤክስፖርተሮችን በማጠናከር ምቹ ሁኔታዎችን እንዲያገኙና የገበያ ትስስርን እንዲያገኙ የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል።

**ልደታ ፋና፡-** አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ከማቋቋምና ወደስራ በማስገባት የስራ ዕድልን ከመፍጠር ጋር በተያያዘ የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አበበ፡-** በ2018 በጀት ዓመት 8 ኢንዱስትሪዎችን ወደስራ ያስገባን ሲሆን በተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች 116 ዜጎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረናል።ከዚህ ጋራ በተያያዘም 53 ዕድሎች ለሴቶች ተጠቃሚነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን 49 ወጣቶችም በተፈጠሩ የስራ ዕድሎች ላይ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን የአካል ጉዳተኞችም ተጠቃሚ ሆነዋል።የአቅም ግንባታ ስልጠናን ለመስጠት በተሰራው ስራ ለ33 ኢንዱስትሪዎች የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ

**አቶ አበበ፡-**ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን ከሀገርም አለፈው ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡና ለስራ ዕድል ፈላጊዎች የስራ ዕድልን መፍጠር እንዲችሉ ለማድረግ ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል የሚል መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን ።

**አቶ አበበ፡-** እኔም መረጃ እንዳካፍል ስለጋበዛችሁኝ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

## ስማርት ሲቲን የመገንባት ራዕይ በልደታ

የአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ቢሮ እንዲሁም በተዋረድ ለሚገኙት ፕላንና ልማት ጽ/ቤቶች ለተቋሙ በተሰጠዉ ተግባርና ሀላፊነት መሰረት ሁለት ፕላኖችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን እነዚህም የስፓሻል ፕላን (ገጸ ምድር ፕላን)፣የማህበራዊ ኢኮኖሚ ልማት እቅድ፣አፈፃፀም፣ ክትትል እና ግምገማ ናቸዉ። የልደታ ክ/ከተማ ፕላንና ልማት ጽ/ቤት መዋቅራዊ ፕላኑን ለመፈፀም በተዘጋጁ ዝርዝር የስፓሻል ፕላኖች መሰረት ለተገልጋዮች እና ባለድርሻ አካላት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል የማህበራዊ ኢኮኖሚ ልማት ፕላን፣የአፈፃፀም ሪፖርት፣የክትትል፣ ድጋፍ እና ምዘና ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል ።

ሌላው የክፍለ ከተማዉን ስፓሻል ፕላን ዝግጅትና አሰራር ከማሻሻል አንፃር ከመሬት ተቋማት እና ግንባታ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ጽ/ቤት ለቀረቡ የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ጥናቶች፣ የፕላን ማብራሪያና አስተያየት ጥያቄዎች ከመዋቅራዊ ፕላን አኳያ በማየት ለሁሉም የፕላን ማብራሪያ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ለሁሉም የፕላን ማብራሪያ ምላሽ መስጠት ተችሏል።

በክፍለ ከተማው የሚገኙትን የመንገድ ፕላን መረጃዎች በአውቶካድ ሶፍት ዌር በአንድ ቤዝማፕ የማደራጀት ስራ ተከናውኗል። የይዞታ ካርታዎች እና የግንባታ ፈቃድ መረጃዎች በመሰብሰብ ከፕላን አንጻር ትክክለኛነታቸው በማረጋገጥ በቤዝማፕ የማደራጀት ስራ በመከናወን የግንባታ ፈቃድ መረጃዎችን በቤዝማፕ እንዲደራጅ ተደርጓል። ሰብሳቢና የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ አርንጓዴ ልማት፣የወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ አካባቢዎች የፕላን አፈፃፀም እና አጠቃቀም በቀጣይ ወደ ቁጥጥር ስራዉ ለመግባት በሚያስችል ሁኔታ የመስክ ክትትል በማድረግና ሪፖርት በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ቢሮ እንዲቀርብ ተደርጓል።

የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት እቅድ እና የአፈጻፀም ሪፖርት ከማዘጋጀት አንፃር የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ በሴክተሮች የተዘጋጁ እቅዶችንና ሪፖርቶችን በማሰባሰብ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩን መሪ እቅድ፣ የተከለሰ እቅድ እና ሪፖርቶችን በማዘጋጀ ለክፍለ ከተማ አስተዳደሩ በወቅቱ እንዲቀርብ የማድረግ ስራዎች እየተሰራ ይገኛል።

የፕላን መረጃ ዝግጅት አደረጃጀትና ስርጭት በተመለከተ ተቋማችን የተለያዩ የፕላን መረጃዎችን የማደራጀትና ለፕላን ተግባረ ተቋማት ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን በዚሁም መሰረት በየበጀት አመቱ የሚዘጋጀዉን የሳተላይት ምስል መረጃ፣ ከማዕከል የተላከ ወቅታዊ የመዋቅራዊ መንገድ መረጃ፣ የህንፃ ከፍታ ማሻሻያ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል እንድደርስ ማድረግ መቻሉ። በመሆኑም ከልደታ ክፍለ ከተማ ፕላንና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ከሆኑት ወ/ሮ ወይኒቱ ሀይሉ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**ልደታ ፋና ፡-** ክፍለ ከተማው በከተማ ፕላንና ልማት ረገድ የያዘው ዋናው ራዕይና ግብ ምንድነው?

**ወ/ሮ ወይኒቱ፡-** ከተማችን አዲስ አበባ እንደነደፈው በ2022 ዓ.ም በዘመናዊ ፕላን የሚትመራ የለማችና የበለፀገች ከተማ ሆና ማየት። ግቡም የክፍለ ከተማዉን ስፓሻል ፕላን ዝግጅትና አሰራር ማሻሻል፣በክትትል፣በግምገማና በቁጥጥር የስፓሻል ፕላን ትግበራ አፈፃፀም ውጤትማነት ማረጋገጥ፣የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ዝግጅት ስራዎችን እና ፕላን አፈፃፀምና የልማት ፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ እንዲሁም የተቋማት አፈፃፀም ምዘና ስራዎችን ማሻሻል እና የፕላን መረጃ እና ስታትስቲክስ ስርጭትን ማሳደግ በክፍለ ከተማው የተሻለ ነገር ለመስራት አንግበን እየሰራን መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ።



## ወ/ሮ ወይኒቱ ሀይሉ
### የፕላንና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የክፍለ ከተማው ፕላን ከዋናው ከተማ ፕላን ጋር በማጣጣም ረገድ ምን አይነት ስራዎች እየተሰሩ ነው ?

**ወ/ሮ ወይንቱ፡-** የክፍለ ከተማው መዋቅራዊ ፕላን ትግበራ ከከተማ ፕላን ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የተለያዩ ማስፈፀሚያ ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላን ፣ የኮሪደር ልማት ፕላን ትግበራ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥረት ይደረጋል። የመዋቅራዊ ፕላኑ በየ2 አመት ተኩል በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ተለይተው እንዲሻሻሉ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ አፈፃፀሙ ክትትል ይደረግበታል።

ሌላው በ2018 በጀት አመት የፕላን አሰተያየት ምላሽ መስጠትን በተመለከተ የመሬት አጠቃቀም እና የህንጻ ከፍታ የፕላን ማብራሪያ ጥያቄዎች በመቀበል ወደ 356 የፕላን ማብራሪያ ጥያቄዎች ከተለያዩ ተቋማት የቀረቡ ሲሆን ከመዋቅራዊ ፕላን አኳያ ታይቶ ለሁሉም የፕላን ማብራሪያ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ተችሏል።

ይህም ከ2017 በጀት አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ186 ልዩነት ያለው መሆኑ እና የተሻለ ስራ የተሰራ መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ። እንዲሁም የውስጥ ለውስጥ የመንገድ ጥናትን በተመለከተ ከፕላኑ አንፃር በማየት 4 የቀረቡ ጥያቄችን በመቀበል የመንገድ ጥናቱ በማጥናት የመልካም አስተዳደር ችግር የነበረውን መፍታት የቻልን መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** በክፍለ ከተማው ውስጥ የሚካሄዱ ግንባታዎች የፕላን ስታንደርድና ጥራት እንደጠበቁ የሚደረገው የክትትል ስርዓት ምን ይመስላል?

ወ/ሮ ወይኒቱ፡- በቢሮ ደረጃ እና በክ/ከተማ ደረጃ የተፈቀዱ የግንባታ ፈቃድ መረጃዎችንና የፕላን ስምምነቶችን በተቻለ መጠን በ7ቀነት ጊዚያት ውስጥ ተከታትሎ ከፈቃድ ሰጪው ተቋም በመረከብ ከፕላን ስታንደርድና ህግጋት አንፃር ትክክል ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ይደረገል ። በመስክም በተፈቀደው ፕላን መሰረት የተገነቡ ስለመሆናቸው የመስክ ኦዲት ይከናወናል ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው የግንባታ መረጃዎች በፊቃድ ሰጪው ተቋም ማስተካከያ እንድደረግበት በግብረ- መልስ እንዲደርሳቸው በማድረግ ማስተካከያ እንዲያደርጉ ይደረጋል።

ይህም በ2018 በጀት ዓመት በ9 ወራት የተሰበሰበው የግንባታ ፈቃድ መረጃ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲናጻጸር በ18 ብልጫ መኖሩን ገልፀዋል።

**ልደታ ፋና፡-** በክፍለ ከተማው ውስጥ ላሉ ክፍት ቦታዎችና ለመናፈሻዎች በፕላኑ ላይ ምን ያህል ትኩረት ተሰጥቷቸዋል?

**ወ/ሮ ወይኒቱ፡-** ህገ ወጥ የመሬት ወረራ እንዳይከናወንባቸው በክፍለ ከተማው የሚገኙ ክፍትና አረንጓዴ ቦታች በፕላኑ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል በተጨማሪም ከክፍለ ከተማው ውበትን አረንጓዴ ልማጽ ጽ/ቤት መብት እንዲፈጠርላቸውና እንዲያለሟቸውና እንዲያስተዳድሯቸው መረጃው ተደራጅቶ ተሰጥቷቸዋል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻ የምታስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ ወይኒቱ፡-** ከተማው የምትመራበትና የመዋቅራዊ ፕላን በአግባቡ እንዲተገበር ከተማችን አዲስ አበባ እንደ ስሟ አበባ እንድትሆን እንዲሁም በዘመናዊ ፕላን የምትመራና ስማርት ሲቲ እንድትሆን ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት ።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ወይኒቱ፡-** እኔም ከልብ አመሰግናለሁ።

## መስሪያ ቦታዎች ልማትና ስኬቶች

በክ/ከተማ አስተዳደሩ የልማትና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የመስሪያ ቦታዎች ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት አንዱ ሲሆን ጽ/ቤቱ የኢኮኖሚ ልማት እቅድ ማጠንጠኛ የሆነውን የስራ ዕድል ፈጠራ፣ ሊሆኑ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞችን የማልማት ተልዕኮ ለማሳካት በአዲስ መልክ የተደራጀ ተቋም ነው። ጽ/ቤቱ የዘርፉን እድገት ያማከለ ተጨባጭ ጥናት ላይ የተመሰረተ እና መሰረተ ልማት የተሟላላት ደረጃውን የጠበቀ የመስሪያ ቦታ ገንብቶ በማስተላለፍ እና ፈጣን አገልግሎትን መሰረት ያደረገ ዘመናዊ አስተዳደርን በመዘርጋት የኢንተርፕራዞች እና አምራች ኢንዱስትሪዎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የማስቻል ተልእኮን ለማሳካት የተደራጀ ሲሆን ተልእኮውን ለማሳካትም ግልጽነት ፣ተጠያቂነት ፣ፍትሀዊነት ፣ቁርጠኝነት፣ ውጤታማነት፣ አጋርነት ፣ስራ ፈጠራን ማበረታታት እና ዘመናዊነት እሴቶች ላይ ተመስርቶ ይሰራል።

በዚሁ መሰረት በመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት ለማከናወን ከአቀድናቸዉ ዋና ዋና ተግባራት ዉስጥ አንዱ ስታንዳርዱን የጠበቀ የመስሪያ ቦታ በማልማት ለስራ ፈላጊ ዜጎች ማስተላለፍ ሲሆን በዚህም 60,000,000 በጀት የ3 ሼዶች ግንባታ 30 ሱቆች ግንባታ እንዲሁም የ2 ህንጻዎች ጥገና የሚሆን በጀት ማስያዝ የተቻለ ሲሆን መሰረተ ልማት ከማሟላት አንጻርም ለነባር እና አዲስ የመስሪያ ቦታዎች 7 የኤሌትሪክ ቆጣሪ ማስገባት ተችሏል። በሌላ መለኩ ያለንን ክፍት ቦታ በፍትሃዊነት ከማስተላለፍ አንጻር በዚህ ወርእንደ ክፍለ ከተማችን 100 ኢንተርፕራይዝና 218 አንቀሳቃሽ ተጠቃሚ ማድረግ ችለናል።የነባር ዉል እድሳት በተመለከተ 314 ኢፕራይዝ ዉል እድሳት ታቅዶ 314 የተከናወነ ሲሆን።

በክ/ከተማችን የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግና ለማረጋገጥ ከጥቃቅን ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ኢንደስትሪዎችን በመደገፍ ዘርፉ ስራ ለሌላቸው ወጣቶችና ሴቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣

የስራ ስምሪት እንዲሳለጥና የኢንዱስትሪ ሰላም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መንግስታዊ ድጋፍችን ማለትም የመስሪያ ቦታዎች ገንብቶ በማስተላለፍ በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፣አምራች ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካትና ወደ ውጪም ምርቶቻቸውን በመላክ ለኢኮኖሚው እድገት አስተዋፅኦ ከማበርከታቸውም በላይ ገበያውን የማረጋጋትና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ሂደት ውስጥ አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡



**ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ**
**የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ሀላፊ**

ክፍለ ከተማዉ ካሉት 27 መስሪያ ቦታዎች ውስጥ እድሳትና ጥገና በማድረግ በምንሰራቸው ስራዎች ውጤታማ እንድንሆን የሚያስችሉ ስራዎችን ሰርተናል፡፡ጥገና የሚያስፈልጋቸውን 2 ህንጻዎችና 25 ሼዶችን በጉዳት ዓይነትና መጠን በጥናት በመለየትና በመጠገን የመስሪያ ቦታዎች አቅርቦት እንዲሻሻል አድርገናል፡፡

ለነባርና ለአዲስ መስሪያ ቦታዎች 1 ትራንስፎርመር፣15 ኤሌክትሪክ ቆጣሪ እንዲሟላላቸው በማድረግ የተሻለ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው አድርገናል፡፡20 የመስሪያ ቦታዎችን የመሰረተ ልማት በማሟላት ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡



የሼድ ጥገና ሲካሄድ




ትራንስፎርመር እና ቆጣሪ ሲገጠም

ሌላው በመስሪያ ቦታዎች በትኩረት ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ አዲስ ለሚገነቡ የመስሪያ ቦታዎች የቦታ መረጣን የተመለከተ ስራ ሲሆን ከወረዳዎችና መሬት ልማት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር 900 ካሬ ሜትር የለማ ቦታን በመለየት ለሚፈለገው ዓላማ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል፡ ፡ወረዳዎችን ክፍለ ከተማው የስራ ዕድል ፈጠራንና ጸጋ ልየታ ላይ ተባብሮ በመስራት ውጤታማ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በ2018 በጀት ዓመት 3 ለኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታ የሚሆን ሼድ እና 45 ሱቆች በመገንባት ለአገልግሎት ፈላጊዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችሉ ስራዎችን ሰርተናል፡፡ከዚህ በተጨማሪም አዲስና ነባር ቦታ ላይ በሚገነቡ መስሪያ ቦታዎች ለ119 ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች፤ለ477 አንቀሳቃሾች 3443 ካሬ ሜትር ቦታ 100% በኪራይ ውል እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡አዲስ የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ ለሆኑ ለ119 ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ውል በመስጠት የተሻለ አፈፃፀም እንዲመዘገብ የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በ2018 በጀት ዓመት ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ ሴቶችን፣ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ላለባቸው አካላት፣አካል ጉዳተኞችንና ከስደት ተመላሾችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ ተግባር ሲሆን በዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በስራ ዕድል ላይ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የኢንተርፕርይዞች እና አምርች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ዉል በማደስ ገቢ እንዲሰበሰብ በማድረግ እና የሚታዩ ህገ ወጥ ድርጊቶች ላይ እርምጃ በመዉሰድ ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ከመዘርጋትም ባለፈ የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎችን በወቅቱ ውል በማደስ፣ የመስሪያ ቦታ ኪራይ እንዲከፍሉ ድጋፍ በማድረግና የቆይታ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁትን በማስለቀቅ የመስሪያ ቦታዎችን የማስተዳደር ስራዎችን በመስራት የመንግስትን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በማድረግ ጽ/ቤቱ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በመስራት ለ180 ኢንተርፕራይዞች በዉላቸዉ መሰረት በወቅቱ ኪራይ እየከፈሉ መሆናቸዉን በማረጋገጥ መንግስት አስፈላጊውን ገቢ እንዲያገኝ እየሰራን እንገኛለን፡፡

## የገበያ ማረጋጋትና የህብረት ስራ ማህበራ ሚና

የህብረተሰባችንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንፃር የህብረት ስራ ማህበራት ሚና ዘመናትን የተሻገረና የማይተካ ፋይዳ ያለው ነው፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በአለም አቀፍና በሀገራዊ ምጣኔ-ሀብታዊ ለውጦች ሳቢያ እየተስተዋለ ያለውን የኑሮ ውድነትና

የገበያ አለመረጋጋት ለመቋቋም፣ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት የህዝብ አለኝታነታቸውን በተግባር እያረጋገጡ ይገኛሉ። የልደታ ክፍለ ከተማ የህብረት ስራ ጽ/ ቤትም ማህበራቱ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር ውጤታማ እንዲሆኑና የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት ፍላጎት ማሟላት እንዲችሉ ዘርፈ-ብዙ የድጋፍ፣ የክትትልና የቁጥጥር ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። በመሆኑም የዝግጅት ክፍላችን ከልደታ ክ/ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ባዬ ባይሌ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርጓል በንባብ ተከታተሉን።



**አቶ ባዬ ባይሌ**
**የህብረት ስራ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የህብረት ስራ ማህበራት ህብረተሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ እና ያላቸው ፍይዳ ምንድን ነዉ?

**አቶ ባዬ፡-** የሸማች የህብረት ስራ ማህበራት የኑሮ ውድነትን በማቃለል ረገድ መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ያቀርባሉ።የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት (Consumer Cooperative Societies) ለአንድ ህብረተሰብ፣ በተለይም ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ያላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው።

እነዚህ ማህበራት በትርፍ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ የአባላቶቻቸውንና የሰፊውን ህብረተሰብ የኑሮ ጫና ማቃለልን አላማ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት ናቸው። በመሆኑም ዋና ዋና ጠቀሜታዎቻቸው እና ፋይዳዎቻቸው

**1.** የገበያ መረጋጋትን መፍጠር (Market Stabilization) የኑሮ ውድነትን መከላከል፡- መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎችን (እንደ ዘይት፣ ስኳር፣ ዱቄት፣ ሩዝ ወዘተ) በቀጥታ ከአምራቾች ወይም ከአስመጪዎች በማስገባት ያለ አላስፈላጊ መካከለኛ ነጋዴዎች (middlemen) ለህብረተሰቡ ያቀርባሉ። ይህም የዋጋ ንረትን ለመግታትና ገበያን ለማረጋጋት ትልቅ ሚና ይጫወታል።
አርቴፊሻል እጥረትን መዋጋት፡- አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች እቃዎችን በማከማቸት (ሆርዲንግ) የሚያደርሱትን የገበያ መዛባትና አርቴፊሻል የእቃ እጥረትን ይከላከላሉ።

**2.** ጥራትና ተመጣጣኝ ዋጋን ማረጋገጥ የአቅርቦት ጥራት፡- ማህበራቱ ለትርፍ ብቻ ስለማይሮጡ ለህብረተሰቡ የሚቀርቡት ምርቶች ጥራታቸው የተጠበቀ፣ ለአጠቃቀም ጤናማና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ፍትሃዊ ዋጋ፡- ምርቶችን በጅምላ ስለሚገዙና አነስተኛ የትርፍ ህዳግ (profit margin) ስለሚጠቀሙ፣ በችርቻሮ ገበያ ላይ ካለው ዋጋ በእጅጉ ባነሰና ፍትሃዊ በሆነ ዋጋ ለተጠቃሚው ያርሳሉ።

**3.** ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህን ማስፈን ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል፡- ከማህበሩ ስራዎች የሚገኘው ትርፍ (Surplus) በአባላቱ መካከል በገዙት ልክ (Patronage refund) ወይም በጋራ ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ እንዲውል ይደረጋል። ይህም ገንዘብ በጥቂት ግለሰቦች እጅ ከመከማቸት ይልቅ ወደ ህብረተሰቡ እንዲመለስ ያደርጋል። የዴሞክራሲያዊ አሰራር ልምድ፡- ማህበራቱ "አንድ አባል አንድ ድምጽ" በሚለው መርህ ስለሚመሩ፣ ህብረተሰቡ በጋራ የመወሰን፣ የመወያየትና ተቋማትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የማስተዳደር ባህልን እንዲያዳብር ይረዳሉ።

**4.** ለአካባቢ አምራቾች የገበያ እድል መፍጠር የቀጥታ ትስስር (Value Chain Supply)፡- ከአካባቢው አምራቾች (ለምሳሌ ከግብርና ምርት ማህበራት) ምርቶችን በቀጥታ በመግዛት ለአምራቹ አስተማማኝ ገበያ፣ ለሸማቹ ደግሞ ትኩስና ርካሽ ምርት ያቀርባሉ።ይህም የገጠርና የከተማን ኢኮኖሚ በጤናማ መንገድ ያገናኛል። የቁጠባ ባህልን ማሳደግ፡- ህብረተሰቡ የሚፈልገውን እቃ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ የዕለት ተዕለት ወጪውን እንዲቀንስና ከተረፈው ገቢ ላይ እንዲቆጥብ ያበረታታል። በአባልነት የሚገቡ ዜጎችም በየጊዜው እጣዎችን (Shares) በመግዛት የረጅም ጊዜ ቁጠባ እንዲኖራቸው ያደርጋል። የገንዘብ ቁጠባ ማህበራት ደካማ የፋይናንስ አቅም ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (በተለይ ሴቶችና ወጣቶች) የብድር አገልግሎት አግኝተው የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ ያደርጋሉ።

በጠቃላይ፤ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት የአንድ ህብረተሰብ የኢኮኖሚ ጋሻ ናቸው። በተለይም የገበያ አለመረጋጋትና የኑሮ ውድነት በሚፈታተንበት ወቅት፣ የመንግስትን

የልማትና የገበያ ማረጋጋት ፖሊሲዎችን መሬት ለማውረድና የዜጎችን የመግዛት አቅም ለመጠበቅ የማይተካ ፋይዳ አላቸው።

**ልደታ ፋና ፡-** የህብረት ስራ ማህበራት የኑሮ ውድነቱን ከመቀነስ እና የገቢያ ማረጋጋት ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

**አቶ ባዬ፡-** የህብረት ስራ ማህበራት የህብረተሰቡን የኑሮ ውድነት በመቀነስ እና ገበያን በማረጋጋት ረገድ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ እጅግ ከፍተኛ ነው። የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት (Consumer Cooperative Societies) የኑሮ ውድነትን በመዋጋት እና የገበያ አለመረጋጋትን በማስተካከል ረገድ የግንባር ቀደምትነት ሚና እየተወጡ ይገኛል ። የእነዚህ ማህበራት ዋነኛ መለያ ባህሪ እንደ መደበኛ ነጋዴዎች "ከፍተኛ ትርፍ ማጋበስን" ሳይሆን፣ የአባላቶቻቸውን እና የሰፊውን ህብረተሰብ "መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላትን" አላማ ማድረጋቸው ነው። የሸማቾች ማህበራት የኑሮ ውድነቱን ከመቀነስ እና ገበያን ከማረጋጋት አንጻር ያላቸው ፋይዳ እና ጠቀሜታ በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ይገለፃል፡- የአቅርቦት ሰንሰለትን ማሳጠር እና (ደላሎችን) ማስወገድ ምርቶችን በቀጥታ ከአምራች እና ዩንኖች ጋር ትስስር በመፍጠር በገበያ ላይ የሚታየውን ሰው ሰራሽ የዋጋ ጭማሪ በመግታት እና ምርቶችን በቀጥታ ለሸማች ማህበረሰቦች በማቅርብ ፍላጎት እና አቅርቦትን የማሳለጥ ስራዎች እየተሰራ ይገኛል። በተለይም በ2018 በጀት አመት የህብረት ስራ ማህበራትን ሪፎርም ስራዎች በማጠናከር እና ማህበራትን ምርት የማቅረብ እና ተደራሽነትን በማስፋት በርካታ ስራዎችን መስራት የተቻለ ሲሆን ከ118 በላይ የገቢ ማስገኛ ተቋማትን በማስለቀቅ ከ93 በላይ ተቋማትን በማዘመን የምርት አቅርቦትን በማሳደግ የምርት ተደራሽነትን እና የዋጋ ተመጣጣንነትን የማሳለጥ

ስራዎችን መስራት ተችሏል፡፡ በተለይም በበጀት አመቱ የምርት አቅርቦትን ለማሳደግ የሚያስችል ስራዎች በመስራት ሸማች ማህበራት በኩል የሰብል ምርቶች ፤የኢንዱትሪ ምርቶችን ፤የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን እና እትክልትና ፍራፍሬ ውጤቶችን በቀጥታ ለህብረትሰቡ በመሸጫ ሱቆች ላይ ፤በሱፐር ማርኬት ፤በገቢያ ማህከል ፤ወፍጮ ቤቶች እና የሸማች ወፍጮ ቤቶች ላይ በተለይም በእሁድ ገቢያ ምርቶችን ይዞ በመውጣት አምራችና ሸ፣ማችን በቀጥታ በማገናኛት የኑሮ ውድነቱን የማረጋጋት ስራዎችን መስራት ተችለዋል፡፡ በተለይም የምርት አቅርቦትን ከማሳደግ ባሻገር እሴት በመጨመር በሸማች ማህበራት በኩል ከ7 በላይ የዳቦ መጋጋሪያ እና መሸጫ እና ከ12 የእንጀራ መጋገሪያ ማእከላትን በመገንባት እና ምርቶችን በማምረት በተመጣጣጣኝ ዋጋ ለህብረትሰቡ እየቀረበ ይገኛል፡፡ በተለይም በበጀት አምቱ የምርት እጥረት እንዳያጋጥም በሸማች ማህበራት በኩል 70 ሚሌን ብር በላይ የተዘዋዋሪ ፍንድ ድጋፍ በማድረግ የምርት አቅርቦቱን የማሳደግ ስራዎች መስራት ተችሏል፡፡ የዋጋ ቅናሽ፦ የሸማች ማህበራት ምርቶችን በቀጥታ ከአምራች የህብረት ስራ ማህበራት፣ ከዩኒየኖች ወይም ከፋብሪካዎች በጅምላ ይረከባሉ። በመሆኑም የሚቀርቡ ምርቶች ከነጻ ገቢያው ከ5% እስከ 25% ድርስ ቅናሽ በማድረግ በቀጥታ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ይህ አሰራር አላስፈላጊ የደላላ ትርፍን ስለሚያስቀር፣ ምርቶች እጅግ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ ያደርጋል። ሰው ሰራሽ የእቃ እጥረትን እና የዋጋ ማጭበርበርን (Speculative Pricing) መከላከል ገበያን ማመጣጠን፦ የግል ነጋዴዎች በተለያዩ ወቅቶች (ለምሳሌ በበዓላት ወቅት ወይም የምርት እጥረት አለ በተባለበት ጊዜ) እቃዎችን በማከማቸት (Hoarding) የዋጋ ጭማሪ ሲያደርጉ፣ የሸማች ማህበራት እቃዎችን በቋሚና ህጋዊ ዋጋ ለህዝብ ያቀርባሉ። የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ለህብረተሰቡ “የኑሮ ጋሻ” ናቸው። በገበያው ውስጥ ነፃ ውድድር እንዲኖር በማድረግ፣ የትርፍ ስግብግብነትን በመግታት እና የአቅርቦት እጥረትን በመቅረፍ የዜጎችን የዕለት ተዕለት የኑሮ ጫና በማቃለል ረገድ የማይተካ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ፋይዳ አላቸው።

**ልደታ ፋና ፡-** ኦዲት እና የኢንስፔክሽን ስረዎች በማድረግ የተገኘ ግኝት እና የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎች ምን ይመስላል?

**አቶ ባዬ፡-** በበጀት አመቱ ከ95 በላይ ሁሉንም የህብረት ስራ ማህበራት ኦዲት በማድረግ በየደረጃው ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል ስራዎችን መስራት የተቻለ ሲሆን እንዱሁም በበጀት አመቱ በድንገተኛ እና በመደበኛ ከ406 ጊዜ በላይ ማህበራቶችን ኢንስፔክስን በማድረግ ስራዎች መስራት የተቻለ ሲሆን 21 በላይ ማህበራቶችን ብቃት ምዘና የማድረግ ስራዎችን መስራት ተችለዋል፡፡ በመሆኑም በኢንስፐክሽን እና በኦዲት ስራዎች የታዩ ዋና ዋና ውስንነቶች የሂሳብ ሰነዶች አያያዝ ፤የገቢና ውጭ ሰነዶችን በተገቢው ያለመያዝ፤በአንዳንድ ማህበራት ዘንድ የሂሳብ መዛግብትን በወቅቱ አለመዘጋጋት፣የብድር አሰባሰብ መዛግየት፣እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መላላት እና ሂሳብ በወቅቱ አዘጋጁቶ አለማቅረብ እና በአንዳንድ ማህበራት ላይ ሂሳብ ጉድለቶች ውስንነቶች ፤ የውስጠ ደንብ መመሪያዎችን ጠብቆ ያለመስራት ፤የምዝገባ ፍቃድ እድሳት በወቅቱ ያለማደስ እንዲሁም በእቅድ ያለመመራት ውስንነቶች በአንዳንድ የማህበራት ላይ ታይተዋል ፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** በኢንስፔክሽን እና በኦዲት ግኝት ዙሪያ የተወሰዱ መፍትሄዎች ወይም እርምጃዎች ካሉ ቢገልጽልን?

**አቶ ባዬ፡-** በበጀት አመቱ ለማህበራት አመራሮች እና ሰራተኞች የተለያዩ የመመሪያ እና ደንቦች እና አሰራሮች ዙሪያ በቂ ስልጠናዎችን በመስጠት በድንገተኛ እና በመደበኛ የድገሃፍና ክትትል ስራዎችን በመስራት በቂ ግብረ መልስ በመስጠት በየጊዜው ያሉ ችግሮች እንዲታረሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተለይም ለማህበራት ህግና መመሪያ አሰራር በማክበር እንዲሰሩ ማድረግ የሚያስችል እና በሚያጋጥሙ የአሰራር ውስንነቶችን መነሻ በማድረግ 341 ለሚሆኑት የህግ ምክር አገልግሎት በመስጠት በአሰራር እና በህግ ዙሪያ ለ430 የግንዘቢ ማስጨበጫ በደንብና መመሪያ መሰረት እንዲሰሩ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በበጀት አመቱ የመጡ ተጨባጭ ውጤቶች ምን እንደሆኑ ቢገልፁልን?

**አቶ ባዬ፡-** በበጀት አመቱ በክፍለ ከተማችን ለሚገኙ ከ20 ሺ በላይ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዘቤ በመፍጠር ከ10 ማህበራት በበላይ በማደራጀት 1700 በላይ ማህበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን 9000 በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ ነባር ማህበራት አባል በመሆ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፍትዊ ተጠቃሚነትን ማረጋጋጥ ተችሏል፡፡ የተደራጁ ማህበራትን በማጠናከር እና ድጋፍና ክትትል በማድረግ ከ76,291,409 ብር በላይ ካፒታላቸውን በማሳደግ 76,765,981 ብር በህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ ማህበረሰብ ክፍሎች የትርፍ ክፍፍል በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን መረጋገጥ ተችልዋል፡፡በህብረት ስራ ማህበራት በማስተባባር ለ650 በላይ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከ118 በላይ የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ከሁተኛ ወገን በማስለቀቅ የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት የሚያስችል አቅርቦት ማሳደግ እና አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ የሚያስችል 93 ተቋማት በላይ በማዘመን ወደተግማር የማስገባት ስራዎችን መስራት የተቻለ ሲሆን በተለይም የምርት አቅርቦት ተደራሽንን ማስፋት የሚያስችል ስራዎችን መስራት የተቻለ ሲሆን ከ36 በላይ የመሸጫ ሱቆች 112 ዘመናዊ ሱፐር ማርኬቶች ፤12 ወፍጮ ቤቶችን 1 ዘመናዊ የገቢያ ማእከል በመገንባት ወደስራ የማስገባት ፤ከ30 በላይ ስጋ ቤቶች፤24 የህዝብ መዝናኛ ተቋማቶች እና 11 የአትክልት መሸጫ ቦታዎችን እንዲሁም 11 የእሁድ ገበያ መዳረሻዎች ላይ ምርቶችን የማዳራስ ስራዎች እተሰራ ሲሆን በተጨማሪም እሴት የተጨመረባቸውን ምረቶችን ከ7 በላይ ዳቦ ቤቶችን እና 11 የእንጀራ መጋጋሪያ ማእከሎችን በመገንባት እና ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህበረትሰቡ ተደራሹ በማድረግ የኑሮ ውድነቱን የማረጋጋት ስራ መስራት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ባዬ፡-** የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት የህዝብ ሀብት በመሆናቸው ሁላችንም ልንጠብቃቸውና ልናጠናክራቸው ይገባል። እነዚህ ማህበራት ተጠናክረው መውጣትና ዘላቂ መሆን የሚችሉት የአባላትና የህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ሲታከልበት ብቻ በመሆኑ፣ ሸማቹ ማህበረሰብ የማህበራቱ እውነተኛ ባለቤት በመሆን በአሰራራቸው ላይ የክትትልና የቁጥጥር እገዛ ሊያደርግ ይገባል። በተመሳሳይ መልኩ የማህበራቱ አመራርም የተጣለበትን ኃላፊነት ተገንዝቦ በታማኝነትና በቅንነት ህዝብን ማገልገል ይኖርበታል። መንግስትም ማህበራቱ ያሉባቸውን የስራ ቦታና የካፒታል እጥረቶች በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚያደርገውን ሁለንተናዊ ድጋፍና ክትትል አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

## ተቋማዊ አቅም ግንባታ ለብልጽግና

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ፐ/ሰ/የሰ/ሀብ/ል/ጽ/ቤት አመራሩንና የፈፃሚው የአመለካከትና የክህሎት ማነቆዎችን በመፍታት የተሻለ አገልግሎት አሰጣጥ ለማስፈን በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የተደራጀና የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል። የአገልግሎት አሰጣጥ ተቋማትና ፈጻሚዎች ምዘና በማካሄድ የዕውቅናና ሽልማት ስነ-ስርዓት በማዘጋጀት ለተቋማት እና ለፈጻሚዎች እውቅና መስጠት ተችሏል። በዕቅድ እና አፈጻጸም ዙሪያ ከዘርፉ አመራሮች፣ አስተባባሪ፣ ፈጻሚዎች፣ ተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ጋር  የጋራ ማድረግ ተችሏል። የአቅመ ደካማ ቤት ማደስ ተችሏል። ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ማዘጋጀት ጽ/ቤቶች ያሉበትን ደረጃ ማመላከት ተችሏል። የባለ ጉዳይ ቀን በተከታታይ ዕሮብና አርብ ምልከታ በማድረግ ተሻለ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ የውጪና ውስጥ ተገልጋይ እርካታ ደሰሳ ጥናት  ደሰሳ ጥናት ማድረግ ሰነድ ማዘጋጀት ተችሏል። የመማክርት ጉባኤ ያቋቋሙ ጽ/ቤቶች ወደ ተግባር እንዲገቡ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያደራጁ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል። ተቋማትና ፈጻሚዎች ምዘና በማካሄድ የዕውቅናና ሽልማት ስነ ስርዓት በማዘጋጀት ለተቋማት እና ለፈጻሚዎች እውቅና መስጠት ተችሏል። በወርቃማ ሰኞ የእውቀት ሽግግር ፕሮግራም ላይ በተለያዩ ርዕሶች እርስ በእርስ መማማር ተችሏል። የሰው ሃብት ስምሪት ስራዎችን በስፋት መስራት ተችሏል። የወረዳ አጠቃላይ የግብዓት መረጃ እና ክፍተት በመለየት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ተችሏል። ከሰው ሃብት ጋር በተገናኘ የክትትልና ድጋፍና ኦዲት ስራ ተከናውኗል፡፡ ቅሬታን በአግባቡ ተቀብሎ ማስተናገድ መቀነስ ተችሏል። በጠቅላላ ካውንስልና በየአደረጃጀቱ ወቅቱን ጠብቆ ስራዎችን የመገምገምና አቅጣጫ የማስቀመጥ ስራ መስራት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ የመፅሔት ዝግጅት ክፍላችን ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ወ/ሮ መቅደስ ያደታ ጋር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ!

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን።
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** እኔም እንግዳችሁ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።



**ወ/ሮ መቅደስ ያደታ**
**የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የአስተዳደሩ አገልግሎት አሰጣጥ ከተገልጋዩ እርካታ አኳያ ያለበት ሁኔታ ቢገልፁልን?
**ወ/ሮ መቅደስ ያደታ፡-** አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል እርካታን ማሳደግ አኳያ አገልግልቶችን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 100% ማከናወን ተችሏል።  በጽ/ቤት ደረጃ 6 ዋናና አገልግሎቶች ያሉ ሲሆን 3 በስታንዳርድ እና 3 ከስታንዳርድ በላይ የሚከናወኑ ናቸው። አገልግሎትን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ በተወሰኑ ጽ/ቤቶች ተገልጋዩ ባለበት (ኦንላይን) ተደራሽ የተደረገ አገልግሎት እና የተገኘ ውጤት በዝርዝር  ለማስቀመጥ  እንደ ክፍለ ከተማችን ተገልጋዮች በቀላሉ ባለበት ቦታ አገልግሎት እንዲያገኝ አስችሏል። እንዲሁም በጽ/ቤቱ በዌብ ሳይት፣ በፌስ ቡክ፣ በቴሌግራም፣ በኤልዲ፣ በስቲከር በመለጠፍ፣ በብሮሸር እንዲሁም በተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ግልጽ ማድረግ ተችሏል። በዚህም የግልጽነት አሰራርን ለማጎልመስ አስችሏል፡፡ የአገልጋዩ ማንነት መለያዎች አቅጣጫ ጠቋሚዎች በአጠቃላይ ሀሁ ስራዎች አፈጻጸም ያለበት ደረጃ እና ውጤት በተመለከተ በተለይም በባለጉዳይ ቀን ምልከታ በማድረግ የሀሁ ስራዎች እንዲተገበሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ምን ተሰርቷል?
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** ጽ/ቤታችን ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ቡድን ጋር በመተባበር የአስተዳደር ዌብ ሳይት ማበልጸግ የቻለ ሲሆን ዌብ ሳይቱ ዳይናሚክ እንዲሆን እና ወደ አገልግሎት እንዲገባ ተደርጓል። ዌብ ሳይቱ በዋናነት የሚሰጠው አገልግሎት በየወሩ ስራዎች፡ ዜናዎች፣ የጽ/ቤት አገልግሎት፣ ራዕይ ተልዕኮና እሴት፣ የአስተያየት መስጫ እና ኦንላይን ቅጥር፣ በድምጽ ቅሬታ መቀበል እንዲሁም ዶክመንቴሽን መጫን እንዲያስች ተደረጎ የበለጸገ ነው። የጽ/ቤት አፈጻጸም ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ አዳዲስ ፈጠራዎች  እንዲተገበሩ ለማድረግ አቅደን ማከናወን ችለናል። የተፈጠሩ አዳዲስ ስራዎች እንዲቀመሩ በማድረግና በተቋም ደረጃ በመግባባት ለስራ ክፍሎች የማስፋት ስራ ማከናወን ተችሏል። አዳዲስ ስራዎች በመተግበራቸው የተገኙ ተጨባጭ ውጤቶች ማስፋት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** የስራ ቦታን ምቹ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን?
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር አገልግሎቱን ማሻሻል ተቋማዊ ግንባታ አስመልክቶ በተቋሙ ምቹ መስተንግዶ ስርዓት በመዘርጋት እንግልት እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል። በክፍለ ከተማ የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ የህጻናት ማቆያ፣ የሸማቾች ሱቅ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣ የጽ/ቤቶች ሌይአውት አገልግሎት ለመስጠት ምቹ እንዲሆን ተደጓል። በወረዳ እና በት/ቤት ደረጃ በተመሳሳያ የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ የህጻናት ማቆያ፣ የሸማቾች ሱቅ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የስፖርት ጅምናዚየም በማዘጋጀት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተገልጋዮችም የአገልግሎት ተደራሽነት የማረጋገጥ ስራ ሰርተናል።

**ልደታ ፋና፡-** አጠቃላይ ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን።
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** እኔም በጽ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።



አቶ ይልማ ተረፈ
የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት ሃላፊ

## የመልካም አስተዳደር እምርታ

መልካም አስተዳደር የማንኛውም ሀገር የልማት መሠረት ነው። በዚህ የሚገኙ ደግሞ ዋና መሠረቶች የተጠቃሚ አገልግሎት፣ ታማኝነት፣ ተጠያቂነትና በሕዝብ ፊት ግልጽ መሆን ናቸው። አቤቱታና ቅሬታ ተቋም የህዝብ ድምፅን ለመስማት፣ የሚነሱ ችግርና አስተያየቶችን በፍትሀዊ መንገድ ለመፍታት እና የመንግስት አገልግሎትን በሕዝብ ፊት እንዲሆን ለማረጋገጥ የሚያገለግል በጣም አስፈላጊ መሣሪያ ነው። እንዲሁም ይህ ተቋም በህዝብ እና በመንግስት መካከል የእርስ በርስ እምነትን ለማጠናከር ይረዳል፤ በህዝብ የተነሱ ቅሬታዎችን በተስፋ እና በፍትህ መልኩ ሲያወጣ የመንግስት አስተዳደር በተጠቃሚ እና ታማኝ መልኩ እንዲቀጥል ያስችላል።

በመልካም አስተዳደር ምክንያትም ለብዙ አመታት ሲነሱ የነበሩ ምላሽ ያልተሰጠባቸዉ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በራሱ በመልካም አስተዳደር አቤቱታና ቅሬታ ጽ/ቤት በኩል እራሱን የቻለ ባለድርሻ አካል በማቋቋም መፍትሄ እንዲሰጥ ምላሽ እንዲያገኝም ጭምር ትልቅ ስራዎችና ለዉጦች እንዲመጡ ምክንያት መሆን ችሏል። ይሄን እንደመነሻ ያነሳነዉ ታዲያ በያዝነዉ በጀት አመት እንደ ልደታ ክፍለ ከተማ መልካም አስተዳደር አቤቱታና ቅሬታ ጽ/ቤት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን በማየት ከሚመለከተዉ አካል ጋር ዉጤታማ ስራ መስራት እንደቻለና እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችም ምን እንደሆኑ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ጋር ቆይታ በማድረግ ለእናንተ ለዉድ አንባቢያን ለማቅረብ ነዉ እናንተ ደግሞ በንባብ አብራችሁን እንስድትቆዩ ጋብዘናል መልካም ንባብ!

**ልደታ ፋና፡-**የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት የተቋቋመበት ዋና ዓላማ ምንድነዉ?

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-** ጽ/ቤታችን የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ ከህብረተሰቡ ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ፍትሃዊ ፣ ቀልጣፋና ፈጣን ምላሽ መስጠት ነው። ይህም ማለት ማንኛዉም ህጋዊ አካል ተቋማችን ድረስ መጥቶ ቅሬታ አቤቱታ ወይም በመልካም አስተዳደር ያቀረብኩት ጥያቄ ምላሽ አላገኘም ብሎ ቅሬታ ቢያቀርብ ጉዳዩን ሚዛናዊ በማድረግ መፍትሄ መስጠት ወይም ቅሬታዉን መፍታት ዓላማችን ነዉ። እዚህ ላይ ዋና ግብ አድርገን የምንወስደዉ በነቃ የህብረተሰብ ተሳትፎ የአገልግሎት አሰጣጣችንን በማሻሻል የህብረተሰቡን እርካታ ማሳደግና ችግርን ከምንጩ መቅረፍ አልያም መቀነስ ሲሆን ከዓላማዉ ጋር ተያያዥነት አለዉ ማለት ነዉ።

**ልደታ ፋና፡-** መልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት በዋናነት የሚያከናዉናቸዉ ተግባራቶች ምንድናቸዉ?

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-**የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት፤ የተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር፤ ውጤትን መሰረት ያደረገ የተጠሪ ተቋማት፣ የሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ የሱፐርቪዥንና ኢንስፔክሽን ስራዎችን በማከናወን፤ ቅሬታና አቤቱታዎችን በመቀነስ፣ መልካም አስተደደርን በማስፈንና አገልግሎት አሰጣጡን ፍትሃዊ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ እና ለከተማው ስትራቴጂክ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት የከተማውን ህብረተሰብ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው።

የክ/ከተማ አስተዳደሩ ለነዋሪው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በእኩልነት፣ በግልጽነትና በፍትሃዊነት መርህ መሠረት ለመስጠት እንዲችል ለህብረተሰቡ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት ተቋማዊ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት በማጎልበት እና ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በመቀነስ የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ በተቀናጀ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የረካ ሕብረተሰብ መፍጠር ።

**ልደታ ፋና፡-**በያዝነዉ በጀት አመት ምን ያክል ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ቀርበዉ ተፈተዋል?

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-** በያዝነዉ በጀት አመት በክፍለ ከተማዉ በአንድ ማእከል አገልግሎት በኩል የቀረቡ ቅሬታዎች አቤቱታዎች ብዛት 536 ሲሆን በወረዳ ደረጃ 1283 ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች ቀርበዋል ይህ ልዩነት የሚሳየው በክፍለ ከተማ አንድ ማእከል በከፍተኛ ደረጃ ቅሬታና አቤቱታ መቀነሱን ያሳያል።

### አንድ ማዕከል አገልግሎት ቅሬታ እንዲቀንስ ምክንያቶች

- በአንድ ማዕከል አገልግሎት ረቡዕ እና አርብ አስተዳደሩ ቅሬታ ከሚበዛባቸው ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን የህብረተሰቡን ቅሬታ በአካል ማዳመጥና መፍታት በመቻሉ።

- ነዋሪዎች በተደጋጋሚ የቤት ይሰጠኝ ጥያቄ በማቅረባቸው ልየታ ተደርጎ ወረፋ እንዲይዙ መደረጉ።

- የባለጉዳይን ቀን ለባለጉዳይ ብቻ ከ/ክተማ ሴክተር ጽ/ቤቶች እስከ ወረዳ ድረስ ተግባራዊ በመደረጉ።

- የወረዳ መልካም አስተዳደርና አቤቱታ ዘርፍ የአንደኛ ሩብ ዓመትና የሁለተኛ ሩብ ዓመት እንዲሁም የሶስተኛ ሩብ አመት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ጠንካራ ጎናቸውን እንዲያስቀጥሉ በክፍተት የተጠቀሱትን እንዲያሻሽሉ በማድረግ አፈጻጸማቸውን እንዲያሻሽሉ ተደርጓል

- የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ፣ ምርመራ፣ አወሳሰን እና የተጠያቂነትሥርዓት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 143/2015 ዓ.ም ዙሪያ ለወረዳ መልካም አስተዳደርና አቤቱታ ዘርፍና ለዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ኃላፊ እና ለፎካል ፐርሰኖች ግንዛቤ በመፍጠር ቅሬታና አቤቱታዎች እንዴት መቀበል እና መፍታት እንዳለባቸው አቅጣጫ ተሰቷል፣

**ልደታ ፋና፡-** በመደበኛ የቀረቡ ቅሬታና አቤቱታ ምን ያክል ናቸዉ?

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-** መደበኛ ቅሬታን ስንመለከት በያዝነዉ በጀት አመት የቀረበው መደበኛ ቅሬታ እና አቤቱ 27 ነው፡፡ይህ የሚያሳየው ከባለፈዉ አመት አንጻር ከቀረቡት ቅሬታ አቤቱታዎች በያዝነዉ በጀት አመት ከቀረበው ጋር በ115% መቀነሱን ያሳያል ፡፡

በሌላ በኩል ግን በመደበኛ በቅጽ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በከፍተኛ መቀነሱን ያሳያል ለዚህም ምክንያቱ መደበኛ ቅሬታ አቀራረብን ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ ባሉ ባለሙያዎች ለባለጉያዮች በመደበኛ ሊታዩ የሚችሉ እና ሊታዩ የማይችሉ ቅሬታና አቤቱታዎችን ላይ ግንዛቤ መፍጠር በመቻሉ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ጭምር በመታገዛ በመደበኛ ቅሬታ አቅራረብ ዙሪያ የግንዛቤ ስርጸት ስራ በመሰራቱ ነው ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራራችሁ ምን ይመስላል?

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-** የባለድርሻ አካላት ተሳቶ በየአአመቱ የተሻለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለምሳሌ የሲቪክ ማህበራት ተሳትፎን ስናይ ለመልካም አስተዳደር መስፈንና ለሰላም ግንባታ ያላቸዉ አስተዋጽኦ ትልቅ ነዉ፡፡ በ2018 በጀት አመት ሲቪክ ማህበራትን የማጠናከር ስራ የተሰራ ሲሆን በእቅድ ኦርንቴሽን ከማሳተፍ ባሻገር በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ስራዎች አብሮ በትብብር ለመስራት ተደጋጋሚ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል ፡፡

- አጠቃላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሰራነዉ ስራ አስተዳደሩ "ችግርን ከምንጩ መቅረፍ" በሚል መርህ፣ የመልካም አስተዳደር እዳዎችን የመለየት ሥራን ከቢሮክራሲያዊ አሠራር አውጥቶ ወደ ሕዝባዊ ንቅናቄ ቀይሮታል፡፡

- ከታችኛው መዋቅር የተነሱ ጥያቄዎች፡- አመራሩ በየብሎኩ ድረስ በመውረድ ከሕዝብ ጋር ባደረገው ቀጥተኛ ውይይት 93 ዋና ዋና ችግሮች (57 በክፍለ ከተማ፣ 36 በወረዳ) ተለይተዋል፡፡

- በበጀት ዓመቱ አጋማሽ 47 ስር የሰደዱ ችግሮችን ለመፍታት ታቅዶ፣ በላቀ የሥራ ተነሳሽነት 56ቱን (119%) መፍታት ተችሏል፡፡ ይህ ስኬት አስተዳደሩ የሕዝብን ጥያቄ የመመለስ አቅሙን (Implementation Capacity) ያሳደገ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እነዚህ ሁሉ ስራዎች ስንሰራ የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት የነበራቸዉ ሚና የላቀ እንደነበር ያሳያል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎት አሰጣጣችሁ ምን ይመስላል?

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-** አገልግሎት አሰጣጡ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ ሰፊ ስራዎች ተጀምረዋል እየሰራንባቸዉ ያሉ የዘመኑ አሰራሮችም አሉን፡፡ በቀጣይ ግን ጊዜ ቆጣቢና የማህበረሰባችንን የአገልግሎት እርካታን ከፍ ለማድረግ የተጀመሩ ስራዎችን በማጠናቀቅ ዉጤታማ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነን፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጦት

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-** አሁን ፤ላይ ሀገራችን በተለያዩ ሰዉ ተኮርና ዘርፈ ብዙ የልማትና የአመለካከት ቀረጻ ላይ ትገኛለች በእዚህም ደግሞ በህዝባችን በኩል የተለያዩ ማጠናከሪያ ሀሳቦች አልያም ደግሞ ጥያቄዎች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ጉዳዮች እንደ አንድ የመንግስት ችግር ፈቺ ተቋም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የሚቀርቡ መልካምና የተለዩ ሀሳቦችን እንደ አመጣጣቸዉ በትኩረት በማየት መፍታት ይጠበቅብናል፡፡ማህበረሰቡም ያለዉን የትኛዉንም ቅሬታ አቤቱታ በህጉ መሰረት ማቅረብ ይችላል፡፡

ሌላዉ በየደረጃው የሚታዩት የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት በተደራጀ መንገድና በቁርጠኝነት ማሳካት ያስፈልጋል፡፡ አመራርና ፈጻሚ ተቀራርቦ በመስራት የክ/ከተማችን ገጽታ በመቀየር በ2018 ዓ.ም ልደታን ከፍ ለማድረግ በቁርጠኝነት መስራት ያስፈልጋል ፡፡

በተጨማሪም በወረዳና በክ/ከተማ በዕቅድና ከዕቅድ ውጪ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ውጤቱን በሰነድና በዶክመንተሪ በማጀብ አደራጅቶ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ አገልግሎት አሰጣጡንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመሆኑ የሚመጡ የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጥያቄዎችንም በጋራ የምንቀንስ መሆኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ አመሰግናለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** እኛም ለነበረን የቃለ መጠይቅ ጊዜ በዝግጅት ክፍሉ ስም በጣም እናመሰግናለን

**አቶ ይልማ ተረፈ፡-**እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ችግርን በቦታው የመፍታት ጥበብ

መንግስት የህብረተሰቡን የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄዎች በዘላቂነት ለመፍታት የተለያዩ አሰራሮችንና ፕሮግራሞችን በመተግበር እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህ ሂደት የመንግስት ተቋማት የልማት ስራዎችን በወቅቱ በማጠናቀቅ እና ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ናቸው፡፡

በልደታ ክፍለ ከተማም የህዝብን ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ የአገልግሎት፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች በስፋት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ልደታ ፋና በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ጢቂ ድሪባ ጋር በመወያየት የተቋሙን ተግባራት፣ የተገኙ ውጤቶች እና የወደፊት አቅጣጫዎች አስመልክቶ ያደረግነው ቆይታ እነሆ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመሪያ የዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ተልዕኮና ዋና ዋና ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-** ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት በስሩ በርካታ ተቋማትን ያቀፈና ሰፊ የሥራ ድርሻ ያለው ተቋም ነው፡፡ የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ አገልግሎት እንዲሰጥ፣ ተቋማት በቅንጅት እንዲሰሩ፣ የልማት ስራዎች በወቅቱ እንዲከናወኑ እና የህዝብ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ የማስተባበርና የክትትል ስራዎችን ያከናውናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በበጀት ዓመቱ ለህብረተሰቡ የተሰጡ አገልግሎቶችን እንዴት ይገልጻሉ?

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-** የህብረተሰቡን ፍላጎት ከግምት በማስገባት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ዘርፍ፣ በጸጥታ እና በመልካም አስተዳደር መስኮች ሰፊ ስራዎችን አከናውነናል፡፡ ይህም የህብረተሰቡን እርካታ ከማሳደግ ባሻገር በአስተዳደሩና በነዋሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት እያጠናከረ ይገኛል፡፡ ዛሬ ህብረተሰቡ ፍላጎቱን በቀጥታ የሚያቀርብበትና ምላሽ የሚያገኝበት ስርዓት ተፈጥሯል፡፡



**አቶ ጠቂ ድሪባ**
**የዋና ስራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** በመልካም አስተዳደር ዘርፍ የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ ጠቂ ድሪባ፡-** መልካም አስተዳደር የህብረተሰቡ ዋና ፍላጎት ነው። ስለዚህ የችግሮችን ምንጭ በመለየት እና ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት ላይ አተኩረን ሰርተናል። የህዝብ ቅሬታዎችን ለመቀበልና ለመፍታት የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅመናል። ከእነዚህ ውስጥ በተለይ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተጠቃሽ ነው።

**የልደታ ፋና፡-** አንድ ማዕከል አገልግሎት ምን አይነት ጥቅም አስገኝቷል?

**አቶ ጠቂ ድሪባ፡-** ይህ ፕሮግራም ረቡዕና አርብ በመደበኛነት ይካሄዳል። ነዋሪዎች ያለምንም እንግልት በቀጥታ ለሚመለከታቸው ተቋማት ጥያቄያቸውን ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት እንዲችሉ አድርጓል። ከዚህም በላይ በማዕከሉ የሚቀርቡ ጉዳዮች በቅርበት ተጠንተው ለመፍትሄ እንዲበቁ የአመራር ክትትል ይደረጋል።

**ልደታ ፋና፡-** ከህዝብ ጋር ያለውን ቅርርብ ለማጠናከር ምን ዓይነት አሰራር ተዘርግቷል?

**አቶ ጠቂ ድሪባ፡-** በቢሮ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ብቻ ሳይሆን ወደ ነዋሪዎች መኖሪያ በመውረድ ችግሮቻቸውን በቦታው እንረዳለን። ይህ አሰራር ችግሮች በፍጥነት እንዲፈቱ እና የህዝብ እምነት እንዲጠናከር አስችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በፋይናንስና በተቋማት ድጋፍ ረገድ ምን ስራዎች ተሰርተዋል?

**አቶ ጠቂ ድሪባ፡-** በስራችን ውስጥ የበጀትና የሰው ሃይል አስተዳደር ወሳኝ ነው። ተቋማት በካሽ ፍሎው መሰረት በጀታቸውን እንዲጠቀሙ፣ ክፍያዎች በወቅቱ እንዲፈጸሙ እና የግዥ ሂደቶች በቅልጥፍና እንዲከናወኑ በትኩረት ሰርተናል። ይህም የፋይናንስ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ከማጠናከሩ ባሻገር አገልግሎቶች ቀልጣፋ እንዲሆኑ አድርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** በካቢኔ ጉዳዮች ዙሪያ የተከናወኑ ስራዎችን እንዴት ይገልጻሉ?

**አቶ ጠቂ ድሪባ፡-** የክፍለ ከተማው ወቅታዊና መደበኛ ጉዳዮች በካቢኔ እንዲመከሩ እና ውሳኔ እንዲያገኙ አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ሰርተናል። በተለይ ከቤቶች፣ ከኮሪደር ልማት እና ከሌሎች የልማት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ የተለያዩ ውሳኔዎች እንዲወሰኑ እና አሰራሮች እንዲጠበቁ ትልቅ ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና፡-** በቀጣይ ምን ላይ ትኩረት ይሰጣሉ?

**አቶ ጠቂ ድሪባ፡-** በቀጣይ የህዝብ እርካታን የበለጠ ለማሳደግ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት፣ የልማት ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ እና ተቋማትን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ እንሰራለን። የህዝብ ተሳትፎን በማጎልበት ልደታን የተሻለ የአገልግሎትና የልማት ማዕከል ለማድረግ ቁርጠኞች ነን።

የልደታ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት የህዝብ ፍላጎትን ማዕከል ባደረገ አሰራር በመልካም አስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በፋይናንስ ግልጽነት እና በልማት ፕሮጀክቶች ቅንጅት ረገድ ጉልህ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። እንደ አቶ ጢቂ ድሪባ ገለጻ፣ የህዝብ ጥያቄን በወቅቱ መመለስ፣ የልማት ስራዎችን በቅልጥፍና ማስፈጸም እና ተቋማትን በቅንጅት ማስኬድ የተቋሙ ቀጣይ ትኩረት ሆኖ ይቀጥላል። ይህም ልደታን ለነዋሪዎቿ የተሻለ የአገልግሎትና የልማት ማዕከል ለማድረግ ጠንካራ መሰረት ይፈጥራል።

## የሠላሙ ዘብ

የከተማችንን እንዲሁም የክፍለ ከተማችንን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ ሌትተቀን ያለመታከት የህዝብ አለኝታ የሆነዉን የፖሊስ ሰራዊት እና ሌሎች የጸጥታ አካላትን በማሰማራት ዘርፈ ብዙ የጸጥታ ስራዎች እያስተባበረ ዜጎች ሰላማዊ እና የተረጋጋ ኑሮ እንዲመሩ ብሎም ሀገራዊ ልማት እንዲፋጠን የተቋቋመለትን አላማ ግብ ለማድረስ እየተጋ ይገኛል ።በመሆኑም ጽ/ቤቱ የተሰጠውን ተልእኮ ዋና ዋና ተግባራት አጠቃላይ አፈጻጸም ከሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ቶሎሳ መርጋ ጋር የመጽሔት ክፍላችን ቆይታ አድርጋለች። መልካም ንባብ!

**ልደታ ፋና፡-**በ2018 በጀት ዓመት በክፍለ ከተማችን ሰላምና ጸጥታን ለማስፈን የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት ምን ይመስሉ ነበር? እስካሁን ባለው ሂደት የታየው አጠቃላይ አፈጻጸምስ እንዴት ይገመገማል?

**አቶ ቶሎሳ፡-** “በ2018 በጀት ዓመት በልደታ ክፍለ ከተማ አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታን ለማስፈን ስትራቴጂካዊ ዕቅዶችን ነድፈን ወደ ስራ ገብተናል። ዋና ዋና ዕቅዶቻችን የወንጀል ስጋቶችን በቅድመ-መከላከል ስራዎች ማክሸፍ፣ የሕዝብ ተሳትፎን ማሳደግ፣ የጸጥታ አጋዥ ሀይሎችን ማጠናከርና ማብቃት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ ላይ ያተኩሩ ነበሩ። በ9 ወራት አፈጻጸማችን ስንገመግመው፣ ያቀድናቸውን ግቦች በከፍተኛ ደረጃ ማሳካት የቻልንበትና በክፍለ ከተማችን አስተማማኝ መረጋጋትን ያረጋገጥንበት ስኬታማ አፈጻጸም ተመዝግቧል። በተለይም ቅንጅታዊ አሰራራችንን በማጠናከራችንና በተሰሩ የቅድመ መከላከል ስራዎች ወንጀል ከአምናው ተመሳሳይ ግዜ ጋር ሲነፃፀር በ2017 522 ወንጀሎች ተፈፅመው የነበረ ሲሆን በዘንድሮ በጀት አመት 279 ወንጀሎች ተፈፅመዋል በዚህም ወንጀል በ243 እንዲቀንስ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በፐርሰንትም 46.5% የወንጀል ምጣኔ እንዲቀንስ ማድረግ ችለናል።



## አቶ ቶሎሳ መርጋ
### የሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** በዚህ በጀት ዓመት የህብረተሰቡን የሰላም ባለቤትነት ለማሳደግ ምን ያህል የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተዘጋጁ? ውጤታቸውስ ምን ይመስላል?

**አቶ ቶሎሳ፡-** የሰላም ዋናው ባለቤትና ጠባቂ ራሱ ሕብረተሰቡ በመሆኑ በዚህ በጀት ዓመት 'ሰላም ለሁሉም፣ ሁሉም ለሰላም' በሚል እሳቤ የሕዝቡን ግንዛቤ ለመፍጠር ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል። በበጀት አመቱ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ከነዋሪዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች እና ከነጋዴው ማህበረሰብ ጋር በአጠቃላይ ከ30 በላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን አዘጋጅተናል። በዚህም በድግግሞሽ 1,111,385 ነዋሪዎችን ማሳተፍ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም በሳምንት ሁለት ቀን ሀሙስና እሁድ በሁሉም ብሎኮች የማህበረሰብ አቀፍ የምክክር መድረኮችን በማካሄድ ህዝቡን የሰላም ባለቤት የማድረግ ስራ ተሰርቷል በዚህም በድግግሞሽ 786,864 የሚሆኑ አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል። የዚህ ስራ ትልቁ ውጤት ሕብረተሰቡ ስጋቶችን ቀድሞ የመጠቆምና በየአካባቢው ለሚታዩ አጠራጣሪ ነገሮች ፈጣን መረጃ የመስጠት ባህሉ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያድግ ተደርጓል።



**የህዝብ ውይይት ሲካሄድ**

**ልደታ ፋና፡-** በየወረዳዉ በየብሎኩ የሚገኙ የሰላም ሰራዊቶችና የጸጥታ መዋቅሮችን በማጠናከር ከማብቃት ረገድ ምን አዳዲስ ስራዎች ተሰሩ?

**አቶ ቶሎሳ፡-** "የሰላም ሰራዊት የሰላማችን የፊት መስመር ጠባቂ ነው። በዚህ ዓመት የሰላም ሰራዊት አደረጃጀታችንን ከማጠናከር አንፃር 2500 አዳዲስ የሰላም ሰራዊቶችን በሶስት ዙር የንድፈ ሀሳብና የመስክ ስልጠና በመስጠት የአካባቢያቸውን ፀጥታ እንዲያስጠብቁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህም የነበረንን 8035 የሰላም ሰራዊት ቁጥር ወደ 10,535 በማሳደግ የማጠናከር ስራ ተሰርቷል። ለሰላም ሰራዊት አባላት ስለ ወንጀል መከላከል ስልቶች፣ ስለ መረጃ አሰባሰብና ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር ስላለው ግንኙነት ተከታታይ ስልጠናዎችን ሰጥተናል። በአሁኑ ወቅት በየብሎኩ የምሽትና የቀን የሰላም ጥበቃ ስራዎች በባለቤትነት ስሜት እየመሩ ይገኛሉ፤ ይህም በየሰፈሩ የሚፈጸሙ ድንገተኛ ወንጀሎችን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል።"

**ልደታ ፋና፡-** የክፍለ ከተማችንን ሰላም ይበልጥ ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለመጠበቅ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን (ለምሳሌ የCCTV ካሜራዎች ተከላ) በማስፋፋት ረገድ በዚህ በጀት ዓመት ምን የታየ ለውጥ አለ?

**አቶ ቶሎሳ፡-** "ዘመናዊ ወንጀልን ለመከላከል ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። በዚህ በጀት ዓመት የክፍለ ከተማችንን የጸጥታ ቁጥጥር በቴክኖሎጂ ለማገዝ ትልቅ እርምጃ ተራምደናል። ከባለሀብቶች፣ ከነጋዴዎችና ከነዋሪው ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት በወንጀል ስጋት ባለባቸው አካባቢዎችና በዋና ዋና መንገዶች ላይ 720 የCCTV ካሜራዎች እንዲተከሉና ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል። ይህ ቴክኖሎጂ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ ፍንጭ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ወንጀለኞች ከመፈጸማቸው በፊት እንዲደነግጡ በማድረግ ረገድ ትልቅ የቅድመ-መከላከል ሚና እየተጫወተ ይገኛል። በቀጣይም ይህንን ይበልጥ የማስፋፋት ዕቅድ ይዘን ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል።



**CC TV CAMERA**

**ልደታ ፋና፡-** ከህገ-ወጥ ንግድ፣ ከመሬት ወረራ ወይም ከሌሎች የማህበረሰቡን ሰላም ከሚያውኩ ህገ-ወጥ ድርጊቶች ጋር ተያይዞ በዚህ በጀት ዓመት የተወሰዱ እርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች ቢገለጹልን?

**አቶ ቶሎሳ፡-** "የልደታ ክፍለ ከተማ የልማትና የንግድ ማዕከል እንደመሆኑ መጠን ሕገ-ወጥነትን መቆጣጠር የሰላም ስራችን ዋና አካል ነው። በዚህ በጀት ዓመት ወጣቶችን ለተለያዩ ሱሶችና ለአልባሌ ነገሮች በመዳረግ የአካባቢውን ጸጥታ በሚያናጉ ሕገ-ወጥ መደበቂያዎች ላይ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ሰፊና የተቀናጀ ኦፕሬሽን አካሂደናል።

በወሰድነው የህግ ማስከበር እርምጃ አዋኪ ድርጊት ይፈጸምባቸው የነበሩ በድምሩ 85 ሕገ-ወጥ ቤቶች እንዲታሸጉ ተደርጓል። እነዚህም 49 አረቄ ቤቶች፣ 10 የፑል ቤቶች፣ 9 የቢንጎ ቤቶች፣ 6 ግሮሰሪዎች፣ እንዲሁም በማህበረሰቡና በወጣቶች ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሱ የነበሩ 4 የጫት ማስቃሚያዎች፣ 3 የቁማር ቤቶችና 1 የሺሻ ቤት ናቸው። በቁጥጥሩ ወቅትም 11 የሺሻ ዕቃዎች፣ 15 የቁማር ካርታዎች እና 29 ሙአሰል በኤግዚቢትነት ተይዘዋል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ ከሕገ-ወጥ ንግድ ቁጥጥር ግብረ-ኃይልና ከደንብ ማስከበር ጋር በመቀናጀት ጥብቅ የበር ለበር ክትትል አድርገናል። የሕዝብና የተሽከርካሪ መሻገሪያ መንገዶችን ዘግተው የነበሩ የጎዳና ላይ ንግዶችን የማጽዳት፣ ንብረት የመውረስና የገንዘብ ቅጣት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ወስደናል።

ከገቢዎች መሥሪያ ቤት ጋር በመሆን በምናከናውነው ድንገተኛ የተሽከርካሪ ቁጥጥርም 840 ተሽከርካሪዎች የተፈተሹ ሲሆን፣ ያለ ደረሰኝ ግብይት የፈጸሙ 112 ተሽከርካሪዎች ተይዘዋል። በዚህም 118 ግብር ከፋዮች በአጠቃላይ ብር 42,319,926.35 ደረሰኝ እንዲቆርጡ የተደረገ ሲሆን፣ ደረሰኝ ዘግይተው በቆረጡ 105 አካላት ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት ተጥሏል።

ይህ ውጤት በክፍለ ከተማችን የሕግ የበላይነትን ያረጋገጠ፣ ለሕጋዊ ነጋዴዎች ፍትሃዊ የገበያ ውድድር የፈጠረ፣ የወላጆችን ስጋት የቀረፈ እና ወጣቶቻችንን ከወንጀልና ከሱሶች የታደገ ትልቅ ስኬት ነው። በቀጣይም ማህበረሰቡን የሚረብሹ ማናቸውም ሕገ-ወጥ ድርጊቶች ላይ እርምጃ መውሰዳችንን እንቀጥላለን።"

**ልደታ ፋና፡-** ወጣቶች በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ወጣቶችን በበጎ ፈቃድ የጸጥታ ስራዎች ላይ ለማሳተፍ የተከናወኑ ተግባራት ምን ይመስላሉ?

**አቶ ቶሎሳ፡-** "ወጣቶች ሰላም ዋነኛ ምሰሶዎች ናቸው። ወጣቱን የሰላም አደፍራሽ ለማድረግ የሚሰሩ አካላትን አፍራሽ ሴራ ባከሸፈ መልኩ፣ እኛ ወጣቶቻችንን የሰላም ግንባታው ግንባር ቀደም ተዋናይ የማድረግ ስራ ላይ በልዩ ትኩረት ሰርተናል።

በዚህ በጀት ዓመት ወጣቶች ስለ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንነት፣ ስለ ወንጀል መከላከል እና ስለ አካባቢያቸው ጸጥታ ጥበቃ ሰፊ የንቃተ ህሊና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰጥተዋቸዋል። ይህ ግንዛቤ በመፈጠሩም ወጣቱ የአካባቢውን ሰላም በባለቤትነት እንዲጠብቅ ትልቅ መነሳሳትን ፈጥሯል።

ከዚህ ግንዛቤ ፈጠራ ባለፈ፣ ወጣቶቹን በቀጥታ በሰላም ሰራዊት አደረጃጀት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ እና እንዲደራጁ አድርገናል። በአሁኑ ወቅት ወጣቶቻችን በየወረዳውና በየብሎኩ የራሳቸውን አካባቢ በበጎ ፈቃደኝነት የሚጠብቁ የሰላም ዘብ መሆን ችለዋል። ይህ የወጣቶች በሰላም ሰራዊት ውስጥ በንቃት መሳተፍ በክፍለ ከተማችን አስተማማኝ ጸጥታ እንዲሰፍን ከማድረጉም በላይ፣ ወጣቱ የኃላፊነት ስሜት እንዲሰማውና የራሱን ሰፈር ሰላም ራሱ እንዲያስከብር ትልቅ አቅም ሆኗል።"



**የሰላም ሰራዊት**

**ልደታ ፋና፡-** ከፖሊስ፣ ከደህንነት እና ከሌሎች የፍትህ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማጠናከር በዚህ ዓመት ምን ስራዎች ተሰሩ?

**አቶ ቶሎሳ፡-** "የጸጥታ ስራ በተበታተነ መልኩ የሚሰራ ሳይሆን የተቀናጀ የጋራ ጥረት ውጤት ነው። በዚህ በጀት ዓመት በክፍለ ከተማችን የሰላምና ጸጥታ መዋቅሩን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በጥምር ኃይል ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል። ይህ የጥምር ኃይል መደበኛ በሆነ መልኩ በየወሩ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ በየ15 ቀኑ እንዲሁም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ድንገተኛ የግምገማ መድረኮችን በማካሄድ ስራዎችን በቅርበት ይከታተላል።

በእነዚህ መድረኮች አማካኝነት በሚፈጠሩ ማናቸውም ወቅታዊ የጸጥታ ጉዳዮች ላይ ፈጣን መረጃ በመለዋወጥ፣ የጋራ ዕቅዶችን በማውጣትና ሙሉ መግባባት ላይ በመድረስ በቅድመ-መከላከል ላይ ያተኮሩ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። የዚህ የተቀናጀ አሰራር ትልቁ ማሳያና ውጤት፡-

- በክፍለ ከተማችን የተከበሩ ታላላቅ የአደባባይ በዓላት፣ ሃይማኖታዊና መንግስታዊ ኩነቶች ያለምንም የጸጥታ ስጋትና ችግር በፍጹም ሰላም እንዲጠናቀቁ ማድረግ ተችሏል።

- የወንጀል ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች ላይ በጋራ የተደረጉ ኦፕሬሽኖች ወንጀልን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርገዋል።

- በተመሳሳይ ኡኩይ አላማ አንግበው በክ/ከተማችን የሚንቀሳቀሱ የፀረሰላም ሀይላት ላይ በሚደረጉ ተደጋጋሚ የኦፕሬሽን ስራዎች ጭምር በርካታ ተጠርጣሪዎችን በመያዝ ሊከሰቱ የሚችሉ እኩይ አላማዎችን ቀድሞ መከላከል ተችሏል።

- ከፌዴራልና ከከተማ ፖሊስ፣ ከደህንነት መዋቅሩ፣ ከደንብ ማስከበርና ከፍትህ አካላት ጋር ያለን የመረጃ ልውውጥ አሁን ላይ እጅግ ፈጣንና የተቀናጀ ሆኗል።

ይህ የጋራ ቅንጅት በአንድ አካባቢ ስጋት ሲፈጠር በአጭር ጊዜ ውስጥ በጋራ ደርሶ የመከላከልና የመፍትሄ እርምጃ የመውሰድ አቅማችንን በእጅጉ አሳድጎታል።”

- በአጠቃላይ ይህ በጥምር ኃይሉ የተመዘገበው ቅንጅት በክፍለ ከተማችን አስተማማኝ መረጋጋትን የፈጠረና የሕግ የበላይነትን ያረጋገጠ ዋና ምሰሶ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** በበጀት ዓመቱ የጸጥታና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሲያከናውኑ በዋናነት ያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው? እንዴትስ ተፈቱ?

**አቶ ቶሎሳ፡-** “እርግጥ ነው፣ ሰላምን የማስፈን ስራ ያለ ፈተና አይሆንም። በዚህ ዓመት ካጋጠሙን ዋና ዋና ተግዳሮቶች መካከል አንዳንድ ሆን ተብለው የሚናፈሱ የሀሰት ወሬዎችና ማህበራዊ ሚዲያን ተጠቅሞ ህብረተሰቡን የማሸበር ሙከራዎች፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ የሚታዩ የህገ-ወጥ ንግድ መስፋፋቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህን ችግሮች የፈታነው በሁለት መንገድ ነው፤ አንደኛው፣ ፈጣንና ትክክለኛ መረጃ ለህብረተሰቡ በየጊዜው በመስጠት የሀሰት ፕሮፓጋንዳዎችን ማክሸፍ ስንችል፣ ሁለተኛው ደግሞ ከነዋሪው ጋር በምናደርጋቸው ውይይቶች ችግሮችን በውይይትና በሕግ የበላይነት የመፍታት ስራዎችን በማከናወን ፈተናዎቹን ወደ መልካም አጋጣሚ ቀይረናቸዋል።”

**ልደታ ፋና፡-** በቀሪው የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች ሰላማቸው ተጠብቆ የልማት ስራዎች እንዲቀጥሉ ምን ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ይከናወናሉ? ለህዝቡስ የሚተላለፍ መልዕክት ካለዎት?

**አቶ ቶሎሳ፡-** “በቀሪው ጊዜ ውስጥ በክፍለ ከተማችን አስተማማኝ ሰላምን ዘላቂ ለማድረግ እና የጀመርናቸውን ስኬቶች ይበልጥ ለማስቀጠል በትኩረት የምንሰራባቸው ዋና ዋና ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች አሉን። እነሱም፡-

**1.** የ7ኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ በሰላም ማስፈጸም፡- በዘንድሮው ዓመት የሚከናወነው 7ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ በክፍለ ከተማችን ያለምንም የጸጥታ ችግር፣ በዲሞክራሲያዊ እና በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ የጸጥታ መዋቅራችንን ሙሉ በሙሉ ዝግጁ በማድረግ ከፍተኛ የክትትልና የጥበቃ ስራ እንሰራለን።

**2.** የጸጥታ አጋዥ ኃይሎችን ማጠናከር፡- የወንጀል ምጣኔን አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ ይበልጥ አውርዶ ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ ለማድረግ፣ በየደረጃው ያሉ የጸጥታ አጋዥ ኃይሎቻችንን አሁን ካሉበት አደረጃጀት በላይ የማብቃት፣ የማጠናከር እና የማስታጠቅ ስራዎችን በስፋት እንሰራለን።

**3.** የቴክኖሎጂ (CCTV) ተደራሽነትን ማስፋፋት፡- እስካሁን የCCTV ካሜራ ቁጥጥር ባልደረሰባቸው እና የወንጀል ስጋት ባለባቸው የአካባቢ ክፍተቶች ላይ ቴክኖሎጂውን ተደራሽ በማድረግ ሙሉ ቁጥጥር የምናደርግበትን አቅም እንገነባለን።

**4.** የጸጥታ ስጋቶችን ማክሰም፡- ለሰላም ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም አዝማሚያዎች፣ ቡታዎች እና ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን አስቀድሞ በመለየት የማክሰም እና የማስወገድ (Neutralize የማድረግ) ስራ በቁርጠኝነት ይሰራል.

**5.** የህዝብ ግንዛቤን እና ባለቤትነትን ማሳደግ፡- ህብረተሰቡን የሰላም ዋና ባለቤት ከማድረግ አንጻር ተደጋጋሚ እና ተከታታይነት ያላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማከናወን፣ የነዋሪው የሰላም ጠባቂነት ሚና ተጠናክሮ እንዲቀጥል እናደርጋለን።

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ቶሎሳ፡-** ሰላም የአንድ ወገን ስራ ሳይሆን የጋራ ውጤት ነው። እስካሁን ለሰጣችሁን ሙሉ ድጋፍ እና አጋርነት በጽሕፈት ቤቱ ስም ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። በቀጣይም የአካባቢያችሁን ሰላም በባለቤትነት በመጠበቅ፣ አጠራጣሪ ነገሮች ሲያጋጥሙ ፈጣን መረጃ በመስጠት እና ከጸጥታ መዋቅሩ ጎን በመቆም የተለመደው ትብብራችሁ እንዲቀጥል ጥሪዬን አቀርባለሁ። የልደታ ክፍለ ከተማ ሁልጊዜም አስተማማኝና ሰላማዊ የኑሮና የስራ ቀጠና ሆና እንድትቀጥል በቁርጠኝነት እንሰራለን።”

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**አቶ ቶሎሳ፡-** እኔም ከልብ አመሰግናለሁ።

## ሕግ አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም!

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 84/2016 የተቋቋመ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 25 የተሠጡት ስልጣንና ተግባራትን በተዋረድ ያለው የክ/ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት ለአስተዳደሩ ሕጋዊ ወኪል በመሆን በየትኛውም የዳኝነት እርከን በመቅረብ አስፈላጊውን ክርክር በማድረግ የነዋሪዉንና የአስተዳደሩን መብት እና ጥቅም የማስጠበቅ እና ንቃተ ህግ የማዳበር ስራ እየሰራ ሲሆን በተዋረድ በተሰጠን ስልጣን መሠረት ለተግባራዊነቱ ተገቢውን ርብርብ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በጀት ዓመቱ በጽ/ቤቱ የተሰሩ ዋና ዋና ስራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

የህዝብና የመንግስት መብትና ጥቅም ከማስከበር አንጻር የተሰሩ ስራዎች የፍትሐ-ብሄር መዝገብ አፈጻጸም በተመለከተ ካለፈው የዞሩ 101 መዝገቦችንና አዲስ የመጡ 131 መዝገብ በአጠቃላይ 232 ያህል መዝገቦች ላይ ክትትል ተደርጓል። ክትትል ከተደረገባቸው መዝገቦች ውስጥ 107 መዝገቦች በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ውሳኔ ካገኙት መዝገቦች ውስጥ 97 ለመንግስት ሲወሰን 10 መዝገቦች በመንግስት ላይ ተወስኗል። 8 መዝገቦች ላይ ይግባኝ ተጠይቆባቸው 3ቱን ማሻር ተችሏል። በሂደት ላይ 130 መዝገቦች ይገኛሉ። የህዝብና የመንግስት ጥቅም ከማስከበር አንጻር 34,143,300.00/ሰላሳ አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሸህ ሶስት መቶ ብር/ እና በአይነት **11389**/አስራ አንድ ሸህ ሶስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ/ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ 64 ክፍል የመንግስት ቤት ጥቅም ተከብሯል።



**አቶ ወርቁ ከተማ**
**የፍትህ ጽ/ቤት ሃላፊ**

የወንጀል ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር የተሰሩ ስራዎች በተመለከተ በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ከቀረበ 800 የግል አቤቱታ የወንጀል ምርመራ መዝገቦች ውስጥ 760 በዕርቅ ያለቀ ሲሆን የእርቅ ምጣኔ 95% መፈፀም ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ የወንጀል ጉዳዮች ክርክር በፍ/ቤት የማስቀጣት 40 መዝገቦች ፍርድ ቤት ቀርበው የመዝገቦች በመርታትና ማስወሰን ተችሏል፡፡ የመርታት ምጣኔ አፈፃፀም 100% በበጀት ዓመቱ የደንብ ማስከበር ውሳኔዎችን የማስፈጸም አቅም 32 መዝገብ የቀረበ ሲሆን 32ቱም ተፈፅሞ ከቅጣት የተሰበሰበ ገንዘብ 1,914,000 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አስራ አራት ሺህ ብር) በመቀታታቸው አፈፃፀሙ 100% ፐርሰነት ማደረስ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ የተያዙና የተከሰሱ ሰዎች የሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ 18 ጊዜ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 48 ጊዜ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህግ የበላይነትን እንዲረጋገጥ/እንዲሰፍን/ ከማድረግ ጋር በተያያዘ በሰብአዊ መብት፤ በምርጫ ህግ፤ በሴቶች መብት፤ አዋጅ ቁጥር 1383/17 የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገዴ አዋጅ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዝ ዳርቻ ልማትና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 ላይ፤ ስለ ስነ-ምግባር፤ የሙስና ወንጀል ውስብስብነት እና ከሌሎች ወንጀሎች ስለሚለይበት ጉዳይ፤ ተጠያቂነትና ቅጣት እና የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ፣ ምርመራ፣ አወሳሰን እና የተጠያቂነት ሥርዓት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 143/2015 ላይ የህግ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ በልደታ ክ/ከተማ በሚገኙ የ10ሩም ቀጠና አስተባባሪዎች በማህበረሰብ አቀፍ ፍትህ አገልግሎት ማዕከል ማኑዋል 1/2017 ላይ፣ በመሰረታዊ ህግ እና በህግ ክበባት ማቋቋሚያ ማኑዋል ላይ፤ በአረጋዊያን ዙሪያ በወጡ ህጎች፤ በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ ስልጠና በመድረክ የተሰጠ ሲሆን በተጨማሪም በአደባባዮች፤ በታክሲና አውቶብስ ሰልፎች፤ ሰው በሚበዛበት አካባቢ የንቃተ ህግ ስራ ተሰርቷል፡፡

## ህግን ማክበር ለህዝብ ጥቅም

በከተማ አስተዳደር ውስጥ የህዝብና የመንግስት ንብረት የሆነውን መሬት ከወረራ መጠበቅ፣ ህገ-ወጥ ግንባታን መከላከል እና ያለፈቃድ የሚካሄዱ የንግድ እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር ለስርዓት የተመሰረተ ከተማ ግንባታ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ የልደታ ክፍለ ከተማ የደንብ ማስከበር ጽ/ቤትም የከተማውን ፕላን፣ ህግና ደንብ በማስከበር የህዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ በርካታ ተግባራትን በትኩረት እያከናወነ ይገኛል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዋጅ 84/2016 ዓ/ም አንቀፅ 50 ከተማ አስተዳደሩ በተሰጠው ተግባር እና ሃላፊነት መሰረት የቅድመ መካላከል እና ስልጠና ዘርፍ እንደገና በማቋቋም ለነባር ኦፊሰሮች የንድፈ ሃሳብ እና ከፊል ወታደራዊ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ፣በጎ ፈቃደኞችን መመልመል  እንዲሁም የህብረተሰብ ተኮር የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባራትን በማከናወን ደንብ መተላለፍ እንዳይፈፀም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡



**አቶ ደበሎ ጃለታ**
**የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ**

ጽ/ቤታችን ካለው ሃይል አንፃር በ4 ቡድን ቀጥታ ለጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪ የሆኑ 1 የህግ ባለሙያ እና የንብረት ክፍል እንዲሁም 1 አስተባባሪ የተዋቀረ ሲሆን በተለይም የቁጥጥር ኢንስፔክሽን እና ግብረ-ኃይል ቡድን ላይ ያለብንን የፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰሮችን ከተለያዩ ወረዳዎች በውስት በማስመጣት የሰው ሃይል ችግራችንን በጊዜዊነት  የፈታን ሲሆን  በቀጣይ ከማዕከሉ እና ከክ/ከተማው ፐብሊክ ሰርቨስ እና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር ዘላቂ በተለይም ከፍተኛ በሆኑ መደቦች ላይ ለቦታው ብቁ የሆኑ የሰው ሃይል የማሟላት ስራ እንሰራለን፡፡

የደንብ ማስከበር ስራ የአንድ ተቋም ብቻ ኃላፊነት ሳይሆን የህብረተሰቡን ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ጽ/ቤቱ ከነዋሪዎች፣ ከፖሊስ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የህግ የበላይነትን ለማስፈን በትኩረት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

በክፍለ ከተማው ውስጥ የሚፈጸሙ የመሬት ወረራ ድርጊቶችን በቅድመ መከላከል፣ በክትትል እና በህጋዊ እርምጃ በመታገዝ የህዝብና የመንግስት ንብረት እንዳይባክን እየሰራ ይገኛል፡፡ በመንገድ ዳርቻዎች፣ በአረንጓዴ ስፍራዎች፣ በልማት ተብለው በተያዙ ቦታዎች እና ለህዝብ አገልግሎት በተመደቡ መሬቶች ላይ የሚደረጉ ህገ-ወጥ ወረራዎችን በመለየት ፈጣን እርምጃ ይወስዳል፡፡ ህጋዊ ፈቃድ ወይም ከተፈቀደው ፕላን ውጭ የሚከናወኑ ህገ-ወጥ ግንባታዎችን በመቆጣጠር የከተማው ፕላን እንዳይዛባ እና የዜጎች ደህንነት ለማስጠበቅ በትኩረት ይሰራል፡፡ የተለያዩ የፍተሻ ስራዎችን በማከናወን፣ ግንባታዎችን በመቆጣጠር እና ለህግ ተገዢነት የማስተማር ስራዎችን በመስራት የችግሩን መጠን ለመቀነስ እየተጋ ነው፡፡

በንግድ ዘርፍም ጽ/ቤቱ ያለፈቃድ ወይም ከተፈቀደለት የንግድ አይነት ውጭ የሚካሄዱ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በመከታተል የንግድ ስርዓት እንዲጠበቅ ለማድረግ በእግረኛ መንገዶች፣ በህዝብ ማለፊያዎች እና በህገ-ወጥ መልኩ በተያዙ ቦታዎች ላይ የሚካሄዱ ንግዶችን በመቆጣጠር የከተማውን ውበት፣ ስርዓትና የህዝብ ምቾት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስራዎችን እየሰራ የሚገኝ ጽ/ቤት ነው።

በመጨረሻም የልደታ ክፍለ ከተማ የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት የህዝብና የመንግስት ንብረትን ከወረራ በመጠበቅ፣ ህገ-ወጥ ግንባታንና ንግድን በመከላከል እና ህግና ደንብ የሚከበርባት ከተማ ለመገንባት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል። የዚህ ተግባር ስኬትም የሁሉንም ዜጎች ህግን የማክበር ባህል እና ከመንግስት ተቋማት ጋር ያለውን ትብብር ይጠይቃል።

## ብክነትን የቀረፈ ተቋም

የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ፣አግባብና ስርዓት ባለዉ መንገድ ማይያዝና አግልግሎት ላይ የማይዉል ከሆነ ሀገራችን ለክፍተኛ ብክነትና ወጪ ትዳረጋለች ይህ ማለት ለልማት ይዉል የነበረ የሀገር ሀብት ለአላስፈላጊ ንብረት ግዥ ይዉላል። ይህን ችግር ለመከላከል የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት በአዋጅ ተቋቁሞ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በክፍለ ከተማችን የምንግስት ንብረት ያለበት ሁኔታና አመታዊ አፈጻጸሙን አስመልክቶ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ኢ/ር ቅድስት ማቴዎስ ከኛ ጋር ቆይታ አድርገዋል ይከታተሉን።

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ሆነዉ በመገኘትዎ አመሰግናለሁ።

**ኢ/ር ቅድስት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** በ2018 በጀት ዓመት በክፍለ ከተማው የሚገኙ የመንግስት ንብረቶችን በአግባቡ ከመለየትና ከመመዝገብ አንጻር ምን አይነት ስራዎች ተሰሩ? በተለይም የቆሙ ንብረቶችን (Dead assets) ወደ ስራ ከማስገባት ወይም በጨረታ ከማስወገድ አኳያ የተመዘገበው ውጤት ምንድነው?

**ኢ/ር ቅድስት፡-**ንብቶችን ወደ ዘመናዊ ቋት ከማስገባት አንፃር የ48 ተቋማት እንዲያስገቡና እንዲመዘገቡ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

•ንብረት ጠግኖ ከመጠቀም አንጻር የንቅናቄ መድረክ በማዘጋጀት ኤሌክትሮኒክ ዕቃዎችን እንዲጠገኑ እና ድጋሚ ስራ ላይ በማዋል ውስኑን የመንግስት ሀበትን ከብክነት ለመከላከል ከኢንቬሽንና ቴክኖሎጂ ቡደን ጋር በጋራ በመሆን የጥገና ቡደን በማዋቀርና እንዲሁም ለጥገና የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በማሟላት በ48 ተቋም የሚጠገኑ ንብረቶችን በመለየት በ15 ተቋማት የንብረት ጥገና በማከናወን በብር 1,890,300.00 ብር የሚገመት የመንግስትን ሀብት ከብክነት ማዳን ተችሏል።

•ንብረት ከማስወገድ አንጻር 26 ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶችን እንዲያደረጁ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ከተያዘው ተቋማት በላይ በ29 ተቋማት በመንግስት ንብረት ግዢና ማስወገድ አገልግሎት እና በራስ አቅም ንብረቶች እንዲወገዱ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**ከዚህ ቀደም በንብረት አስተዳደር ዘርፍ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን (ለምሳሌ፡- የጥገና መጓተት፣ የቁሳቁስ እጥረት ወይም ፍትሃዊ ያልሆነ የንብረት ትስርጭት ለመፍታት በበጀት ዓመቱ የተወሰዱ ተጨባጭ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

**ኢ/ር ቅድስት፡-**በዘንድሮ አመት በተለይም የንብረት ጥገናን በተመለከተ የተለመዱ መጓተቶችን በማስቀረት በቅንጅታዊ አሰራር ክላስተር ውስጥ እንደ ዕቅድ በመያዝ እና በከተማ ደረጃ የተጀመረ የአንድ ወር የንብረት ጥገና ንቅናቄ በርካታ ንብረቶችን በመጠገን ንብረት እና የሚወገዱትን በጊዜ እንዲወገዱ በማድረግ የመንግስትን ሀብት ማዳን ተችሏል። በዚህም የቁሳቁስ ዕጥረት የነበረበትን የተጠገኑ ንብረቶችን መልሶ በመጠቀም የማድረግ ስራ ተሰርቷል።



**ኢ/ር ቅድስት ማቲዎስ**
**የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**የመንግስት ንብረት አያያዝን ከባህላዊ አሰራር ወጥቶ በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (*Digital Invento ry System*) ለመምራት የተጀመሩ ጥረቶች አሉ? ይህስ የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ ረገድ ምን ሚና ተጫውቷል?

**ኢ/ር ቅድስት፡-** ከ*Digital Inventory System* አንጻር በ2016ዓ.ም በከተማ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በበጸለገው ሶፍት ዌር አመካኝነት በተጠቃሚ ዕጅ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶችን እንዲመዘገቡ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም አላቂ(ስቶክ) ወደ ሲስተም እንዲገባና በተጠቃሚዎች ኦንላይ ወጪ እንዲያደርጉ ማስጀመር ተችሏል። ግልጽነትና ተጠያቂነት ከመፍጠር አኳያ እያንዳንዱ ንብረት በማን እጅ እንደሚገኝ የንብረት በኪውአር ኮድ እንዲለጠፍ በማድረግ በሲተም አማካኝነት የዕርጅና ቅናሽ እንዲሁም አሁን ያለበት ሁኔታ በኦላይን ኮምፒውተር መረብ ስለሚታወቅ የንብረት መጥፋትና መባከን እድልን በእጅጉ ቀንሷል። እንዲሁም የመንግስት ንብረት እንደ ባለቤት አልባ ከሚታይበት አሁን ላይ ሁሉም ባለቤትነት ስሜት እንዲሰማዉ እና ለተረከበዉ ንብረት ሀላፊነት ተጠያቂነት እንዲሰማዉ በማድረግ ረገድ ቴክኖሎጂ መጠቀም ትልቁን ሚና ተጫዉቷል።

**ልደታ ፋና፡-** የመንግስት ሀብትንና ንብረትን ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በማድረግ፣ ብክነትን ለመቀነስ ምን አይነት የክትትልና የቁጥጥር ስርአት ተዘርግቷል? በዚህ ረገድ የታዩ የለውጥ ውጤቶች ቢገለጹልን?

**ኢ/ር ቅድስት፡-** የንብረት ኦዲት በየጊዜው ድንገተኛና መደበኛ የንብረት ቆጠራና ኦዲት በ13 ተቋማት በማድረግ በዚህ መሰረት 112,742.40 ብር ወደ መንግስት ካዝና መመለስ የተቻለ ሲሆን ንብረት ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋሉ ማረጋገጥ ተችሏል።

•የወጪ ቆጣቢነት ውጤት አንጻር አዳዲስ ንብረቶችን ከመግዛት ይልቅ የቆዩትን ጠግኖ የመጠቀም ባህል በመዳበሩ፣በበጀት ዓመቱ ለግዢ ሊወጣ የነበረ ከፍተኛ ወጪን መቀነስ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** እስካሁን ባለው አፈጻጸም የታዩ ጠንካራ ጎኖችእንደተጠበቁ ሆነው፣ አሁንም በዘርፉ እንደፈተና የሚታዩና በቀጣይ በልዩ ትኩረት ሊፈቱ የታቀዱ የመልካም አስተዳደርጉዳዮች ምንድናቸው?

**ኢ/ር ቅድስት፡-** በ2018 በጀት ዓመት በርካታ የመልካም አስተዳደር የሚሆኑ ችግሮችን እንዲፈቱ የማድረግ እንዲሁም ለዉስጥም ሆነ ለዉጭ ተገልጋይ የተሟላ እና አስተማማኝ ደህንነቱን የጠበቀ ምቹ የሆነ የስራ አካባቢ መፍጠር የተቻለ ሲሆን ለቀጣይ አመት የአስተዳደሩ ህንፃ ርክክብ ያልተፈፀመ በመሆኑ ያላለቁ የፊኒሽንግ ስራዎች ምክንያት የሚፈጠሩ የመልካም አስተዳደር ችግር ለምሳሌ፡ የፓርኪንግ ጥበት እና መሰል ስራዎች እንዲጠናቀቁ ማድረግ እና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚሰራ ስራዎች ትኩረት የሚሹ እና ሊፈታ የሚገባ አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግር ነዉ፡፡

## መልካም ሥነ-ምግባር ለሀገር ዕድገት

ሙስና የህዝብ ሀብትን በመዝረፍ፣ የህግ የበላይነትን በመሸርሸር፣ የፍትህ ሥርዓቱን በማዛባትና የህብረተሰብ እምነትን በመናድ የሀገርን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት የሚያደናቅፍ አደገኛ ጠንቅ ነው። በመሆኑም ሙስናን መከላከል የአንድ ተቋም ብቻ ሳይሆን፣ የመንግስት፣ የተቋማት እና የህብረተሰብ የጋራ ኃላፊነት መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።

ሥነ-ምግባር የሰው ልጅ ባህሪን የሚመራ መሠረታዊ እሴት ሲሆን፤ ታማኝነትን፣ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትንና ፍትሃዊነትን ያቀፈ ነው። እነዚህ እሴቶች በተቋማት ውስጥ በተግባር ሲተረጎሙ ለተሻለ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ለህዝብ እምነትና ለአስተዳደር ጥራት ወሳኝ ናቸው። በአንጻሩ፣ እነዚህ እሴቶች ባልተጠናከሩባቸው ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራር በቀላሉ ሥር ይሰዳሉ። ስለዚህ፣ የሥነ-ምግባር ግንባታ ከፀረ-ሙስና ትግል ጋር ያላቸው ቁርኝት እጅግ የጠበቀ ነው።

በኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል በህግ፣ በፖሊሲና በተቋማዊ አቅም ግንባታ ሰፊ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል። የሙስና ወንጀል አዋጆች፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቶች መዘርጋት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችና የህብረተሰብ ተሳትፎን ማሳደግ ከእነዚህ ጥረቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ እርምጃዎች በየደረጃው አበረታች ውጤቶችን እያመጡ ቢሆንም፣ ሙስናን ሙሉ በሙሉ ለመግታት የተቀናጀ፣ ዘላቂና የማይናወጥ ትግል እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው።

በዚህ መሠረት በ2018 በጀት ዓመት የልደታ ክፍለ ከተማ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል በተቋሙ ውስጥ የሚፈጠሩ የሙስና ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ፣ የአሠራር ግልጽነትን ለማሳደግ፣ የተጠያቂነት ሥርዓትን ለማጠናከርና የህብረተሰቡን እምነት ለመገንባት በተለያዩ አቅጣጫዎች እየሰራ ይገኛል። ከዚህም በላይ፣ ለነገው ትውልድ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ለማላበስ በትምህርት ተቋማት፣ በማህበራዊ መድረኮችና በሚዲያ አማካኝነት የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተከናውነዋል።



**ወ/ሮ እማዋይ አበባው**
**የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪ**

**ልደታ ፋና፡-**በበጀት አመቱ በተቋሙ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ያመጡትን ለውጥ ቢገልፁልን?

**ወ/ሮ እማዋይ አበባው ፡-** የሞራል እሴቶችንና ተቋማዊ አቅም ግንባታ ስራ ማሳደግ ተችሏል በ2018 በጀት ዓመት በክፍለ ከተማና በወረዳ በስነ ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ክፍል ለአመራር፣ ለሠራተኞች፣ለወጣቶች፣ለሴቶች ፣መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ፣ ለምክር ቤት አባላት፣ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ከ14,000 በላይ ለሚሆኑ አካላት በሙስና መከላከል ጸንስ ሃሣብ፣በሙስና ወንጀል አዋጅ 881/2007 ፣ በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ እና በሙያ ስነ ምግባር ግንባታ፣በአስቸኳይ ሙስና መከላከል አጠቃላይ የሥነ ምግባር እና የሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሥርዓት ለማሣደግ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት ተችሏል።በትምህርት ተቋማት የሥነ ምግባር ማጎልበቻ ሥርአት ማጠናከር በተመለከተ በክፍለ ከተማው ስር በሚገኙ 49 መንግስትና የግል አንደኛና 2ኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶች የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክበባት እንዲቋቋም ተደርጓል። ክበበት ያሉበት ደረጃ ለማወቅ የክትትልና ድጋፍ ስራ መስራት ተችሏል፡ ፡ ለመንግስትና ለግል ትምህርት ቤቶች የክበባት አመራርና ተማሪዎች ስልጠና በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፣ ትምህርት ቤቶች በክበባት መካከል የልምድ ልውውጥ በማድረግ የተገኘውን ተሞክሮ ወደ ተቋማቸው በመቀየር የተሻለ የትውልድ ስነ ምግባርግንባታ እንዲኖር ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣እንዲሁም ተማሪዎች በሙስና መከላከልና በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ ላይ ያላቸውን እውቀት ለማወቅ የጥያቄና መልስ ውድድ የተሻለ ውጤት ያመጡትን የማበረታቻ ሽልማት በመስጠት በተማሪዎች መካከል የክክር መንፈስ እንዲፈጠር የማድረግ ሰራ ተሰርቷል።በ2018 በጀት ዓመት በዓለም 22ኛውንና በሀገራችን 21ኛውን የፀረ-ሙስና ቀን "ትውልድን በሥነ-ምግባር፣ ተቋምን በአሰራር" በሚል መሪ ቃል በተደረገው የፓናል ውይይት በክፍለ ከተማ እና በወረዳ በተደረገው ንቅናቄ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ 53,145 የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ ችለናል። ይህም በዝርዝር ሲታይ፤ 29,645 የሚሆኑት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች (አመራርና የመንግስት ሠራተኞች፣ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች፣የፀጥታ አካላት) ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ 27,510 ደግሞ በተለይ ለነገ ሀገር ተረካቢ በሆኑ ተማሪዎችና መምህራን (በፓናል ውይይት፣ በሚኒ-ሚዲያ፣ በሰልፍ ስነ-ስርዓት) ይህ ቁጥር የሚያሳየው የንቅናቄው ስራ ህብረተሰቡን ያሳተፈና እስከታችኛው እርከን ድረስ የወረደ መሆኑንና የፖለቲካ አመራሩም ለጉዳዩ ትኩረት የሰጠበት ነው።

የፀረ-ሙስና መልዕክቶችን በስፋት ለማዳረስ ከኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት ተሰርቷል። የተለያዩ መልዕክቶች ተዘጋጅተው በማህበራዊ ሚዲያ የተሰራጩ ሲሆን፣ የኮሚሽኑን የማህበራዊ ሚዲያ ተከታዮች ቁጥር ለማሳደግም ጥረት ተደርጓል። የተለያዩ ህትመቶች (ባነሮች፣ ብሮሸሮች፣ በራሪ ጽሑፎች) ተዘጋጅተው እንዲሰራጩ በማድረግ የፀረ ሙስና ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማረጋገጥ ሙስናን ለመከላከል የጥቆማ ስርዓቱ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በበጀት ዓመቱ ውስጥ በክፍለ ከተማና ወረዳዎች 42 የሙስና ጥቆማዎች (36 መደበኛ እና 6 አስቸኳይ የሙስና ጥቆማዎች) ቀርበዋል። የቀረቡ ጥቆማዎች በዓይነት ሲገለጹ መሬት ነክ ጉዳዮች 1፣የስዉ ሀብት ሰምሪት 7፣የቤት ነክ ጉዳዮች 6፣ ማጭበርበር 7፣ ከከለላ ጥያቄ ጋር የተያያዘ 1፣ እንዲሁም 14 ሌሎች የሙስና አይነቶች በበጀት ዓመቱ ቀርበዋል። ከቀረቡት ጥቆማዎች 42 ያህሉ ተጣርተው ለ28ቱ ምክረ ሀሳብ የተሰጠ ሲሆን 1 ጉዳዮች ለህግ እንዲቀርቡ ተደርጓል፤ 13ቱ ደግሞ አግባብነት የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል። ቀሪዎቹ በማጣራት ሂደት ላይ ናቸው።በክፍለ ከተማና በቀረቡ ጥቆማዎች መነሻነትና በመከታተያ ክፍሎች ክትትል ሊፈጸሙ የነበሩ የሙስና ድርጊቶችን ማስቆም ተችሏል። በተለይም በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራዎች በክፍለ ከተማ 454,825.00 የመንግስትና የህዝብ ሀብት ከብክነት እንዲድን ማድረግ ተችሏል እንዲሁም በመደበኛ የሙስና መከላከል ስራ የአሰራር ክፍተት የነበረባቸውን ተቋም አሰራራቸውን እንዲያስተካክሉና ችግር የነበረባቸው አካላት ተጠያቂ እንዲደረጉ ማድረግ ተችሏል፡ ፡ በበጀት ዓመቱ በአገልግሎት ማዘግየት ፤ በሌብነትና ብልሹ አሰራር ተጠያቂ የተደረጉ 14 ፈጻሚዎችና 1 አመራር ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰድ ተደርጓል። የሙስና ተጋላጭነት ጥናቶችን በማካሄድ የአሰራር ክፍተቶችን ለመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ የሚያስችሉ ስራዎች ተከናውነዋል። በቀረቡ ጥናቶችና ምክረ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎችን የመከታተልና የመገምገም ስራም ተከናውኗል።

**ልደታ ፋና፡-** ስለ ሙስና አስከፊነት እየተሰጠ ያለው ግንዛቤ ያመጣው ተጨባጭ ለውጥ ካለ ቢገልፁልን?

**ወ/ሮ እማዋይ አበባው፡-** ቀደም ሲል ህብረተሰቡ የሙስና ድርጊቶችን ሲመለከት "ምን አገባኝ" ወይም "ብናገርም ለውጥ የለውም" በሚል ዝምታን ይመርጥ ነበር። አሁን ግን የግንዛቤ ስራው ውጤት አምጥቶ በበጀት ዓመቱ 42 ጥቆማዎች በድፍረት መቅረባቸው፣ ህብረተሰቡ ሙስናን የመታገል የባለቤትነት ስሜት እያሳየ መሆኑን ያረጋግጣል። በተለይም በትምህርት ቤቶችና በወጣቶች ዘንድ የሚሰሩ የግንዛቤ ስራዎች ሙስናን እንደ ብልህነት ሳይሆን እንደ ሀገር ክህደትና እንደ "ነውር" እንዲታይ አድርገዋል። በ 49 ትምህርት ቤቶች የተቋቋሙት የፀረ-ሙስና ክበባት ተማሪዎች ገና በለጋነታቸው በታማኝነትና በስነ-ምግባር እንዲታነጹ በማድረግ ረገድ ትልቅ ለውጥ እያመጡ ነው። የግንዛቤ ስራው በባለሙያዎችና በአመራሩ ዘንድ አሰራርን የመፈተሽ ዝንባሌን ፈጥሯል። ድርጊቱ ተፈጽሞ ከሚደረግ ክትትል ይልቅ፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ 454,825.00 ብር ከመባከኑ በፊት እንዲድን መደረጉ የግንዛቤ ስራው ብልሹ አስራር ሲያጋጥም ቀድምው እንደሚከታተሉ ያሳያል።የግንዛቤ ስራው የፀረ-ሙስና ትግሉን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት የጋራ አጀንዳ እንዲሆን አድርጎታል። ይህም ሙስናን በጋራ የመከላከል ህዝባዊ ንቅናቄ እንዲፈጠር ረድቷል።

**ልደታ ፋና፡-**በየተቋሙ ያለውን የፀረ- ሌብነት ትግል እንዴት ይገልጹታል?

**ወ/ሮ እማዋይ አበባው ፡-**በየተቋሙ እየተካሄደ ያለው የፀረ-ሌብነት ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረና ወደ ተደራጀ የስርዓት አቀራረብ እየተሸጋገረ መሆኑ ይታያል። ትግሉ በተለይ አሰራርን በቴክኖሎጂ የማዘመን ጥረትየሰው ንክኪን በመቀነስ አገልግሎቶችን ወደ ዲጂታል መስክ ማስገባት በመጠናከር፣ ለሙስናና ለሌብነት የሚፈጠሩ እድሎችን መቀነስ ተቻሏል። ለአመራሮችና ለሰራተኞች በተሰጡ ስልጠናዎች ሌብነትን እንደ ወንጀል ብቻ ሳይሆን እንደ ስነ-ምግባር እንከን እንዲመለከቱ የአመለካከት ለውጥ ተፈጥሯል።የውስጥ ኦዲት፣ የክትትል ስርዓቶችና የጥቆማ ስርዓቶች በመጠናከር ሌብነት ከመፈጸሙ በፊት ማስቆም የሚችል አቅም እየተፈጠረ መሆኑ።"በየተቋሙ ትግሉ በአንድ ወገን ስራ ብቻ ሳይሆን፣ የአመራሩን ቁርጠኝነት፣ የአሰራር ግልጽነትን እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ ያጣመረ በመሆኑ፣ በቀጣይ የተሻለ አስተዳደራዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ተስፋ የሚሰጥ ነው።"

**ልደታ ፋና፡-**ፀረ- ሙስና ከመከላከል አንፃር ህብረተሰቡ ያለው ሚና እንዴት ይገለፃል?

**ወ/ሮ እማዋይ አበባው ፡-**ህብረተሰቡ ሙስና በሚፈጸምባቸው ተቋማት ውስጥ አገልግሎት የሚፈልግ አካል እንደመሆኑ፣ የተንዛዙ አሰራሮችን፣ ጉቦ የመጠየቅ ተግባራትንና የመብት ጥሰቶችን በመጠቆም ለፀረ-ሙስና ትግሉ የላቀ ግብዓት ሊሆን ይገባል። ህብረተሰቡ በየተቋማቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀልጣፋና ህጋዊ እንዲሆኑ መጠየቅ አለበት። "አገልግሎቱ ለምን ዘገየ?", "የአሰራር ሂደቱ ምንድን ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን በተደጋጋሚ ማንሳቱ፣ ተቋማት በድብቅና በብልሹ አሰራር እንዳይሄዱ ያግዛቸዋል። የሚጠይቅ ህብረተሰብ ባለበት ቦታ ሙስና ቦታ አይኖረውም።ሙስናን መከላከል በህግ ብቻ ሳይሆን በባህልና በሞራል ጭምር መሆን አለበት። ህብረተሰቡ በቤተሰብ፣ በሰፈርና በስራ ቦታ ስነ-ምግባር ያላቸውን ሰዎች በማበረታታት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሌብነት የተገኘን ሀብት በመጸየፍና "በላብህ አግኝ" የሚለውን እሴት በማስረጽ ረገድ ትልቅ ሚና አለው።

**ልደታ ፋና፡-**በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

**ወ/ሮ እማዋይ አበባው ፡-**ሙስና የጋራ ቤታችንን መሰረት የሚሸረሽር፣ የዜጎችን መብት የሚገፍና የአገራችንን እድገት የሚገታ አደገኛ ጠንቅ ነው። ይህንን ተግዳሮት በአንድ ተቋም ብቻ መፍታት አይቻልም፤ የተሳካ የፀረ-ሙስና ትግል የሚኖረው የአመራሩ ቁርጠኝነት፣ የተቋማት ግልጽነትና የህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ሲጣመሩ ብቻ ነው።ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር፣ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለህዝብ ግልጽ ማድረግ የዘወትር ተግባራችን ይሁን። ብልሹ አሰራርን በመጠቆም፣ ግልጽነትን በመጠየቅና የስነ-ምግባር እሴቶችን በየቤታችን በማስረጽ፣ ሙስናን እንደ ነውር የምንጸየፍበትን አዲስ ምዕራፍ በጋራ እንክፈት።

**ልደታ ፋና፡-** ስለ ቃለ መጠይቁ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ እማዋይ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ ።



## ወ/ሮ በላይነሽ ሞሲሳ
### የትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** ፍትሃዊ የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነትን ከማሳደግ ተሰሩ ስራዎች ቢገልጹልን?

**ወ/ሮ በላይነሽ፡-** የአንድን ሀገር እድገት ከሚወስኑት ጉዳዮች ዋነኛው ትምህርትና ሥልጠና ነው፡፡ የተጀመረውን የለውጥና የብልጽግና ጉዞ በአስተማማኝነት ከግብ ለማድረስ ብቁና በቂ የሰው ሃይል ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ መንግሥት ለትምህርትና ሥልጠና ትኩረት በመስጠት የትምህርት ተደራሽነትን፣ ተገቢነትን፣ ፍትሐዊነትንና ጥራትን ለማረጋገጥ ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ እንደ ልደታ ክ/ከተማ በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፉ ትምህርቱን እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሁሉም ዜጎቻችን ለማዳረስ የትምህርት ተቋማት ቁጥር በ57 ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በ44 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በ11 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ61,308 (ስልሳ አንድ ሺ ሶስት መቶ ስምንት) በላይ ተማሪዎችን ማስተናገድ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ 100%፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎን 100% እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎውን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

በ2018 የትምህርት ዘመን በ6ኛ ክፍል 3,532 እና በ8ኛ ክፍል 3,400 ከተማቀፍ ፈተናዎች ማስፈተን የተቻለ ሲሆን በ12ኛ ክፍል ከ3,411 በላይ ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን ለማስፈተን በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር ለማሻሻል መምህራንና የትምህርት አመራሩን ለደረጃው ብቁ ለማድረግ አቅም በመገንባት፣ የትምህርት ቤቶችን ስታንደርድ አቅም በፈቀድ መጠን በማሻሻል የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥ ሰፋፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በትምህርት ለትውልድ ስራዎች የመጣ ውጤትና ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን?

**ወ/ሮ በላይነሽ፡-** የተማሪ ዉጤትና የትምህርት ቤቶችን ደረጃቸውን ለማሻሻል ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን በማከናወን ከግል ባለሃብቶች፣ ከግብረ-ሰናይ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ጋር በማቆራኘት በገንዘብ 2,094,768 በጉልበት 17,281,663 በቁሳቁስ 96,835,211 እና በእውቀት 15,994,834 በአጠቃላይ 132,196,476 ሃብት በማሰባሰብ በየትምህርት ተቋማቱ የመማሪያ ክፍል ግንባታ፣ የቴራዞን ንጣፍ ስራዎች፣ የትምህርት ግብዓት ማሟላት ስራዎች፣ ትምህርት ቤቶች የግቢ ማስዋብና የልዩ ፍላጎት የራምፕ ስራዎች፣ የትምህርት አጋዥ ማጣቀሻ መጽሃፍት እንዲሟላ ማድረግና የተማሪ መማሪያ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ማሟላት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በትምህርት ተቋማት ተጨማሪ ግንባታና የተሰሩ ማስፋፊያ ስራዎች ካሉ ቢገልጹልን?

**ወ/ሮ በላይነሽ፡-** በሁሉም የትምህርት ተቋማት ምቹና ማራኪ እንዲሆኑ እድሳትና ጥገና የተደረገላቸው እንዳለ ሆኖ በ2018ዓ/ም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቅድመ አንደኛ ደረጃ እና ፍሬህይወት ቅድመ አንደኛ ደረጃውን የጠበቀ G+2 እና G+4 ህንጻዎች እንዲሁም አፍሪካ ብርሃን አንደኛና መካከለኛ ደረጃ G+4 ህንፃ እና ደጃ/ዘራይ ደረስ G+4 ህንፃ እና መካኒሳ አካባቢ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች G+4 ህንፃዎች በማስገንባት የትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሻሻል እንዲሁም የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል በተጨማሪም ስታንዳርዱን የጠበቀ ተቋማዊ ደረጃ ማሻሻል ተችሏል፡፡



**አዲስ የተገነቡ ትምህርት ቤቶች**

**ልደታ ፋና፡-** የተማሪዎች ምገባና ግብዓት አቅርቦት የተሰሩ ስራች ምን ምን ናቸው?

**ወ/ሮ በላይነሽ፡-** በክ/ከተማ ደረጃ በ19 ቅድመ አንደኛ ደረጃ እና በ20 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች 22,337 ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም (School feeding Program) የምገባ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል የትምህርት ቁሳቁሶች እና የደንብ ልብሶች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህም በመሆኑ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር 0.05% እንዲዲቀንስ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባሻገር ትምህርት ቤቶች ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ወላጆች ለሚመጡ ተማሪዎች በመምህራንና በበጎ አድራጎት ክበብ የሚደረገውን ድጋፍ አጠናክሮ ማቀጠል ተችሏል፡፡ ከቅድመ አንደኛ እስከ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች 239,520 የተማሪ ደብተሮች፤ 21,115 የተማሪ ዩኒፎርሞች፣ 2,322 የመምህራን ጋውን እና 322 የመጋቢ እናቶች ሽርጥ ስርጭት በማከናወን የትምህርት ግብዓቶች ማሟላት ተችሏል፡፡



አዲስ የተገነቡ ትምህርት ቤቶች

**ልደታ ፋና፡-** የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ምን ምን ስራች ተሰሩ?
**ወ/ሮ በላይነሽ፡-** በየውጭ ኢንስፔክሽን ምዘና በስታንዳርድ መሰረት ያደረገ ቅድመ መደበኛ ካሉት 57 ተቋማት መካከል 21 ትምህርት ቤቶች ደረጃ 3 ሲሆኑ 36 ትምህርት ቤቶች ደረጃ 2 እና የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ካሉት 44 ተቋማት መካከል 31 ትምህርት ቤቶች ደረጃ 3 ሲሆኑ 13 ትምህርት ቤቶች 2 ደረጃ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ካሉት 11 ተቋማት መካከል 9 ደረጃ 3 ሲሆን 2 ትምህርት ቤቶች ደረጃ 2 ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህ የሚያሳየው ከደረጃ በታች ተቋም በክ/ከተማ ደረጃ በተደረገው ሱፐርቪዥን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን
**ወ/ሮ በላይነሽ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## የሴቶች ተሳትፎ ለሁለንተናዊ ተጠቃሚነት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክ/ከተማ ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ፅ/ቤት የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ 84/2016 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የከተማዋን ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ሌሎች ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ደህንነታቸውን እንዲጠበቅ፣ እኩልነታቸው እንዲረጋገጥ፣ በልማት በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲያዊ ስርዓትግንባታ እኩል ተሳታፊእና ተጠቃሚ እንዲሆኑና ተቋማት የአካቶ ትግበራ ጉዳይንየልማትአጀንዳመሆኑን በመረዳት መብታቸው እንዲረጋገጥ ያላሰለሰጥረትእያደረገይገኛል፡፡በሴቶች የለዉጥና የዕድገት ፓኬጅ ውስጥ የተቀመጡ ዋና ዋና ትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ ሴቶችን በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም መልካም አስተዳደር ዘርፎች ተሳታፊነታቸዉና ተጠቃሚነታቸዉን የማረጋገጥ ስራዎች እየተሰራ ይገኛል፡፡ ዓለም ዐቀፍ እና አህጉር ዐቀፍ የሕፃናት መብት ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ የሕፃናት ጥበቃ ስርዓት እንዲጠናከርና መብትና ደህንነት በማስጠበቅ፣ የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ እንዲሁምየቀዳማይ ልጅነት እድገት ፕሮግራም በማስተግበር የነገ ሀገር ተረካቢ ህፃናት የወደፊት ህይወታቸው ስኬታማና ለአገራቸው ጠቃሚ ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ፤ የማኅበራዊ ጥበቃፖሊሲውን መሰረት በማድረግ ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ፣ ተሳታፊነታቸውና ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ከችግሮቻቸው ነፃ እንዲወጡ ለአገራቸው ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ይከናወናል፡፡

የዝግጅት ክፍላችን በነዚህና በሌሎች ጉዳዩች ዙሪያ ከሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ሃላፊ ወ/ሮ ሄለን መሀመድ ጋር ቆይታ አድርጓል መልካም ቆይታ፡፡



**ወ/ሮ ሄለን መሀመድ**
**የሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና ፡-** ሴቶችና ህፃናት ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በተመለከተ ቢገልፁልን?
**ወ/ሮ ሄለን መሃመድ፡-** ሴቶችና ህፃናትን ተጠቃሚ ለማድረግ በክፍለ ከተማ ደረጃ በበጀት አመቱ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን ሴቶች በተስማሚ ቴክኖሎጂ 280 ሴቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን ሴቶች እራሳቸውን በኢኮኖሚ እንዲያሻሽሉ በገቢ ማሽገኛ ስራ ተሰማርተው ቤተሰቦቻቸውን እንዲያሻሽሉ 1250 ሴቶችን በግልና በቡድን በማደራጀትና በሲቪል ማህበረሰብ ድጆቶች ጋር በመቀናጀት ሰፊ ስራ ተሰርተዋል፡፡ ህፃናትን በሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ስራ ላይ ተጠቃሚ ለማድረግ ከመንግስት ሰራተኞች 1% ተቆራጭ በማድረግ በአስቸጋሪ በኖሮ ደረጃ ያሉ ህፃናትን የመደገፍ ስራ ተሰርቷል በተጨማሪም በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንዲደገፉ የማድረግ ስራ በተጨማሪም የህፃናት ወላጆች ራሳቸውን ችለው ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተዳድሩ የገቢ ማስገኛ መነሻ ካፒታል ተሰጥቷቸው ወደስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ ኑሯቸውን በጎዳና ላይ ያደረጉ ህፃናትን ከጎዳና በማንሳት ወደቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉና ወደ ተቋም እንዲገቡ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** ሴቶች በስራ እድል ፈጠራ በቀረበላቸው ፀጋዎች ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰሩ ያሉ ያመለካከት ቀረፃ ስራ ቢያብራሩልን?
**ወ/ሮ ሄለን መሃመድ፡-** ሴቶችን የስራ እድል ፈጠራ ከመፍጠር አንፃር ግንዛቤ ለ2850 ሴቶች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ስራ አጥ ምዝገባ LMIS 1895 ሴቶችን መመዝገብ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** የሴቶችንና የህፃናትን ጥቃት ለማስቀረት በጽህፈት ቤታችን ደረጃ እየተሰራ ያለውን ስራ ቢገልፁልን
**ወ/ሮ ሄለን መሃመድ፡-** በክፍለ ከተማ ደረጃ የሴቶችንና የህፃናትን ጥቃት ለመከላከል ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ ድረስ 14 አባላት ያሉት የጥቃት ተከላካይ ኮሚቴ ከህብረተሰቡ የተውጣጣ መቋቋም መቻሉ ፡፡

በተያያዘ የህፃናትንና የሴቶችን ጥቃት ለመከላከል በትምህርት ቤት ደረጃ የጥቃት ተከላካይ ኮሚቴ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን የጥቃ አስከፊነትን በተመለከተ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች ያማከለ የግንዛቤ ስራ መሰራት ተችሏል ።

**ልደታ ፋና ፡-** በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ
**ወ/ሮ ሄለን መሀመድ፡-** የሴቶችን የህፃናት ፣የአረጋዊያንናንና የአካል ጉዳተኞችን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳታፊነታቸውን ለማረጋገጥ በጋራ መስራት ያስፈልጋል

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን
**ወ/ሮ ሄለን መሀመድ፡-** እኔም በጽ/ቤቱ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## የህዝብ ጤና እና የአገልግሎት ጥራት

በአሁኑ ወቅት የማኅበረሰባችንን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተከናወኑ ካሉ የልማት ሥራዎች መካከል የጤናው ዘርፍ ግንባር ቀደሙን ስፍራ ይይዛል። በጤና ተቋሞቻችን የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት ማሻሻል፣ አሠራርን ማዘመንና ተደራሽነትን ማስፋፋት የነገ አገር ተረካቢ ትውልድን ለመገንባት የምናደርገው ጥረት አካል ነው። በዚህ እትማችን በጤና ጣቢያዎቻችን ያለውን ተጨባጭ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ የተመዘገቡ ስኬቶችና የወደፊት አቅጣጫዎችን በተመለከተ ከልደታ ክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ መስፍን ጋር ተከታዩን ቆይታ አድርገናል።

**ልደታ ፋና ፡-** በጤና ጣቢያዎች እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ምን ይመስላል?
**አቶ መስፍን ፡-** በጤና ጣቢያዎቻችን በአሁኑ ወቅት ሰፊና ዘርፈ-ብዙ አገልግሎቶች ለኅብረተሰቡ እየቀረቡ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል፡-

የመከላከያና የሕክምና አገልግሎቶች፡- የእናቶችና ሕፃናት ጤና ጥበቃ፣ የክትባት ፕሮግራሞች፣ የድንገተኛ አደጋ ሕክምና፣ የተላላፊና ሥር የሰደዱ በሽታዎች ክትትልና መድኃኒት ዕደላ በስፋት እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች ናቸው።

የላቦራቶሪና ፋርማሲ አገልግሎት፡- መሠረታዊ የሆኑ የበሽታ መመርመሪያና የላቦራቶሪ ሥራዎች እንዲሁም የመድኃኒት አቅርቦት ሥራዎች ይከናወናሉ።



**አቶ መስፍን በየነ**
**የጤና ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎቱን ለማዘመን በጽ/ቤቱ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን ቢገልጹልን ?
**አቶ መስፍን፡-** የጤና ተቋማቱን አገልግሎት ማዘመን አማራጭ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ ጽ/ቤቱ ሥር ነቀል የአሠራር ለውጦችን ለማምጣት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡-

የዲጂታላይዜሽን ስትራቴጂ ማውረድ፡- አገልግሎቱን ፈጣን፣ ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት ለማድረግ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማቶችን መዘርጋት።

የባለሙያዎችን አቅም መገንባት፡- የሕክምናና የአስተዳደር ሰራተኞች ከአዲሱ ዘመናዊ አሠራርና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲላመዱ ተከታታይ የስልጠናና የዕውቀት ሽግግር (Knowledge Transfer) መድረኮችን ማዘጋጀት።

የአገልግሎት ስታንዳርዶችን ማዘጋጀት፡- ተገልጋዮች በየተቋማቱ ሲመጡ የሚስተናገዱበትን ጊዜ (Waiting Time) ለመቀነስ አዳዲስ የአሠራር መመሪያዎችንና የክትትል ሥርዓቶችን መዘርጋት።

**ልደታ ፋና፡-** በጤና ተቋማት ወረቀት አልባ (Paperless) አገልግሎት በመሰጠቱ የመጣው ውጤት ቢገልጹልን?
**አቶ መስፍን፡-** ወረቀት አልባ አሠራርን (Smart Health System) በጤና ተቋሞቻችን መተግበራችን በትውልድ ቅብብሎሽ ሂደት ውስጥ ትልቅ ምዕራፍ የከፈተ ስኬት ነው። ይህ አሠራር ያስገኛቸው ተጨባጭ ውጤቶች በሚከተለው መልኩ ይገለጻሉ፡-

የጊዜ መቆጠብና ቅልጥፍና፡- ቀደም ሲል ለታካሚዎች ካርድ ፍለጋና ለምዝገባ ይባክን የነበረውን ረጅም ሰዓት በማስቀረት፣ ታካሚው እንደደረሰ በቀጥታ ወደ ሕክምና ባለሙያ እንዲሄድ አስችሏል።

የመረጃ ጥራትና ደኅንነት፡- የታካሚዎች የሕክምና ታሪክ (Medical History) ሳይጠፋና ሳይበላሽ በአንድ ማዕከል ተቀምጦ ስለሚገኝ፣ ሐኪሞች ፈጣንና ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጡ ረድቷል።

የሀብት ብክነትን መቀነስ፡- ለወረቀት፣ ለካርድና ለፋይል መግዣ ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ ወጪ በማስቀረት ተቋማዊ አቅምን አሳድጓል።
የተሻለ የሪፖርት አያያዝ፡- ለዕቅድና ለውሳኔ አሰጣጥ የሚያገለግሉ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን በጥራትና በፈጣን ሁኔታ በኔትወርክ ለማስተላለፍ አስችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**የህክምና ቁሳቁሶችን ከማሟላት አንጻር የተሰሩ ስራዎችን ይግለጹ?

**አቶ መስፍን፡-** በጤና ጣቢያዎች የሚታየውን የቁሳቁስ እጥረት ለመቅረፍ ጽ/ ቤቱ በልዩ ትኩረት እየሰራባቸው ያሉ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

የግዥ ሥርዓትን ማሻሻል፡- ወሳኝ የሆኑ የሕክምና መሣሪያዎችን (እንደ አልትራሳውንድ፣ ዲጂታል ኤክስሬይና የላቦራቶሪ ማሽኖች) በዕቅድና በቅድሚያ ለመግዛት የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል።
የአጋር አካላት ቅንጅት፡- ከበጎ አድራጊ ድርጅቶች፣ ከልማት አጋሮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶችን በድጋፍ የማሰባሰብ ሥራ ተከናውኗል።

የጥገና ሥርዓት መዘርጋት፡- የተበላሹና አገልግሎት ያቋረጡ የሕክምና መሣሪያዎችን በፍጥነት ጠግኖ ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችል የባለሙያዎች ቡድን በማደራጀት የጥገና ሥራዎች በስፋት ተሰርተዋል።

**ልደታ ፋና፡-** ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ?

**አቶ መስፍን፡-** "ጤና አጠቃላይ የልማታችንና የደስታችን መሠረት ነው። የጤና ተቋሞቻችንን አገልግሎት ማዘመንና ማሻሻል የሕክምና ባለሙያዎችን ወይም የጽሕፈት ቤቱን ጥረት ብቻ አይጠይቅም። ይህ የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው።

በመሆኑም፣ የሕክምና ባለሙያዎቻችን የተዘረጉትን አዳዲስ የቴክኖሎጂ አሠራሮች በታማኝነትና በሙያዊ ሥነ-ምግባር በመተግበር ሕዝባችንን በቅንነት እንዲያገለግሉ፤ ተገልጋዩ ማኅበረሰብም የተቋማቱን ንብረቶችና የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማቶች በጥንቃቄ በመጠበቅና አሠራሩን በመደገፍ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።
"እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ ዘመናዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ተደራሽ እናደርጋለን።

**ልደታ ፋና፡-** ስላነበረን ቆይታ በድጋሚ እናመሰግናለን።

**አቶ መስፍን፡-** እኔም በድጋሚ ለዚህቃለ መጠይቅ ስለጋበዛችሁኝ በጽ/ ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።

## ስፖርት ለጤና፣ ለስብዕና እና ለኢኮኖሚ እድገት

የወጣቶችን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግና ስፖርትን ባህሉ ያደረገ ፣ ጤናማ ዜጋ ፣ ብቃት ያለው ስፖርተኛና ህብረተሰብን በመፍጠር የከተማዋን የሰላም ፣ የልማትና የዴሞክራሲ እድገት ማፋጠን ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው።

ወጣቶች በሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ከማንኛውም ዜጋ በላይ ከፍተኛ ድርሻ ሊወጡ የሚችሉ ሀገር ገንቢና ተረካቢ፣ የነገ ተስፋዎችና በአገራችንም ሆነ በክፍለ ከተማችን በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሪ ተዋናይ መሆናቸው እሙን ነው። በተመሳሳይም ስፖርት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጾ ጉልህ ሲሆን በዘርፉ የስራ እድል ከማስገኘት ባሻገር ጤናማና አምራች ዜጋ በመፍጠር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

በልደታ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ፖሊሲውን መሰረት ያደረገ የወጣቶች የልማትና የእድገት ፓኬጅ በመከለስና በመተግበር ወጣቶች በኢኮኖሚያዊ፤ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተቋምና ከሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት ወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር እና የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ እንዲሁም የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንዲገነቡና ሁለገብ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ በርካታ ተግባራትን ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህም ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

ወጣቶች በሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ከማንኛውም ዜጋ በላይ ከፍተኛ ድርሻ ሊወጡ የሚችሉ ሀገር ገንቢና ተረካቢ፣ የነገ ተስፋዎችና በአገራችንም ሆነ በክፍለ ከተማችን በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሪ ተዋናይ መሆናቸው እሙን ነው። በተመሳሳይም ስፖርት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጾ ጉልህ ሲሆን በዘርፉ የስራ እድል ከማስገኘት ባሻገር ጤናማና አምራች ዜጋ በመፍጠር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

በልደታ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ፖሊሲውን መሰረት ያደረገ የወጣቶች የልማትና የእድገት ፓኬጅ በመከለስና በመተግበር ወጣቶች በኢኮኖሚያዊ፤ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተቋምና ከሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት ወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር እና የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ እንዲሁም የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንዲገነቡና ሁለገብ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ በርካታ ተግባራትን ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህም ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

ወጣቶች የአንድ ሀገር የዛሬ ኃይል እና የነገ ተስፋ ስለሆኑ በአካል፣ በአእምሮ፣ በስብዕና እና በኢኮኖሚ አቅማቸው እንዲጎለብት የማድረግ መንግሥትና ዋና ተግባር ነው። በዚህ ረገድ የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ያከናወናቸው ተግባራት ወጣቶችን በብዙ ዘርፎች ለማብቃት የተደረገ ሰፊ ስራ ተሰርቷል።
ከአካል ብቃት ማሻሻል እስከ ስራ እድል ፈጠራ፣ ከስፖርት ማህበራት ማጠናከር እስከ የህጋዊ አሰራር ስርዓት መዘርጋት ድረስ የተከናወኑ ስራዎች በወጣቶች ህይወት ላይ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣታቸውን ያሳያሉ።

## የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፡ ጤናማ ዜጋ ለመፍጠር የተጣለ መሠረት

የአካል ብቃት መርሃ ግብሮች በወጣት ማዕከላት፣ በትምህርት ቤቶች እና በመንግሥትና በግል ተቋማት በስፋት ተካሂደዋል። የማለዳ ስፖርት መርሃ ግብሮች በተከታታይ መካሄዳቸው የአካል ብቃት ባህል እንዲዳብር አድርጓል።

ዛሬ በብዙ አካባቢዎች የሚታየው የጠዋት የእግር ጉዞ፣ የሩጫ እና የማህበራዊ የአካል እንቅስቃሴ ባህል የእነዚህ ፕሮግራሞች ውጤት ነው። ይህም ወጣቶችን ከህመም፣ ከአልባሌ ጊዜ አጠቃቀም እና ከተለያዩ ሱሶች ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ወጣቶች ጤናማ ከሆኑ ብቻ በትምህርት፣ በሥራ እና በማህበራዊ ሕይወት ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ የአካል ብቃት ፕሮግራሞችን የጤና መሠረት አድርገን እየሰራን ነው።



**አቶ ግዛው አለሙ**
**የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ሃላፊ**

## የስፖርት ማዘውተሪያዎች፡ የወጣቶች ተስፋ ማዕከላት

በየአካባቢው የተገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ለወጣቶች ብዙ ጥቅሞችን እያስገኙ ይገኛሉ። እነዚህ ተቋማት የአካል ብቃት ማዳበሪያ ብቻ ሳይሆኑ የመገናኛ፣ የትስስር እና የተስፋ ማዕከላት ሆነዋል።ብዙ ወጣቶች ነፃ ጊዜያቸውን በጤናማ መንገድ እንዲያሳልፉ፣ በስፖርት ውድድሮች እንዲሳተፉ እና ተሰጥኦአቸውን እንዲያዳብሩ እድል  ሲሆን በተለይ ወጣቶችን ከአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚነት፣ ከወንጀል እና ከሌሎች አሉታዊ ተግባራት በማራቅ የማህበራዊ ሰላም ግንባታ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው።

## ስፖርትና ስብዕና ግንባታ

ስፖርት ተግሣጽን፣ ትዕግሥትን፣ የቡድን ሥራን እና አመራርን የሚያስተምር ትልቅ ትምህርት ቤት በመሆኑ ባሉት  በስፖርት ማህበራት ውስጥ የሚሳተፉ ወጣቶች በውሳኔ አሰጣጥ፣ በአመራር እና በድርጅታዊ አሰራር ልምድ እያገኙ ናቸው። ይህም ለወደፊት ሙያዊ እና ማህበራዊ ሕይወታቸው ወሳኝ ካፒታል ነው።

## ስፖርት እንደ የስራ እድል ምንጭ

በብሪሞ ሜዳ የተገነቡ ሱቆች ተጠናቀው ለኪራይ መቅረባቸው ለወጣቶች የገቢ ምንጭ ሆነዋል። ብዙ ወጣቶች በንግድ ሥራ ተሳትፈው ራሳቸውን ከመቻል በተጨማሪ የሃብት አሰባሰብ ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት እና ለተለያዩ ድርጅቶች በማቅረብ የፋይናንስ አቅማቸውን ማሳደግ የቻሉ ሲሆን ይህ በቀጣይ ተጨማሪ የስራ እድሎችን ለመፍጠር የሚያግዝ ጠንካራ መሠረት ነው።

## የወጣቶች የሥራ እድል ግንዛቤ መፍጠር ለኢኮኖሚያዊ እድገት መሠረት ነው

ወጣቶች የአንድ ሀገር ዋነኛ የሰው ኃይል ሀብት ናቸው። በመሆኑም ስለ ሥራ እድሎች፣ ስራ ፈጠራ፣ የሙያ ስልጠናዎች እና የንግድ ሥራ መጀመሪያ አማራጮች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።የሥራ እድል ግንዛቤ መፍጠር ወጣቶች ችሎታቸውን እንዲያውቁ፣ እንዲያዳብሩ እና በሥራ ገበያው ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያግዛል። በተጨማሪም ራሳቸውን በራሳቸው ለመቻል እና ለሌሎችም የሥራ እድል ፈጣሪ እንዲሆኑ ያበረታታቸዋል።በመሆኑም የመንግሥት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶችና የማህበረሰብ ተቋማት በቅንጅት በመሥራት ወጣቶች የሥራ እድሎችን እንዲያውቁና እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችሉ መድረኮችን ማዘጋጀት ተችሏል።



**የስብዕና መገንቢያ ማዕከላት**

## የታዳጊዎች ስፖርት ውድድር ለተሻለ ትውልድ ግንባታ

ስፖርት ከጤና ጥበቃ ባለፈ የወጣቶችን ስነ-ምግባር፣ ተግሣጽ እና የቡድን ስራ ባህል በማጎልበት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በዚህ ረገድ የታዳጊዎች ስፖርት ውድድሮች የተሰጥኦ ማሳያና የወደፊት ስፖርተኞች መፍለቂያ መድረክ ናቸው።ውድድሮቹ ታዳጊዎች በጤናማ ውድድር እንዲሳተፉ፣ ችሎታቸውን እንዲያሳዩ እና በስፖርት መስክ ያላቸውን ተሰጥኦ እንዲያዳብሩ እድል ይሰጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ የአካል ብቃትን ከማሳደግ ጎን ለጎን ከአደገኛ ባህሪያት እንዲርቁ ያግዛሉ።ስለዚህ የታዳጊዎች ስፖርት ውድድሮችን ማበረታታትና ማስፋፋት ጤናማ፣ ተግሣጽ ያለው እና ተሰጥኦውን ያዳበረ ትውልድ ለመፍጠር አስፈላጊ ነው።



**በክ/ከተማ የተገነባ የስፖርት ማዘውተሪያ እና በጋራ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ሲደረግ**

## የህጋዊ አሰራር ማጠናከር

በመመሪያና በደንብ መሠረት የማይሰሩ የስፖርት ንግድ ቤቶች ላይ የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎች ዘርፉን ከህገ-ወጥ አሰራር በማጽዳት በዘርፉ ውስጥ ፍትሃዊ ውድድር እንዲኖር፣ የአገልግሎት ጥራት እንዲሻሻል እና የወጣቶች ተጠቃሚነት እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል።

የተመዘገቡት ውጤቶች አበረታች ቢሆኑም ወደፊት የስፖርት ንግድ ቤቶች ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር፣ ለስራ እድል ፈጠራ ተጨማሪ ፋይናንስ መመደብ፣ የስፖርት ማህበራትን በስልጠና ማብቃት እና ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ያስመዘገበው አፈጻጸም ስፖርት የመዝናኛ ብቻ ሳይሆን የጤና፣ የስብዕና ግንባታ፣ የማህበራዊ ትስስር እና የኢኮኖሚ እድገት መሳሪያ መሆኑን በተግባር በማረጋገጥና የተገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ጤናማ፣ ተግባቢ፣ ስራ ፈጣሪ እና ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ ለመፍጠር እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ በመሆኑ ይህ ጥረት በቀጣይነት ሲጠናከር የወጣቶችን አቅም በማሳደግ ለከተማውና ለሀገሪቱ ልማት የላቀ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ጥርጥር የለውም።

**የስፖርት ምክር ቤት ስብሰባ ( ጉባዔ)**

## ተፈጥሮአዊ፣ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቻችን ለብልፅግናችን!

ኢትዮጵያ በብዝኃነት የተዋበች፣ የበርካታ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ ሀገር ናት። ይህም ሀገራችንን የበርካታ ባህላዊ እሴቶች፣ ቋንቋዎች፣ ታሪኮችና የአኗኗር ዘይቤዎች ባለቤት ከማድረጉም በላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን አስችሏታል።

የልደታ ክፍለ ከተማም ይህን ሀገራዊ ብዝኃነት የምታንፀባርቅ አካባቢ ሲሆን፣ በውስጧ ያሉ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ኪነ-ጥበባዊ እሴቶች ለልማትና ለማህበራዊ ትስስር ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። “ልደታ ፋና” በዚህ እትሙ ከልደታ ክ/ከተማ ባህልና ኪነ-ጥበብ ጽ/ቤት ኃላፊ ከአቶ አንተነህ በፍቃዱ ጋር ቆይታ በማድረግ የጽ/ቤቱን ተግባራት፣ ስኬቶችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ዳሳለች ተከታተሉን መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** የባህልና ኪነ-ጥበብ ዘርፍ ለአንድ ከተማ ልማት ያለውን ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፡-** ባህልና ኪነ-ጥበብ የማንነት መገለጫዎች ብቻ ሳይሆኑ የኢኮኖሚ እድገት፣ የሥራ ፈጠራ፣ የማህበራዊ ትስስርና የሀገር ገጽታ ግንባታ መሠረቶች ናቸው። ስለዚህ ዘርፉን ማጠናከር ማለት የልማት መሠረትን ማጠናከር ማለት ነው።



**አቶ አንተነህ በፍቃዱ**
**የባህልና ኪነ-ጥበብ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤታችሁ በአሁኑ ወቅት ምን ዓይነት አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፡-** ጽ/ቤታችን ተለያዩ ዓይነት አገልግሎቶችን ለማህበረሰቡ ይሰጣል። ከእነዚህም መካከል የእደ-ጥበብ ማህበራትን ማደራጀት፣ ሙያዊ ድጋፍና ሥልጠና መስጠት፣ የባህልና የእደ-ጥበብ ምርቶች አውደ ርዕይ ማዘጋጀት፣ የቱሪዝም መረጃ አገልግሎት መስጠት አገልግሎቶች ይገኙበታል።

**ልደታ ፋና፦** የእደ-ጥበብ ዘርፍን ለማጠናከር ምን ዓይነት ሥራዎች ተሰርተዋል?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፦** በእደ-ጥበብ ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች በማህበራት እንዲደራጁ ድጋፍ አድርገናል። ሙያዊ ሥልጠናዎችን ሰጥተናል፣ አውደ ርዕዮችን አዘጋጅተናል፣ በዚህም አምራቾች ምርታቸውን እንዲያስተዋውቁና የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ አስችለናል።

**ልደታ ፋና፦** ቅርሶችን በመጠበቅና በማስተዋወቅ ረገድ የተሠሩ ሥራዎች ምንድናቸው?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፦** በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን በመለየት እና በመመዝገብ ጥናት፣ ጥበቃና እንክብካቤ እያደረግን ነው። ይህም ቅርሶቻችን ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፉ ያግዛል።

**ልደታ ፋና፦** በባህል ዙሪያ የሚከናወኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፦** አዎ፣ ጠቃሚ የባህል እሴቶችን በማህበረሰቡ ዘንድ ለማስረፅ በተከታታይ እንሠራለን። አሉታዊ መጤ ባህሎችን በመከላከል፣ ጎጂ ልማዳዊ አሠራሮችን በመቀየርና ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር የተሻለ ማህበራዊ ለውጥ እንዲመጣ እንሠራለን።

**ልደታ ፋና፦** የባህል በዓላትና ሁነቶች ምን ያህል አስተዋፅኦ አላቸው?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፦** የባህል በዓላት የአንድነት፣ የመቻቻልና የብዝኃነት እሴቶችን የሚያጠናክሩ መድረኮች ናቸው። የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀንን ጨምሮ የተለያዩ በዓላትን በማክበር ህዝቦች እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁና እንዲቀራረቡ እናደርጋለን።

**ልደታ ፋና፦** ተቋሙ ገዥ ትርክትን በማስረጽ ረገድ ምን አስተዋጾ አበረከተ?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ ፦** ሰላምና አብሮነትን፣ ህብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ ገዥ ትርክትን፣ ህብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ላይ የሚያተኩሩ የተለያዩ የኪነ ጥበብ ስራዎችን በመቅረባቸው ሁሉም ስለሀገሩ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ስሜት መፍጠር ተችሏል።

**ልደታ ፋና፦** በቀጣይ የጽ/ቤቱ ዋና ትኩረት ምን ይሆናል?

**አቶ አንተነህ በፍቃዱ፦** ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በማልማትና በማስተዋወቅ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ እንሠራለን። ባህልና ቱሪዝም ለሀገራችን ብልፅግና የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ የተቀናጀ ጥረት እናደርጋለን።

ከአቶ አንተነህ በፍቃዱ ጋር ባደረግነው ቆይታ እንደተረዳነው የባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ዘርፍ የማንነት መገለጫ ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለማህበራዊ አንድነትና ለትውልድ ግንባታ ወሳኝ ድርሻ አለው። በመሆኑም ያሉንን ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶች በአግባቡ ጠብቀን፣ አልምተንና አስተዋውቀን ለሀገራችን ብልፅግና መጠቀም የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

## የቅንጅት ዉጤት

ከተማችን እያሳካች በምትገኘዉ የልማትና የብልጽግና ጉዞ ላይ የራሳቸዉን ሚና እየተወጡ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ይገኛሉ። እነዚህ ተቋማት ታዲያ በማህበረሰቡ የየእለት እንቅስቃሴ ላይ ተግዳሮት ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮችን በተሰጣቸዉ እቅድና ተግባር መሰረት ወደ ኃላ ሳይሉ ዉጤታማ ስራ እየሰሩ ነዉ። እኛም ለዛሬ በልደታ ፋና መጽሄታችን የምንዳስሰዉ ታዲያ የመንግስትን ተልዕኮ ተቀብሎ ዉጤታማ ስራ ከሚሰራ ተቋም መካከል የልደታ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤትን ትኩረት በማድረግ ነዉ። ይህ ተቋም በስሩ የሚገኙ ተቋማትን በማዘጋጃ ቤታዊ ክንዉን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለክፍለ ከተማዉ ነዋሪ በዘመነ አገልግሎት አሰጣጥ መሰረት በማድረግ በያዝነዉ 2018 በጀት አመት ዉጤት ተኮር ተግባር ማከናወን ችሏል።

በእዚህ ዙሪያ የዝግጅት ክፍላችን ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ ያየህ ከተማ ጋር አጭር ቆይታ አድርጓል በንባብ ተከታተሉን መልካም ቆይታ።

**ልደታ ፋና፦** ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን

**አቶ ያየህ ከተማ፦** እኔም አመሰግናለሁ

**ልደታ ፋና፦** እንደ መጀመሪያ ጥያቄ በበጀት አመቱ ተቋሙ በስሩ ያሉ ተቋማትን ከማስተዳደር አንጻር ምን አይነት ስራዎች እንደሰራ ቢያነሱልን?

**አቶ ያየህ ከተማ፦** ተቋሙ በስሩ ተቋማትን ከማስተዳደር አንጻር ዘርፈ ብዙ ስራዎችን መስራት ችሏል፡ ዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የተለያዩ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማለትም የጽዳት ጽ/ቤት፣ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት፣ የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽንን የሚመራ፣የሚቆጣጠር፣ የሚያስተባብርና ክትትልና ድጋፍ የሚያደረግ ተቋም ነዉ። የህዝብ እድገት እና አገልግሎት ፍላጎት ሊመጥን የሚችል ዘመናዊ ቀልጣፋ እንዲሁም ዉጤታማ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ተግባራዊ መሆናቸዉን የመከታተልና የመደገፍ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና የመስጠት ክፍለ ከተማችንን ጽዱ ዉብና ማራኪ ለማድረግ የማህበረሰቡና የሚመለከዉ አካል ከጎናችን በመሆን እንዲሰራ በግንዛቤ ስርጸት ዉጤት ማምጣት ችለናል። ዘመኑ በሚከተለዉ የቴክኖሎጂ አሰራር በመጠቀም የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት እንግልትን መቀነስም ሌላኛዉ ስራችን ነዉ።

እነዚህን ስራዎች ስንሰራ ግን ቅንጅታዊ አሰራራችንን በማጠናከር ነዉ፡ ፡ በቅንጅት የሰራናቸዉ ስራዎችን በዝርዝር ስንመለከት

**ከኤሌክትሪክ አንፃር ፦** የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች ቅያሪ 3638፣ መቀየር ያለባቸው ያረጁ እና የረገቡ/ለአደጋ የተጋለጡ/ የኤሌክትሪክ ገመድ 40.5 በኪሜ፣በተደጋጋሚ መብራት የሚጠፋባቸው ቦታዎች 2 ፣የመስመር ብልሽት ጥገና 12 ፣9 ትራንስፎርመር ቅድመ ጥገና ፣101 የረገቡ ገመዶችን መወጠር ፣ከፍተኛ መስመር ቅድመ ጥገና 24.98 ኪ.ሜ፣ 112 ትራንስፎርመር ቅድመ ጥገና ስራ ተሰርቷል። ከዚህ በተጨማሪ 0.8 ኪ.ሜ ከፍተኛ መስመር ዝርጋታ ስራ ተሰርቷል ።556 አዲስ ደንበኛ ማገኛኘት፣ 4.85 ከፍተኛ መስመር መልስ ግንባታ ስራ ተሰርቷል።70 ኤሌክትሪክ ቆጣሪ ማስገባት፣ 70 የውሃ ቆጣሪ ማስገባት እና 2 ትራንስፎርመር አዲስ እንዲገጠም የማደረግ ችለናል።

ሌላዉ ያረጁ ፖሎችን መቀየር፣በእሳት ቃጠሎ የወደመና የዳነ ንብረት የማቀናጀት ስራ ተሰርቷል። ተረጂነትንና ልመናን መቀነስ ላይ ሰብአዊ ድጋፍ በራስ አቅም ለሉአላዊነት በሚል ተረጂነትንና ልመናን ለመቀነስ በሚደረጉ ስራዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል። በክፍለ ከተማ ስታንዳርዱን የጠበቀ አንድ የማከማቻ መጋዘን ማዘጋጀትና የማከማቻ መጋዘን ግንባታ 75% ማድረስ ተችሏል።

ምግብ ነክ የሆኑና እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ሀብት መሰብሰብ ከጠቅላላው መሰብሰብ ካለበት የመጠባበቂያ ክምችት (ምግብ ነክ) በቆሎ ዱቄት እና ፍርኖ ዱቄት) ዘይት ፣ ፓስታ ፣የዕለት ደራሽ አልባሳት ፣ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ክምችት(ሳሙና፤የገላ ሳሙና፤ሶፍት) የቤት ቁሳቁስ ክምችት በአጠቃላይ በገንዘብ ሲተመን **2,944,925.00** ብር ተሰብስቧል።



**አቶ ደየህ ከተማ**
**የስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመርያ ለቃለ- ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እያመሰገንኩ ስሞትን ያስተዋውቁልን
**አቶ ደየህ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጠራችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ ደየህ አለም እባላለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ የሚያከናውናቸው ተግባራትን ቢገልጹልን
**አቶ ደየህ፡-** የከተማው ስራ አስኪያጅ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረት ተጠሪነቱ ለከተማው ከንቲባ ሆኖ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈጻሚ ነው። በመሆኑም በአዋጁ መሰረት የሚተሉት ስልጣን፣ ኃላፊትና ተግባር ይኖሩታል። ተጠሪነታቸው ለስራ አስኪያጅ የሆኑ አስፈጻሚ አካላትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤የተቋሙ ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት እንዲቋቋሙ ወይም ሌሎች የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በስራ ላይ እንዲውሉ ለከንቲባው ሃሳብ ያቀርባል፤ ከተማ አቀፍ እና ክፍለ ከተማ ዘለል የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎትን በተመለተ ዕቅድና በጀት ለከንቲባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናቀር ለከንቲባው ያቀርባል ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤ስሉጥ፣ ግልጽና ፍትሃዊ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት መስጠቱን ያረጋግጣል፤ የማዘጋጃቤታዊ አልግሎትን የሚመለከት የፖሊስ ሃሳብ እና የህግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከንቲባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤ ለስራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣኑ በከፊል ለምክትል ስራ አስኪያጅ፣ የራሱ ተጠሪ ለሆነ ኃላፊ ወይም አስፈጻሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ በቻርተሩ የተሰጡትን ሌሎች ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም በከንቲባው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

**ልደታ ፋና፡-** በህብረተሰቡ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የተሰሩ ስራዎችን ይግለጹልኝ?
**አቶ ደየህ፡-** ከኤሌክትሪክ አገልግሎት አንጻር፡- 2ኪ.ሜ መቀየር ያለባቸው ያረጁ እና የረገቡ /ለአደጋ የተጋለጡ/የኤሌክትሪክ ገመድ መቀየር፣240 የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች መቀየር፣240 አዲስ ፖል መትከል የመቀየር፣2 የአዲስ ትራንስፎርመር የመትከል፣2 የተቃጠለ /የተበላሸ/ ትራንስፎርመር ጥገና ማድረግ ፣110 አዲስ ቆጠሪ ጥያቄ የማስገባት፣2 በተደጋጋሚ መብራት የሚጠፋባቸው ቦታዎች የማስተካከል፣1የሃይል ጭማሪ የማስተካከል፣120 የመስመር ብልሽት ጥገና፣1የትራንስፎርመርና የቆጣሪ ማንሳት ስራ፣1 የትራንስፎርመር እና ቆጣሪ ቦታ ማዘዋወር ስራ፣2 የወደቀ ፖል ማስተካከል፣1 የሃይል ማነስ ያለባቸው ቦታዎች የማስተካከል ስራ ተሰርቷል

**ልደታ ፋና፡-** በህብረተሰቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በአግባቡ ከመፍታት አንጻር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ምን ይመስላሉ?
**አቶ ደየህ፡-** ከእሳት አደጋ ስጋት አንፃር የተሰሩ ስራዎች ለጐርፍ ተጋላጭ ቦታዎች ለሁለቱም ቦታዎች ላሉበት ወረዳ አስተዳደር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው፤11 ለእሳት አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች እና ተቋማት በመለየት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፤የቅድመ አደጋ መከላከል ስራዎች ለ1365 አባላት በአደጋ ስጋት ቅነሳ በአደጋ እና በድህረ አደጋ አገልግሎት ተሰጥቷል፤7 የደረሰ አደጋዎች ሳይስፋፋ መቆጣጠር ተችሏል፤2 ቦታዎች ለአገልግሎት ተቆፍረው በተተው ጉድጓዶች ለይቶ ምላስ በመስጠት ለሁለቱም ቦታዎች ላሉበት ወረዳ አስተዳደር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፤ተረጅነት እና ድህነት ቅነሳ ላይ ቅድመ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል በተለይም ምግብ ነክ ምግብ ነክ ያልሆኑ መገልገያ እቃዎችንና የንጽና መጠበቂያን ከየወረዳው በማሰባሰብ ወደ መጋዘን በማስገባት በዚህ ወር ብቻ ግምታቸው ከ200,000.00 (ከሁለት መቶ ሺህ) ብር በላይ የሆነ ተሰብስቧል።

ከውሃና ፍሳሽ አንፃር፡- 9 ኪ.ሜ የውሃ መስመር ዝርጋታ ማዘጋጀት ተችሏል፣በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአይን የሚታይ የውሃ ብክነት ለመቀነስ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆኑ የመለስተኛ መጋቢ መስመሮችን ጥገና ስራ ተሰርቷል፤62 ህጋዊ ሰነድ ለሚያቀርቡ አዲስ ደንበኞች የውሃ መስመር ቅጥያ በመፈጸም የውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤3 ጥያቄ ለሚያቀርቡ ነባር ደንበኞች የውሃ መስመር ማሻሻያ በመከናወን የአገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤120 ጥያቄ ለሚያቀርቡ ነባር ደንበኞች የውሃ መስመር ማዘዋወሪያ በመፈጸም የውሃ ተጠቃሚ ማድግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?
**አቶ ደየህ፡-** ተቋማችን በቅንጅታዊ አሰራር ከተጠሪ ተቋማት ጋር ሆኖ በማስከበር በተለይም ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን በማሳለጥ እየሰራ ይገኛል በአደጋ ቅነሳ እና ቅድመ መከላከል ጋር በተያያዘ ለጐርፍ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ከቦታው በማንሳ እና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል፤ከመብራት ጋር በተያያዘ ያረጁ ፖሎችን እና ገመዶችን ለመቀየር በተጨማሪም የመብራት እንዳይኖር በማስተባበር ከተቋሙ ጋር እየሰራ ይገኛል፤ ከተማችን ውብ እና ጽዱ ከማድረግ አኳያ ሞዴል ወረዳ እና ሞዴል ብሎክ ከመፍጠር ጋር ተያይዞ በመመዘኛ መስፈርት መሰረት እንዲለዩ ያደረግን ሲሆን ሞዴል ያልሆኑ ብሎኮችን ሞዴል ለማድረግ ነዋሪ ማህበረሰቡን በማሳተፍ በርብርብ ላይ እንገኛለን፤ ሲቪል ምዝገባ እና ነዋሪዎች አገልግሎት የመልካም

አስተዳደር ችግሮቹን ለምቅረፍና ለመቆጣጠር ሁሉንም ነዋሪዎች በሲቪል ምዝገባ እና ነዋሪዎች አገልግሎት መታወቂያ እንዲያወጡ በብሎክ ጭምር እየተገበርን እንገኛለን።

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራርያ ከልብ እናመሰግናለን ።
**አቶ ደየህ ፡-** እኔም በጽ/በቱ ስም አጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

## በጎ ፈቃድ ከተግባር ወደ ባህል

ዘላቂ ልማትና መልካም አስተዳደር የሚረጋገጡት በመንግሥት ጥረት ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ነው። ይህንን እውነታ በተግባር ካረጋገጡ ተቋማት መካከል በልደታ ክፍለ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት አንዱ ነው። ጽሕፈት ቤቱ በከተማ አስተዳደሩ የተሰጠውን ተልዕኮ በማሳካት ረገድ ህዝቡን በልማት፣ በሰላምና ፀጥታ፣ በበጎ ፈቃድ እና በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ በማሳተፍ ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል።



**አቶ ፍራኖል ሞሲሳ**
**የህብተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሃላፊ**

ብሎክን ማዕከል ያደረገ የህዝብ ተሳትፎ፡- ጽሕፈት ቤቱ የብሎክ አደረጃጀትን በማጠናከር ነዋሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ችግሮችን እንዲለዩ፣ ቅድሚያ እንዲሰጡና በጋራ መፍትሄ እንዲያመጡ አድርጓል። ይህም ችግሮችን ከምንጫቸው በመፍታት የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጠቃሚ መድረክ ሆኗል።

በዚህ አሰራር ነዋሪዎች ስለ ከተማቸው የሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ መረጃ የማግኘት፣ ሀሳብ የማቅረብ እና በውሳኔ ሂደቶች የመሳተፍ እድል አግኝተዋል። ይህም ለከተማው ነዋሪ በሚሰሩ ልማቶችና በእያንዳንዱ የልማት ተግባር ላይ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን እና ፍትሃዊነትን ለማጠናከር አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በክፍለ ከተማው የበጎ ፈቃድ ተግባራት በስፋት ተካሂደዋል። በአረንጓዴ ልማት፣ በደም ልገሳ፣ በማጠናከሪያ ትምህርት፣ በአጫጭር የክህሎት ስልጠናዎች፣ በአካባቢ ጽዳት፣ በጎርፍ መከላከል እና በትራፊክ ደህንነት ዘርፎች ህብረተሰቡ በንቃት ተሳትፏል። በተለይም "ሙያዬን ለሀገሬ" በተሰኘው ፕሮግራም የህክምና፣ የህግ፣ የምህንድስና፣ የትምህርት እና የስነ-ጥበብ ባለሙያዎች በሙያቸው ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። ይህም የእውቀትና የልምድ መጋራት ባህልን አጠናክሯል።



**በጎ ፈቃድ አገልግሎት**

በክፍለ ከተማው በጎ ፈቃደኞች በስፋት ከተሳተፉባቸው ተግባራት መካከል የማዕድ ማጋራት መርሃ ግብር ቀዳሚ ነው። በዚህ ፕሮግራም በቀን አንዴ እንኳን ምግብ ለማግኘት የሚቸገሩ ዜጎች የምግብ ድጋፍ አግኝተዋል። በበዓላት ወቅትም ዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ ሰራተኞችና አቅመ ደካማ ዜጎች ማዕድ እንዲጋሩ ተደርጓል። ይህ ተግባር ከምግብ ድጋፍ በላይ የመተሳሰብና የማህበራዊ አንድነት እሴቶችን ያጠናከረ ነው።



**ማዕድ ማጋራት ሲካሄድ**

በ2018 በጀት ዓመት ውስጥ ከተመዘገቡ ውጤታማ ተግባራት መካከል የአቅመ ደካማ ዜጎችን የመኖሪያ ቤት ማሻሻል ተጠቃሽ ነው። አሮጌ መኖሪያ ቤት ፈርሶ በዘመናዊ መልኩ በድጋሚ ተገንብቶ ለተጠቃሚዎች ተረክቧል።ለዚህ ፕሮጀክት የባለሀብቶችና የተቋማት ድጋፍ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የተገነቡ ቤቶች ዜጎች ከዝናብ፣ ከብርድ እና ከጤና ችግሮች እንዲጠበቁ አስችሏል።

## በሶስቱ ዘርፎች የተመዘገቡ ለውጦች

በፖለቲካ ዘርፍ፡- የሰላምና ፀጥታ ስራዎች በመጠናከራቸው ነዋሪዎች በሰላም ወጥተው በሰላም የሚመለሱበት አካባቢ ተፈጥሯል። በብሎክ አመራር ምርጫዎችም ህዝቡ በቀጥታ ተሳትፎ አድርጎ የሚወክለውን አመራር በነፃነት መምረጥ ችሏል።

**በኢኮኖሚ ዘርፍ፡-** የማዕድ ማጋራትና የቤት ግንባታ ፕሮግራሞች በተጠቃሚዎች ላይ የነበረውን ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመቀነስ አስችለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ የህብረተሰቡን ሀብትና አቅም በማስተባበር በመንግስት ላይ የሚደርሰውን ጫና ለመቀነስ ተችሏል።

**በማህበራዊ ዘርፍ፡-** በህብረተሰቡ ውስጥ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍና የአብሮነት እሴቶች በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክረዋል። በጎ ፈቃደኝነትም ከጊዜ ወደ ጊዜ የማህበረሰቡ ባህል እየሆነ መጥቷል።

በአጠቃላይ የልደታ ክፍለ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት ያስመዘገበው ውጤት የህብረተሰብ ተሳትፎ ለልማት ያለውን ወሳኝ ሚና በግልጽ አሳይቷል። የቤት ግንባታ፣ የማዕድ ማጋራት፣ የሰላምና ፀጥታ ስራዎች እና የበጎ ፈቃድ እንቅስቃሴዎች በነዋሪዎች ህይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ችለዋል። ይህ ስኬት የሚያሳየው ልማት የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የህዝብ ተሳትፎ ውጤት መሆኑን ነው።

## ውብ፣ ምቹና ጽዱ ልደታ

አዲስ አበባ የፌደራል መንግስት መቀመጫ፣ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩበት፣ ለስራና ለጉብኝት የሚመላለሱበት የሃገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማዕከል ስትሆን በተጨማሪም የአፍሪካ ህብረት መቀመጫና በርካታ የዲፕሎማቲክ ህብረተሰብ የሚገኝባት ከተማ ነች። በመሆኑም ከተማዋን ሊመጥኑ የሚችሉ መናፈሻዎች፣ አረንጓዴ ውብና ማራኪ ቦታዎች፣ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች እንደሚያስፈልጓት ይታመናል።

የልደታ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት የተፋሰስ እና አረንጓዴ ቦታዎችን ልማት፣ እንክብካቤና አስተዳደር ስራዎች ላይ ትኩረት በመስጠት በዋነኝነትም በክፍለ ከተማው የሚገኙ ክፍት አረንጓዴ ቦታዎችን፣ መንገድ አካፋይ፣ መንገድ ዳርቻ፣ አደባባዮችን፣ ደሴቶችን፣ ፓርኮችን፣ ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎችን እና የህዝብ መጸዳጃ ቤት በማስተዳደር እና በማልማት ለነዋሪዎች ተደራሽ ማድረግ ዋነኛ ተግባሩ ሲሆን በተጨማሪም ህብረተሰቡን፣ ባለድርሻ አካላት እና ባለሀብቱን በማስተባበር የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። በመሆኑም የልደታ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት የአረንጓዴ ልማት ስራውን ለማስቀጠል የህብረተሰቡ ሚና የላቀ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ህብረተሰቡን አሳታፊ የሚያደርግ እቅድ በማቀድ በ2018 በጀት ዓመት ወደ ስራ የገባ ሲሆን በዚህም በርካታ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

በመሆኑም ልደታ ክፍለ ከተማ ባለፉት ዓመታት ከነበራት ገጽታ እጅግ ባማረ መልኩ በኮሊደር ልማቱ ያሸበረቀችና ንጹህ፣ ማራኪና አረንጓዴ ቦታዎች የሚታዩበት፣ በየቦታው የልጆች መጫወቻና ማረፊያ ወንበሮች የተሰሩባት፣ ፅዱ የመጸዳጃ ቤቶችን በቅርብ ርቀት የሚያገኙባት፣ ፕላዛና የመጫዎቻ ቦታዎችን አካታና መንገዶቿን ለእግረኛው ሰፋ አድርጋ የሰራች ውብ፣ ምቹና ጽዱ የከተማዋ ክፍል ሆና ትገኛለች። ለዚህም ጽ/ቤቱ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።የዝግጅት ክፍላችን በነዚህ ጉዳዩች ዙሪያ ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ወ/ሮ ትዕግስት ዋለልኝ ጋር ቆይታ አድርጓል መልካም ንባብ።



**ወ/ሮ ትዕግስት ዋለልኝ**
**የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና ፡-** አረንጓዴ አሻራን ከማስቀመጥ አንጻር የህብረተሰቡ ሚና ምን እንደሆነ ቢገለጽልን?

**ወ/ሮ ትእግስት ዋለልኝ፡-** የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ስኬታማ እንዲሆን የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ እና መሰረታዊ ነው። ህብረተሰቡ ከችግኝ ተከላ ጀምሮ እስከ እንክብካቤ ድረስ ያለውን ሂደት በባለቤትነት ሲመራው የሀገርን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ይቻላል።ከአረንጓዴ አሻራ አንጻር የህብረተሰቡ ዋና ዋና ሚናዎች በችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር ላይ በንቃት መሳተፍ አለባቸው፤የተተከሉ ችግኞችን የመንከባከብ እና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።በአጠቃላይ፣ የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ በዘላቂነት እንዲቀጥል ህብረተሰቡ እንደ አንድ ዜጋ ብቻ ሳይሆን እንደ ዋና ባለቤት በመሆን የተፈጥሮ ሚዛኑ የተጠበቀ አካባቢን የመፍጠር ትልቅ አደራ አለባቸው።

**ልደታ ፋና፡-**የበጋ ችግኝ እንክብካቤ በተመለከተ የተሰራ ስራ ካለ ቢገልጹልን?

**ወ/ሮ ትእግስት፡-** በአጠቃላይ የእንክብካቤ ስራዎች የሚሰሩት በህብረተሰቡ፣ በተቋማትና በእንክብካቤ ማህበራት ሲሆን በዚህም በህብረተሰቡና በተቋማት 308,206 ካሬ ቦታ እና በጥቃቅን አነስተኛ ማህበራትና ፈጻሚዎች ደግሞ 36,759 ካሬ በድምሩ 344,965 ካሬ ቦታ እንክብካቤ እየተደረገለት ሲሆን በዚህም 6 ጥቃቅን አነስተኛ ማህበራት፣ 1501 በህብረተሰብና ተቋማት እና የ10ሩም ወረዳ ፈጻሚዎችን ጨምሮ በእንክብካቤው ላይ ተሳታፊ ናቸው። ከዚህ ባሻገር ደግሞ በክረምት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ላይ ተሳታፊ የነበሩ ድርጅቶችና የመንግስት ተቋማት ከጽ/ቤታችን ጋር በመነጋገርና እቅድ በማውጣት ተሳታፊ መሆን ችለዋል። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህልም የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት፣ አዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ እና የልደታ ክፍለ ከተማ ስራና ክህሎት ጽ/ቤት ይገኙበታል። እንዚህ ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት የልደታ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት በቸክሊስትና ግብረመልስ የተመራ የክትትልና ድጋፍ አግባብ ሲኖረው ሁሉም የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ወረዳና ማንበራትን በመከፋፈልና ከ10ሩም ወራዳ ባለሙያዎች ጋር በጋራ በመሆን ስራዎችን በመስክ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ስራዎች በተቀላጠፈና ጥራቱንና ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ እንዲሰሩ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

**ልደታ ፋና፡-**በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ ትእግስት፡-** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የከተማ አስተዳደሩ የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ለማዋቀር በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 ይህንን ተልዕኮ እንዲወጣ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ለማሳካትና የከተማዋ ነዋሪዎችና እንግዶችን እርካታ ለማረጋገጥ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን መነሻ በማድረግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። የጽ/ቤቱ ዓላማ የልደታ ክፍለ ከተማ ውብና ማራኪ እንዲሁም አረንጓዴ ሆና እንድትታይ በመዋቅራዊ ፕላኑ መሰረት አረንጓዴ መሰረተ ልማት በማልማትና በመንከባከብ የነፍስ ወከፍ አረንጓዴ ሽፋን ተደራሽነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የከተማዋ ወንዞች ጽዳት እንዲረጋገጥ በስፋት ይሰራል፤ በተጨማሪም በህዝብ መጸዳጃ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ በማድረግ የከተማዋ ነዋሪዎችና ጎብኚዎች እርካታን ማሳደግን አላማ አድርጎ እየሰራ ይገኛል። በመሆኑም ከተማዋን በመንግስትና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ውብና ማራኪ ማድረግ፣ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን አሟልቶ ለመተግበር ነዋሪ ህብረተሰብ፣ ባለሀብትና ባለ ድርሻ አካላትን በስፋት በማሳተፍ የዘርፉን ልማት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤ በከተማው መሪ ፕላን መሰረት የተለዩ አረንጓዴ ቦታዎች በስታንዳርዱ መሠረት እንዲለሙ እና እንዲጠበቁ በማድረግ ተደራሽነትና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት፤ የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ ልማትና አስተዳደር ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትኃዊና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት የመስጠት ስራዎችን በማከናወን የፀዱና የለሙ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎችን ዋና የትኩረት መስኮችን መሰረት መስራት ሲሆን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ለመስራት ከከፍተኛ አመራሩ እስከ ፈጻሚ ያለው ድርሻ ወሳኝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማስተባበር ቀሪ ተግባራቶቻችንን መፈጸም ያስችል ዘንድ ሁሉም የራሱን አሻራ እንዲያስቀምጥ ስንል ለባለድርሻ አካላቶችና ይሄ ልማት ለሚመለከተው ሁሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

## ፅዱ ልደታ

በልደታ ክፍለ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት በ2018 ዓ.ም የተቋሙን ስራ ለማሳካት ብዙ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። በዚህ ዘርፍ በዋናነት የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ ተቋማቶች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ያለውን ችግር በዘላቂነት በመፍታት የክፍለ ከተማውን ጽዳት ፣ንጽህና በትኩረት በማስጠበቅ ዘላቂ ጽዱ ክፍለ ከተማ እና ከተማ መፍጠርና የመልሶ መጠቀምና ዑደት ተግባራትን በስፋት መስራት ዋነኛ ተግባሩ ነው ።በመሆኑም በጽ/ቤቱ ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም ምን እንደሚመስል ከፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ አክረም መሀመድሲራጅ ጋር ቆይታ አድርገናል ይከታተሉን።

**ልደታ ፋና፡-** ፅዳትን ባህል ያደረገ ማህበረሰብ ለመፍጠር ቤት ለቤት እየተሰጠ ያለው የግንዛቤ ስራ ያመጣውን ለውጥ ቢገልፁልን?

**አቶ አክረም፡-** የልደታ ክፍለ ከተማን ማህበረሰብ ፅዳት ባህሉ የሆነ ማህበረሰብ አድርጎ ለመለወጥና ለመፍጠር በዚህ አመት ብዙ ስራዎች መስራት ተችሏል ። አጠቃላይ ነዋሪውን ማህበረሰብ በበር ለበር በግንዛቤ ባለሙያዎች ተደራሽ በማድረግ ከ43,500 እማ ወራ አባ ወራ ስለ ደረቅ ቆሻሻ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ስፊ ስራ መስራት ተችሏል ። ህበረተሰብን ማግኘት በሚቻልባቸው በተለያዩ መድረኮች ፣ በሀይማኖታዊ ተቋማቶችና በድርጅቶች በመንግስት ተቋማቶች ስለ ፅዳት ዘመቻ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር በየሳምንቱ አርብ እና ቅዳሜ በበር ለበር በማዕከል ደረጃ የፅዳት ንቅናቄ በቋሚነት በማድረግ ነዋሪውን ተሳታፊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል ። በክፍለ ከተማ ደረጃ ለ5 ወረዳዎች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ የቤት ለቤት ግንዛቤ አሰጣጡን ዘመናዊ ለማድረግ የQR-CODE በማስተግበር ደረጃ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል። በ2018 ዓ.ም 45 ሞዴል ፣ 10 ሞዴል ት/ት ቤቶችን፣ 6 ሞዴል ተቋማቶችን ፣ 3 ሞዴል የሀይማኖት ተቋማቶችን ለመፍጠር ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ብቁ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። በሁሉም ወረዳዎች 2117 ሞዴል ቤተሰብ ለመፍጠር ታቅዶ 2171 ሞዴል ቤተሰብ መፍጠር ተችሏል። የክፍለ ከተማውን ንፅህና በመጠበቅ ረገድ በየሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ በአንድ ማዕከል ለሚደረገው ፅዳት የተሳታፊዎች ቁጥር መጨመሩ እና እየተለመደ መሄዱ የበር ለበር ፅዳት በብዙት በየብሎኮች ነዋሪ ማህበረሰቡ ያለማንም ቀስቃሽ ራሱ በሀላፊነት ማፅዳት መቻሉ እና የክፍለ ከተማው ወጣቶች በፍቃደኝነት ተሳታፊ ሆነዋል።

**ልደታ ፋና ፡-** ከደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አስተዳደር ስርዓቱን ከማዘመን ጋር የተሰሩ ስራዎች ቢገልፁልን

**አቶ አክረም፡-** በሁሉም ወረዳዎች በተቀመጠው የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ ስታንዳርድ መሰረት 32,982.30 ቶን ደረቅ ቆሻሻ ለማጓጓዝ ታቅዶ 27,752.30 ቶን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ላንድ ፊል ማጓጓዝ ተችሏል። ይህም በየዓመቱ ደረቅ ቆሻሻ የማመንጨት አቅም መቀነሱን እና የመልሶ መጠቀምና ዑደት ተግባር ስኬታማ መሆኑን ያመላክታል ። ከዚህ ቀደም ከነዋሪዎችና ከድርጅቶች ከቤት ለቤት ጠዋት ጠዋት ይሰበሰብ የነበረ ደረቅ ቆሻሻ በአዲስ መልኩ እና ቀልጣፋ የከተማዋን እድገትና ለውጥ በሚመጥን መልኩ ማታ ከ 11፡ 30 ጀምሮ ከቤት ለቤት ቆሻሻ የሚወጣበት ሰዓትና ከምሽቱ 4፡00 ድርስ አገልግሎቱ የሚጠናቀቀብ አሰራር ተዘርግቶ በአግባቡ የተሻለ አገልግሎት የመስጠት ስራ በመስራት ውጤታማ ለውጥ እና አሰራርን መዘርጋት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**ደረቅ ቆሻሻን መልሶ ከመጠቀም አንፃር የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን

**አቶ አክረም ፡-**ደረቅ ቆሻሻን መልሶ መጠቀምና ዑደት ተግባርን ስኬታማ ከማድረግ እና አሁን ካለበት 11 ወደ 12.5 ከፍ ለማድረግ ከተሰሩ ስራዎች መካከል በ2018 ዓ.ም በክፍለ ከተማ ደረጃ በህብረት ሽርክና ማህበራቶች የመልሶ መጠቀምና ዑደት ዘርፍ የፕላስቲክና ጠርሙስ ፌስታል በተገቢው መንገድ ለመልሶ መጠቀምና ዑደት አገልግሎት ለማዋል 4100 ቶን ታቅዶ 5121ቶን ለመልሶ መጠቀምና ዑደት ዓላማ ማዋል ተችሏል። በመልሶ መጠቀምና ዑደት ዘርፍ ተደራጅተው ለሚሰሩ ማህበራቶች አስተማማኝ የገበያ ትስስር ለመፍጠርና 54,442,144 ብር ገቢ እንዲያገኙ ታቅዶ 68,673,885.23 ብር ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል ።በክፍለ ከተማችን ባሉ 4ቱ የደረቅ ቆሻሻ ሰብሰብ ሽርክና ማህበራቶች ላይ ወደ ረጲ ከሚጓጓዘው የደረቅ ቆሻሻ መጠን የሚበሰብሰውን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ኮምፖስት ዝግጅት ግብዓት በመለወጥ ከ20 ቶን በላይ የኮምፖስት ዝግጅት ማምረት ተችሏል። በዚህ የመልሶ መጠቀምና ዑደት ዘርፍ የዜጎችን የስራ ዕድል እጣ ፋንታ በትኩረት ተደራሽ ለማድረግ በዘርፉ ለ99 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል። በክፍለ ከተማ ደረጃ በመልሶ መጠቀምና ዑደት ዘርፍ ማህበራቶችን በማደራጀት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመለየት ፣ መልሶ የመጠቀምና የኮምፖስት ፍላጎት በከፍተኛ ለውጥ ማየትተችሏል።

# ቀልጣፋ አገልግሎትን እያሰፈነ ያለ ተቋም

በልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ ለማከናወንና ማስረጃው ለህጋዊ፣ ለኢኮኖሚያዊ ለአስተዳደራዊና ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግና ህብረተሰቡን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የነዋሪነት አገልግሎት አሰጣጥና የወቅታዊ ኩነት ምዝገባ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል።የበጀት ዐመቱ ግብ እንዲሳካም ከአመራና ባለሞያ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ፤ክፍለ ከተማዉ ስር የሚገኙ ወረዳዎችን በማዘመን ለተገልጋዮችም ሆነ አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ከእድርና ተቋማት ጋር በመሆን የሚከሰቱ ኩነቶችን በቅንጂት እንዲመዘገቡ በማድረግ የተጣራ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ መላክ በበጀት ዓመቱ የተያዙ ዋና ዋና ግቦች የሚሳካ ተቋም ነዉ።

በዛሬዉ አምዳችንም ከላይ የጠቀስኩት የልደታ ክፍለ ከተማ ሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት ያከናወናቸዉ ዉጤት ተኮር ተግባራትን ከሲብል ምዝገባና ነዋሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ዘነበች እረና ጋር ቆይታ አድርግናል መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** ወ/ሮ ዘነበች ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ሆነዉ ስለ ተገኙ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ዘነበች፡-**እኔም አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፡-**የልደታ ክፍለ ከተማ ሲቪል ምዝገባና ነዋሪዎች አገልግሎት ጽሕፈት ቤት በ2018 በጀት ዓመት የነዋሪውን እርካታ ለመጨመር የያዛቸው ዋና ዋና ግቦች ምን ምን ነበሩ? እስካሁንስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-**ተቋሙ ከሚሰጣቸው 9 ዋና ዋና አገልግሎቶች መካከል 8ቱን (89%) በዲጂታል ዘዴ መስጠት የጀመረ ሲሆን፣ ባለፉት ወራት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት:30,278 የዲጂታል ነዋሪነት መታወቂያ ተሰጥቷል።21,000 በላይ የኩነት ምዝገባዎች (ልደት፣ ጋብቻ፣ ፍቺና ሞት) ተከናውነዋል። ከሐምሌ 1/2017 እስከ መጋቢት 15/2018 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለ162,413 ዜጎች የብሔራዊ መታወቂያ ምዝገባ አገልግሎት ተደራሽ ሆኗል።



**ወ/ሮ ዘነበች እረና**
**ሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ**

በክፍለ ከተማው በሚገኙ 13 የጤና ተቋማት (5 ሆስፒታሎችና 8 ጤና ጣቢያዎች) ምዝገባው እንዲከናወን በመደረጉ፣ 4,190 ህጻናት በተወለዱ በ24 ሰዓት ውስጥ የልደት ካርዳቸውን በነጻ ማግኘት ችለዋል።

ቅንጅታዊ አሰራርና የመረጃ ጥራት በተመለከተ የሰራናቸዉ ስራዎች ከሃይማኖት ተቋማትና ከእድሮች ጋር በመቀናጀት የኩነት መረጃዎች በወቅቱ እንዲመዘገቡ ተደርጓል፣ የወረዳ ጽሕፈት ቤቶችን በማዘመን ለተገልጋዮችም ሆነ ለሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ ተፈጥሯል፣ የተጣራ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ የማድረስ ግብ ተሳክቷል።

**ልደታ ፋና፡-** ቀደም ሲል በጽሕፈት ቤቱ ይስተዋሉ የነበሩ እንደ የአገልግሎት መጓተት፣ የሰነድ አያያዝ ክፍተቶች እና ተያያዥ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችን ለመቅረፍ በዚህ በጀት ዓመት ምን ተሰራ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በዚህ በጀት ዓመት ቀደም ሲል በጽ/ቤቱ ይስተዋሉ የነበሩ ለአገልግሎት አሰጣጥ መጓተት፣ የሰነድ አያያዝ ክፍተቶች እና ተያያዥ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችን ለመቅረፍ የተወሰዱ ተጨባጭ እርምጃዎች ወረዳዎች ላይ ይስተዋል የነበረ የመብራት መቆራረጥ ችግር ሶላር በመጠቀም የአገልግሎት አሰጣጥ መስተጓጉሎች እንዲቀረፍ ተደርጓል። በተለይም አንድ እንድ ወረዳዎች ላይ ከወረዳው ገቢዎች ጋር በመሆን ጀነሬተር እንዲጠቀሙ በማድረግ ችግሩ እንዲቀረፍ ተደርጓል፡ ፡ ሌላው በበጀት አመቱ የመልካም አስተዳደር እንቅፋት ተደርጎ የተያዘው የተቀላቀሉ ወረዳዎች አካባቢ የነዋሪዎችን ፋይል የመለየትና የማደራጀት ችግር ሲሆን ይህ ችግር በቂ የሆነ የፋይል ቤት በማዘጋጀት የነዋሪዎችን ፋይል የመለየትና የማጥራት እንዲሁም በግልጽ በቀበሌና በቀጠና አደራጅቶ የማስቀመጥ ስራ በመሰራቱ መረጃዎችን በቀላሉ የማግኛ ስልቶችን መጠቀም ተችሏል። በሶስተኛ ደረጃ ለመልካም አስተዳደር ችግር ተደርጎ የተያዘው በአካል ተገኝተው አገልግሎት ማግኘት የማይችሉ ነዋሪዎች መኖራቸው ሲሆን ለእነዚህ ነዋሪዎችም የቤት ለቤት አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ ተደርጓል፡ ፡ከዚህ ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ የተሰጠው በማንዋል ሲሆን አገልግሎት ያገኙ አካላት ብዛት ከ56 በላይ መሆናቸውን በቂ መረጃ አደራጅቶ መያዝ ተችሏል።



**የጽ/ቤቱ ምቹ የስራ ሁኔታ**

**ልደታ ፋና፡-** አንድ ነዋሪ የልደት፣ የጋብቻ ወይም የነዋሪነት መታወቂያ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈጅበትን ጊዜ ለማሳጠር ምን አይነት አዳዲስ አሰራሮች ወይም ቴክኖሎጂዎች (ዲጂታላይዜሽን) ስራ ላይ ውለዋል?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** ተቋሙ ለነዋሪዎች ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ልደት፣ ጋብቻ፣ ፍቺ፣ ሞት፣ ልደት፣ ድጂታል የነዋሪነት መታወቂያ፣ በህይወት ስለመኖር ማረጋገጫና ሌሎችም አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሰጡ ሲሆኑ አብዛኞቹን አገልግሎቶች ከስታንዳርድ በላይ መስጠት እንደተቻለ የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል። እነዚህ በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚሰጡ አገልግሎቶች cashier እና case two ላይ ተንጠልጥለው እንዳይቆዩ ድጋፍና ክትትል በማካሄድ፤ የተቋሙ ባለሙያዎች አዳር ገብተው ለሊት እንዲሰሩ በማድረግ እና የዘመቻ ስራዎችን አጠናክሮ በማካሄድ በሁሉም ወረዳዎች የተሰጡ አገልግሎቶችን cashier እና case two ላይ ዜሮ /free pending/ ማድረግ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ በ2018 ዓ.ም በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በአዲሱ ሲስተም (በአዲሱ VPN) ለነዋሪዎች አገልግሎት ለመስጠት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን በክፍለ ከተማችን ስር ካሉት 10ሩ ወረዳዎች መካከል 9ኙ ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ በአዲሱ ሲስተም አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። በአዲሱ VPN አገልግሎት ለነዋሪዎች መስጠት ያልጀመረው በወረዳ 02 ሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት ላይ ሲሆን ይህ ወረዳ የኔት ወርክ ዝርጋታ ተደርጎለት ቀጥታ ወደ ተግባር ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛል። ሌላው በ2018 በጀት ዓመት የአገልግሎት አሰጣጥ ፍጥነት እና ጥራት እንዲኖር ለማድረግ የDMS ስራ ማለትም በክፍለ ከተማችን ስር ለሚገኙ ከ3000 በላይ የነዋሪዎችን ፋይል ስካን የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና፡-** በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚዎች ነዋሪውን በታማኝነትና በቅንነት እንዲያገለግሉ ምን አይነት የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት እየተገበራችሁ ነው?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** እንደሚታወቀው አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት መካከል የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት በዋናነት ይጠቀሳል። ይህ ተቋም ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚለየው ለሰው ልጅ ከውልደት እስከ ሞት ድረስ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ ነው። ስለሆነም የአገልግሎት አሰጣጡ ጥራት ከፈጻሚው ስነ-መግባር ጋር የተያያዘ መሆኑ አያጠራጥርም። ጥራት ያለው አገልግሎት በየደረጃው ያሉ አካላት እንዲሰጡ ከማድረግ አንጻር እንደ ዋና ስልት ተደርጎ የተወሰደው በቂ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ቅድሚያ በመስጠት አሰራሩ ጥራት ያለው እንዲሆን ማድረግ ነው። በዚህም መሰረት በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በተቋማዊ ሪፎርም ማላቅና የብልሹ አሰራር ስርዓትን ማክሰም፣ በሙያ ስነ-መግባር፣ በተግባቦት ክህሀሎትና በሌሎችም የስልጠና ርዕሶች ዙሪያ በየደረጃው ላሉ አካላት መስጠት ተችሏል። እነዚህን ስራዎች ከመስራት ጎን ለጎን አመራሩም ሆነ ባለሙያው አገልግሎት በአግባቡ ለተገልጋዮች እየሰጡ መሆኑን የድጂታል ካሜራ በ10ሩም ወረዳዎች ላይ በማስገጠም ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ይኛል።

**ልደታ ፋና፡-** በሲቪል ምዝገባ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችንና ደላሎችን ለመከላከል እንዲሁም አሰራሩ ለነዋሪው ግልጽ እንዲሆን ምን ስራዎች ተሰሩ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በ2018 በጀት ዓመት በተቋሙ ሊከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችንና የደላሎችን ጣልቃ ገብነት ለመከላከል የተቀናጁ ስራዎች ተከናውነዋል። በዚህም የአሰራር ግልጽነትን ለማስፈን አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ብቻ እንዲሰጡ ከመደረጉም በላይ፣ የአገልግሎት ክፍያዎችን በቴሌ ብር በመፈጸም እና የአሰራር መመሪያዎችን በQR ኮድና በተለያዩ የህትመት ውጤቶች ለተገልጋዩ ተደራሽ በማድረግ ግልጽነት ተፈጥሯል። ከዚህ በተጨማሪ በ7533 ነጻ የስልክ መስመር አማካኝነት የአሰራር ጥሰቶች የሚጠቁሙበት ስልት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል።

የተጠያቂነት ስርዓትን በማስፈን ረገድም በበጀት ዓመቱ 9 ወራት ውስጥ የዲስፕሊን ግድፈት የፈጸሙ 14 ሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፣ የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎችን የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣትም የተለያዩ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል። በአጠቃላይ እነዚህ ተግባራት መከናወናቸው በተቋሙ ሊከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከልና ተቋማዊ አሰራርን ከማስጠበቅ አንጻር የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻም ምንም እንኳን በዚህ በጀት ዓመት ውጤቶች ቢመዘገቡም፣ አሁንም በስራ ሂደት ላይ ያሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው? ቀሪ የቤት ስራዎቻችሁስ ምንድን ናቸው?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በልደታ ክፍለ ከተማ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ቤት በ2018 በጀት ዓመት አበረታች ውጤቶች ቢመዘገቡም፣ በጤና ተቋማት ለምዝገባ የሚሆኑ ምቹ ቢሮዎችና የግብዓት እጥረት እንዲሁም የሰው ኃይልና የበጀት እጥረት በሥራ ሂደቱ ላይ ተግዳሮት ሆነው ቀጥለዋል። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና አገልግሎቱን ይበልጥ ለማዘመን የነዋሪዎችን ፋይል ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ሥርዓት (DMS) በማስገባት ወረቀት አልባ አሰራርን መዘርጋት፣ በጤና ተቋማት የሚታዩ የቢሮና የቁሳቁስ ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መፍታትና የወረዳ አገልግሎቶችን ማዘመን በቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ናቸው። በተጨማሪም ያለውን የሰው ኃይል በአግባቡ በመጠቀምና ከሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ከእድሮች ጋር በቅንጅት በመስራት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዷል።

**ልደታ ፋና፡-** ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ሆነዉ ጊዜዎን ስለሰጡን እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## አካባቢ ጥበቃና የልደታ አዲስ ምዕራፍ

የልደታ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ዋና ዓላማ የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅና ብክለትን በመከላከል፣ ለነዋሪዎች ምቹና ጤናማ አካባቢን መፍጠር በዘላቂ ልማት መርሆዎች ላይ በመመስረት፣ መጪው ትውልድ ንጹህና አረንጓዴ አካባቢ እንዲወርስ በትጋት መስራት ነው። የከተማዋን የስነ-ምህዳር ሚዛን ለመጠበቅና ለነዋሪዎቿ ምቹና ተስማሚ አካባቢን ለመፍጠር በርካታ ሳይንሳዊና አሳታፊ ስራዎችን በግንባር ቀደምትነት እየመራ ይገኛል። በመሆኑም በበጀት አመቱ የተከናወኑ ተግባራትን መነሻ አድርገን ከአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ሃላፊ ወ/ሮ ቅብአት ገ/ክርስቶስ ጋር ቆይታ አድርገናል ።

**ልደታ ፋና፡-** የአካባቢ ጥበቃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችና ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ምን እንደሚመስል ቢያብራሩልኝ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት በአካባቢ ጥበቃ ረገድ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራባቸው ካሉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የፍሳሽ ብክለትን በዘላቂነት መቆጣጠር እንዲሁም የስነ-ምህዳር መበላሸትን መከላከል ቀዳሚዎቹ ናቸው።



## ወ/ሮ ቅብአት ገ/ክርስቶስ
### የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የአካባቢ ጥበቃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችና ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ምን እንደሚመስል ቢያብራሩልኝ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት በአካባቢ ጥበቃ ረገድ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራባቸው ካሉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የፍሳሽ ብክለትን በዘላቂነት መቆጣጠር እንዲሁም የስነ-ምህዳር መበላሸትን መከላከል ቀዳሚዎቹ ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-** የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላችሁ ቅንጅት ምን ይመስላል?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅትም ከመቼውም ጊዜ በላይ የጠነከረ ሲሆን፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከምርምር ተቋማት፣ ከሲቪል ማህበረሰቡና ከአለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ድርጅቶች ጋር የተቀናጀ አጋርነት ተፈጥሯል። ይህ ቅንጅት ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ በየዓመቱ የሚካሄደውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ውጤታማ ከማድረጉም በላይ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ ዘመናዊ መጋቢ ፕሮጀክቶች በጋራ እንዲቀረፁ ትልቅ አቅም ሆኗል።

**ልደታ ፋና፡-** የፍሳሽ ብክለት ቁጥጥርና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ቢገለፁልኝ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** የፍሳሽ ብክለት ስርዓታችንን ለማዘመንና በባህላዊ መንገድ የሚደረገውን አወጋገድ ለመቀየር በርካታ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ወደ ትግበራ ገብተዋል። ከእነዚህም መካከል በተለይም የፍሳሽ ብክለትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዘመናዊ የፍሳሽ ማጣሪያና ማከሚያ ቴክኖሎጂዎች (Waste Water Treatment Systems) በኢንዱስትሪዎችና በዋና ዋና የፍሳሽ መስመሮች ላይ እንዲገጠሙ እየተደረገ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም ደረቅ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል (Recycling) የሚያስችሉ አሰራሮች እና የቆሻሻ ክምችት ቦታዎችን በጂፒኤስ (GPS) የታገዘ የክትትል ስርዓት በመጠቀም የብክለት አድማሱን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** የብዝሃ-ሕይወት (Biodiversity) መመናመንን ለመከላከል ምን ዓይነት ሳይንሳዊ ጥናቶች እየተደረጉ ነው?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** የብዝሃ-ሕይወት (Biodiversity) መመናመንን በሳይንሳዊ መንገድ ለመከላከል በአካባቢው የሚገኙ እፅዋትና እንስሳትን ስነ-ምህዳራዊ ሁኔታ የሚያጠኑ ጥናቶች ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር እየተካሄዱ ይገኛሉ። እነዚህ ጥናቶች በከተማዋ ውስጥ እየጠፉ ያሉ አገር በቀል እፅዋትን ለመለየትና እነሱን መልሶ በአረንጓዴ ስፍራዎች ላይ ለመትከል የሚያስችል ሳይንሳዊ ፍንጭ የሰጡ ሲሆን፣ የስነ-ምህዳር መዋዠቅን ቀድሞ ለመተንበይ የሚያስችሉ ጠቋሚ መረጃዎችንም እንድናገኝ ረድቶናል።

**ልደታ ፋና፡-** ኢንዱስትሪዎች የሚለቁትን ተረፈ ምርት ለመቆጣጠር የሚደረገው ክትትል ምን ያህል ውጤታማ ነው?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** ኢንዱስትሪዎች የሚለቁትን አደገኛ ተረፈ-ምርት ለመቆጣጠር የሚደረገው ክትትል በአሁኑ ወቅት እጅግ ውጤታማ በሆነ ደረጃ ላይ ይገኛል። ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው ጥብቅ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (EIA) መመሪያ መሰረት፣ እያንዳንዱ ኢንዱስትሪ ከመመረቂያው በፊት የቆሻሻ ማጣሪያ መትከሉ ይረጋገጣል። ከተሰማሩ በኋላም ድንገተኛና መደበኛ የላቦራቶሪ ፍተሻዎችን በማድረግ፣ ህግ ጥሰው ተረፈ-ምርታቸውን በተለይም የፍሳሽ ብክለትን ወደ አከባቢው በሚለቁ ፋብሪካዎች ላይ የማያደላ የእርምጃና የእገዳ ስራዎች እየተወሰዱ ሲሆን፣ ይህም ተቋማቱ ኃላፊነት የሚሰማቸው አረንጓዴ አምራቾች እንዲሆኑ አስገድዷቸዋል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** አካባቢን መጠበቅ የህልውና ጉዳይ ነው። የምንተነፍሰው አየር፣ የምንጠጣው ውሃና የምንኖርባት ከተማ ፅዱና አረንጓዴ መሆን የምትችለው እያንዳንዳችን ለአካባቢያችን ጥበቃ የባለቤትነት ስሜት ሲኖረን ብቻ ነው። በተለይም የፍሳሽ ብክለትን በጋራ በመከላከል፣ ለመጪው ትውልድ የምትመች ለኑሮ ተስማሚ ከተማን ለማውረስ የምናደርገውን ጥረት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በንቃት እንዲደግፍ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**ልደታ ፋና፡-** ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ሆነዉ ጊዜዎን ስለሰጡን እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## የህዝብ ተሳትፎ ስኬት

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ መላው የሀገራችን ህዝቦች በሃሳብ፣ በዕውቀትና በሃብት ያደረጉት ተሳትፎ የቁርጠኝነታችንና የብሄራዊ አንድነታችን ትልቅ ማሳያ ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል። በዚህ ታሪካዊና አገራዊ ፕሮጀክት ውስጥ የየደረጃው ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ህዝቡን በማንቀሳቀስና ሀብት በማሰባሰብ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል። ከእነዚህ መካከል የልደታ ክፍለ ከተማ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ በማስተባበር፣ በየወቅቱ የሚጠበቁበትን ግቦች በማሳካትና የአሰራር ግልፅነትን በማረጋገጥ ረገድ ተጠቃሽ ስራዎችን ማከናወን ችሏል።ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት እያከናወናቸው ያሉ ዋና ዋና ተግባራት፣ኃላፊነቶች እና የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ የተሰሩ የኦዲት ስራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።



**አቶ ኤፍሬም መገርሳ**
**የልደታ ክ/ከተማ የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ**

አገራዊ ጥሪን ተቀብሎ ህዝቡ በላቡና በጥሬ ገንዘቡ የሚያደርገው አስተዋፅኦ በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት ጽ/ቤቱ በፅኑ ያምናል። በመሆኑም የተሰበሰበው የህዝብ ሃብት በአግባቡ ለታለመለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ፣ የአሰራር ግልፅነትን ማስፈንና የተጠያቂነት ስርዓትን መገንባት የዕለት ተዕለት የትኩረት አቅጣጫ ነው። ይህንን ለማረጋገጥም በየበጀት ዓመቱና በየሩብ ዓመቱ ጥብቅ የፋይናንስና የንብረት ኦዲት ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን የኦዲት ስራዎች መካከል የቦንድ ሽያጭ መግለጫዎችን፣ የ8100 አጭር የፅሁፍ መልዕክት ድጋፎችን፣ በየደረጃው ከሚገኙ ተቋማትና ግለሰቦች የተሰበሰቡ የገንዘብ ልገሳዎችን በዝርዝር የመፈተሽ ስራ ይገኝበታል። የክ/ከተማችን የመንግስት ሰራተኞች የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ለህዝብ ይፋ ከተደረገበት ማለትም ከመጋቢት 24/2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ አቅማቸውን የፈቀደውን ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበረውን የቦንድ ግዢ የኦዲት ስራ እና ቦንድን በተመለከተ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ቦንድ ያልወሰዱ 233 የክ/ከተማችን ሰራተኞች 612 ቦንድ 264,575 ብር መጠን ያለው ስማቸውን ከተለያዩ ፑሎች በመልቀም ቦንዱን እንዲወስዱ እያደረግን ያለንና የኦዲት ስራን ጨምሮ ሰነዶችን በማሰባሰብ ለማዕከል የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል።

ከተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት በደመወዝ ቅናሽም ሆነ በፈቃደኝነት ቃል የተገቡ (Pledge) የተሰበሰቡ ገቢዎች በባንክ ገቢ የተደረጉበት ማረጋገጫ (Bank Advice) እና ህጋዊ ደረሰኞች እርስ በእርስ የመቀመርና የማጣጣም (Reconciliation) ስራ በኦዲት ሂደቱ ተከናውኗል። በተጨማሪም ለቦንድ ሽያጭ የተዘጋጁ ሰነዶችና በእጅ ላይ ያሉ ቀሪ የቦንድ ደረሰኞች ቁጥር ተቆጥሮ በትክክል መመዝገቡ ተረጋግጧል።

በዚህ የኦዲት ስራ አማካኝነት በክፍለ ከተማው የተሰበሰበው እያንዳንዱ ሳንቲም ያለ ምንም ጉድለትና መባከን ለታለመለት ታላቅ አገራዊ ዓላማ በቀጥታ ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ ተችሏል። ይህም ጽ/ቤቱ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን አመኔታ ይበልጥ ያጠናከረው ሲሆን፣ ነዋሪው ለቀጣይ አገራዊ ጥሪዎችና ድጋፎች በሙሉ ልብና ባልተቋረጠ ተነሳሽነት እንዲሳተፍ ትልቅ ስነ-ልቦናዊ መተማመንን ፈጥሯል።

የግድቡ ግንባታ መጠናቀቁን በማስመልከት ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ በከፊልም ቢሆን የሚያመላክት ታሪካዊ ፍሰቱን የጠበቀ አንድ ደረጃውን የጠበቀ ፎቶ አልበም ማዘጋጀት ተችሏል።

የግድቡ ግንባታ በስኬት መጠናቀቁን የሚያመላክት የህተሰቡ ተሳትፎ የነበረውን የገንዘብ ድጋፍ ወደ ዳታ ቤዝ የገባውን የሀብት አሰባሰብ መረጃ በሀርድ ኮፒና በሶፍት ኮፒ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል። ሌሎች የጽ/ቤቱ ዕቅዶች፣ሪፖርቶች፣ብሮሸሮች በንዶች፣ የሀብት አሰባሰብ ሰነዶች፣የህዝብ ንቅናቄ ሰነዶች የዶክመንቴሽን ስራ ተሰርቷል። በአጠቃላይ ከላይ የተገለጹት ተግባራት በቀጣይ ለሚሰሩ ፕሮጀክቶች እንደ ተሞክሮ ያገለግል ዘንድ ሰነዶችን በማደራጀት የዶክመንቴሽን ስራ ተሰርቷል።

## የቁጥጥር ሥርዓት ለጤና ደህንነት!

ሀገራችን ኢትዮጵያ የጀመረችው ሁለንተናዊ የለውጥ ጉዞ በተጨባጭ ውጤቶች ታጅቦ ወደ ብልፅግና እየተሸጋገረ ይገኛል።የሁላችን መለያ የሆነችው አዲስ አበባም "እንደስሟ አበባ" የማድረግና የብልፅግና ተምሳሌት የመሆን ሥራዋ በአስደናቂ ፍጥነት እየቀጠለ ነው።ከእነዚህ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች መካከል ደግሞ የጤናው ዘርፍ በሽታን በመከላከልና ጥራት ያለው አገልግሎት ለዜጎች ተደራሽ በማድረግ ረገድ ግንባር ቀደሙን ስፍራ ይይዛል።

ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት እንዲሰፍን ደግሞ ጠንካራ የቁጥጥር (Regulatory) ሥርዓት መዘርጋት ወሳኝ መሆኑ አያጠያይቅም።በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን የልደታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፣የምግብና መድኃኒት ምርቶችን ደህንነት፣ጥራትና ፈዋሽነት በማረጋገጥ የሕዝባችንን ጤና የመጠበቅ ከባድ አደራ ተጥሎበታል።

የ2018 በጀት ዓመት ለቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤታችን ልዩ የሚያደርገው፣የተጀመረው የሪፎርም ሥራ ወደ ላቀ ደረጃ የተሸጋገረበት መሆኑ ነው።በተለይም ተቋሙ ወደ ዲጂታላይዜሽን 2030 (Digital 2030) ስትራቴጂ በመሸጋገር፣የወረቀት አልባ (Paperless) አሠራርን በቁጥጥርና በአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓታችን ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል።ይህ የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎታችንን ቀልጣፋና ከቢሮክራሲ የጸዳ በማድረግ የተገልጋይን እርካታ ጨምሯል፤የቁጥጥር መረጃዎቻችን በዲጂታል ሥርዓት እንዲመዘገቡ በማድረግ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን አረጋግጧል እንዲሁም የባለሙያ ብቃት ማረጋገጫና የቁጥጥር ግኝቶችን በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሕገ-ወጥ ምርቶችን ዝውውር ለመግታት አስችሎናል።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከ8.1 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች፣ምግቦችና መጠጦች ተከታትለን ማስወገዳችን የዚሁ ጠንካራ ክትትልና የቴክኖሎጂ እገዛ ውጤት ነው።አሁንም የቁጥጥር ሥራችንን ይበልጥ በማዘመንና በቴክኖሎጂ በማጠናከር፣ኅብረተሰባችን ከስጋት ነፃ የሆነ የምግብና መድኃኒት አገልግሎት እንዲያገኝ በቁርጠኝነት እንሠራለን።

በመጨረሻም በዚህ ስኬታማ የሥራ አፈጻጸም ውስጥ የድርሻችሁን ለተወጣችሁ ለጽሕፈት ቤታችን አመራሮች፣ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ምስጋናዬን እያቀረብኩ፤በቀጣይም በዲጂታል ሽግግራችን ታግዘን የሕዝባችንን ጤና በጋራ እንድንጠብቅ ጥሪን አስተላልፋለሁ።



**አቶ በላይነህ ገብሩ**
**የልደታ ክ/ከተማ የምግብና መድሃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤታችሁን የያዘውን ዓላማ ግቡን እንዲመታ የተሰሩ የግንዛቤ ስራዎችን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎችን ቢያብራሩልን?

**አቶ በላይነህ፡-** ጽ/ቤታችን የሚሰራውን ስራ ለህብረተሰቡና ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ስራ በመስራት የተያዙት ግቦች እውን እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስራዎችን ሰርተናል፡፡በዚህም ለምክር ቤት አባላት፣ለሴቶችና ህጻናት አደረጃጀቶች፣ለወጣቶች፣ለአመራሮችና ሰራተኞች በአዋጅ 84/2016 እና በጽ/ቤቱ እየተከናወኑ ስለሚገኙት ስራዎች የግንዛቤ ስራዎችን የተሰሩ ሲሆን ይህም ሁሉም አካላት ከመድሃኒት ቁጥጥር ጋር የሚሰሩ ስራዎች ላይ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እያደረግን እንደኛለን፡፡ከዚህ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን የልደታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፣የትንባሆ ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙባቸውን አሰሳች ስልቶች በማጋለጥ ተጠቃሚነትን ለመቀነስ ለወጣቶችና ነዋሪዎች ተደጋጋሚ የሆኑ መድረኮችን ፈጥረናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ጊዜ ያለፈባቸውን መዳኒቶችና ምግቦች ጥቅም ላይ እንዳይውሉና እንዲወገዱ ከማድረግ አንጻር ምን ሰራችሁ?

**አቶ በላይነህ፡-** ጊዜ ያለፈባቸውን መዳኒቶችና ምግቦች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በመስራት መዳኒቶችንና ምግቦችን የማስወገድ ስራ ሰርተናል፡፡ይህ ርምጃ መወሰዱ የተጠቃሚዎችን ጤና መጠበቅ ችለናል፡፡ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲጋራ በሚያስጨሱና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ችግር ባለባቸው ተቋማት ላይ ጥብቅ እርምጃ ተወስዷል፡፡ሌላው በ2018 በጀት ዓመት ከተከናወኑ ስራዎች ውስጥ የህዝብን ጤና ለመጠበቅና የግብዓቶችን ጥራት ለማረጋገጥ፤የጤና ተቋማት ቁጥጥር፤የመዳኒት ቤቶችና ባለሙያዎች ላይ የተከናወኑ የቁጥጥር ስራዎች ውጤትን አስመዝግበናል፡፡ከምግብ ማከፋፈያና መሸጫ ተቋማት ላይ በተደረገው የቁጥጥር ስራ ላይ የውኃ ናሙናዎችን በመውሰድ ምርምራ በማካሄድ የህብረተሰቡን ጤና እንደማይጎዱ የማረጋገጥ ስራን ሰርተናል፡፡
ትምባሆ ማጨስ በተከለከለባቸው የሕዝብ መገልገያ በታዎችና ተቋማት ላይ ቁጥጥር በማድረግ ህብረተሰቡን ከሲጋራ ጭስ መከላከል ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የብቃት ማረጋገጫና ደረጃን ለማስጠበቅ የሰራችሁትን ስራ ቢገልጹልን

**አቶ በላይነህ፡-** ተቋማትና ባለሙያዎች የሚፈለገውን መስፈርት አሟልተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በወሰድነው እርምጃ ለጤና ተቋማት፣ለመድኃኒት ቤቶች እና ለባህል ሕክምና ተቋማት እንዲሁም በምግብ ዘርፍ ለ6 አምራቾች፣ለ1 አከፋፋይ፣ለ27 አገልግሎት ሰጪ እና ለ7 መሸጫ ድርጅቶች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡የብቃት ዕድሳትን ስንመለከት ደግሞ ለ512 ምግብ አገልግሎት ሰጪዎች ፣ለ197 መሸጫዎች እና ለ106 አምራቾች ፈቃዳቸውን በማደስ ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡በጤና ነክ አገልግሎት ዘርፍ 229 ተቋማት እንዲሁም 40 አከፋፋይና መሸጫዎች የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ተከናውነዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የምግብና መድሃኒት ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር ከማድረግና ችግር በፈጠሩ ተቋማት ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ በላይነህ፡-** በምግብ ተቋማትና የትንባሆ ተጋላጭነት በሚበዛባቸው ስፍራዎች ላይ የሕግ ማዕቀፎችን የማስከበርና የቁጥጥር ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡በ2018 በጀት ዓመት ውስጥ በ1,323 ተቋማትና የሕዝብ መሰብሰቢያ በታዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ተከናውኗል፡፡በበጀት ዓመቱ በተከናወኑ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች፣የሕዝብን ጤና አደጋ ላይ የሚጥሉ ግድፈቶች በተገኙባቸው ተቋማትና ባለሙያዎች ላይ እንደጥፋታቸው ክብደት የሚከተሉት እርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን ለ165 ተቋማት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፤ለ32 ተቋማት ጊዜያዊ እሸጋና ለ1 ተቋም ፈቃድ የመሰረዝ ስራን አከናውነናል፡፡እርምጃዎች እንዲወሰዱ ምክንያት የነበሩ ጉዳዮችም፤አገልግሎት ያለፈበት ምርት ይዞ መገኘት፤የአካባቢና የግል ንጽሕና አጠባበቅ ጉድለት እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይዙ ወይም ሳያድሱ መሥራት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች ከማስወገድ አንጻር የተከናወነ ተግባር ምን ይመስላል?

**አቶ በላይነህ፡-** የልደታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅና ጥራታቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ከገበያ እንዲወገዱ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ውጤታማ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡የ2018 በጀት ዓመት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን መድኃኒቶች ውገዳ አፈጻጸም ስንመለከት 6,405.6 ኪ.ግ ምርቶች የተወገዱ ሲሆን በገንዘብ ሲተመንም 8,139,603.96 ብር የሚሆን ምርትን በማስወገድ የህብረተሰቡን ጤና መጠበቅ የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**አቶ በላይነህ፡-** የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ስራዎች ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ፍሬያማ እንዲሆኑና ከምግብና መድሃኒት ጋር ተያይዞ ችግሮች በማስወገድ የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪየን አቀርባለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ስለ ቃለ ምልልሱ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ በላይነህ፡-** ለተደረገልኝ ቃለ-መጠየቅ በራሴ እና በጽ/ቤቱ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡